# ምዕራፍ ሠላሳ አራት

## የራስ ስብሐት ወደ ኢትዮጵያ ጐራ መመለስ — የአንቶኔሊ ግስጠንተቴያ የኢትዮጵያ ጦር በሜዳ፤ የኢጣሊያ ጦር በምሽግ ለመገኘ ስለ መፈላለጋቸው ።

ንጉሥ ነገሥቱ በዩሃ ከእቴጌ ጣይቱ፤ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ከሌሎችም ጋር በሰፈሩበት ሰዓት ሁለት አስደሳች ነገር ገጥሟቸዋል ። አንደኛው፤ ከራስ መንገሻ ዮሐንስ ጋር ባላቸው ጠብ የተነሣ ለኢጣልያኖች ገብተው ያገለግሉ የነበሩት የራስ ስብሐትና የደጃች ሐጎስ ተፈሪ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ጐራ መመለስ ነው ። ሁለቱም የስመ ጥሩው የአጋሜ ባላባት የደጃች ሰባጋዲስ ተወላጆች ስለሆኑ፤ የአጋሜና ይነስ ይብዛ የእንደርታም ሕዝብ ስለሚከተላቸው፤ እነዚህ ሁለት መኳንንት ቀድሞ ከኢጣልያ ጋር በነበሩበት ጊዜ በግናቸውም ረገድ በወታደር ምልመላ በስንቅ አቀራረብ በወሬ ስለላ ጣልያንን ይጠቅሙበት ከነበረው ጐራ አሁን ወደ ወገናቸው ሲመጡ፤ ለኢትዮጵያ የሚሰጡትና በውነትም የሰጡት ጥቅም ብዙ ሲሆን በዚያው መጠን የኢጣልያን የጦር ጐራ ክፉኛ ጐድተውታል ። የኢጣልያ ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒና ጠቅላይ የጦሩ አዛዥ ባራቲዬሪ፤ "ኢትዮጵያ አንድነት የሌላት አገር ነች ። ጦርነቱ ገና ሳይጀመር የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ምኒልክን ከድተው ወደያውራጃቸው ይመለሳሉ ። ወይም ወደኛ ይገባሉ" ብለው ሲጠባበቁ፤ ይልቁንስ ከነርሱ ጋር የነበሩት ወደአገራቸው ጐራ መግባት ጀመሩ ።

ሁለተኛው ያፄ ምኒልክና የመኳንንቱ ደስታ በአውሳ የመሐመድ አንፋሪ የመሸነፉን ወሬ መስማታቸው ነው ። ጦርነቱም በጥር 12 ቀን ተፈጽሞ ይኸን ወሬ ለማብሰር ከአውሳ የመጣው መልእክተኛ ዩሃ ዐፄ ምኒልክ ዘንድ የደረሰው፤ በየካቲት 22 ቀን የዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ላይ ነው ። የዚህም ሁሉ ሁኔታ የኢትዮጵያን ወታደር ሞራሉን ከፍ እያደረገው ሲሔድ የኢጣልያኖችን ዝቅ እያደረገው መጥቷል ።

እስካሁን ድረስ ንጉሠ ነገሥቱን በጣም ያስቸገራቸው፤ አንደኛ ኢጣልያኖች እንደዚያው እንደ መቀሌ በአዲግራት፤ በእንቲጮና በሳውሪያ መሽገው ከምሽጋቸው ውስጥ ሆነው መጠባበቅ እንጅ ወደ

ሜዳ ወጥተው አለመግጠማቸው ፤ ሁለተኛ ጦርነቱን ከፈሩት ደግሞ
ታርቀው አገር ለቀው አለመሔዳቸው ፤ ሦስተኛ ቤቱን ንብረቱን ትቶ
ለጦርነት የመጣው ቁጥሩ ከ80,000 እስከ 100,000 የሚደርሰው
ጦርና የርሱ ተከታይ አሽከር ገረድ ቤቱን ለቆ ከወጣ አምስት
ወር ስለሆነው ፣ በዚህም ጊዜ የያዘው ስንቅ በሶውም ፣ ጭብጦውም ፣
ቆሎውም አልቆበት ስለሚራብና በዙሪያው የሚገኘውን አገር ፣ ትእ
ዛዝ እየተላለፈ ፣ በመዝረፍ ከባላገሩ ጋር ጠብ ማብቀሉ ፣ ያለበት
አገር በከብትና በእህል ረገድ ይኸን ያህል ስለማያወላዳ ፣ ተዋ
ጊውን ወታደር እየቀለበ ለከብቱም ሁሉ ሣር እያቀረበ ሊያዋጋ አይ
ችልም ። ከደቡብ አውራጃዎች እያጓዙ ወታደሩን የማጥገቡ ነገር
በዚያን ጊዜ የማጓጓዣው ድርጅት ጉድለት በተለይ ሰሩቅ አገር
የተሟላ ባለመሆኑ ችግር ፈጥሯል ። እስከዚህም እስከ አምስት ወራት
የተደረሰው በዚሁ በእህያና በአጋሰስ እየተጫነ ፣ በሰውም ትከሻ
ከሩቅ አውራጃዎች በሹማምንቱ ፣ በጭፍራው ፣ በገባሩና በገበሬው
ትጋትና ድካም የመጣ ነው ።

ዋና ስንቅ መስፈሪያው ወረይሉና ቦሩ ሜዳ ላይ ነው ። ከሸዋ
የሚመጣው ወታደር ሁሉ በያዘው ስንቅ ተጨማሪ ቦሩ ሜዳ ላይ
ተሰፍሮ እየተሰጠው ነው ጉዞውን ወደ ሰሜን ቀጥሎ እዚህ ሰዓት
የደረሰው ። ቦሩ ሜዳና ወረይሉ (ሆሪው) የስንቅ ኃላፊ የሆኑት ቢቶ
ደድ አጥናፌ ተከለ ዮሐንስ ፣ ከሸዋና ከየትኛውም ከፍል በከብትም
በሰው ትከሻም የሚመጣውን ዱቄቱንም ፣ ጥራጥሬውንም እየተቀ
በሉ ወደጦሩ ግንባር በመላክ ታላቅ አገልግሎት ማድረጋቸው ቢታ
ወቅም ፣ ጊዜው በተራዘመ መጠን ችግሩ በጣም እየከበደ ይሔዳል።

ዳግማዊ ምኒልክም ፣ መሳፍንቱም ፣ መኳንንቱም ፣ ወታደሩም በዚህ
ሁሉ ችግር መካከል ስለሚገኙ ፣ ይኸን ሁሉ ጦር ይዘው ንጉሠ ነገ
ሥቱ ወይ ካልተዋጉ ወይ ካልታረቁ ፣ እንደዚሁ ዝም ብለው ባሉበት
ሥፍራ ሰረጅም ዘመን መቆየት አይሆንላቸውም ። በዚህ ምክንያት
ከዩሃ ተነሥተው መረብን አልፈው ሐማሴንንና አከለ ጉዛይን ለመ
ውጋትና ከዚሁ ከኤርትራ በተለይ ከምጽዋና ከአሥመራ ወደ አዲግ
ራት ፣ ወደ ሳውሪያ ለዋናው የኢጣልያ ጦር ሠራዊት የሚመጣውን
የመሣሪያና የምግብ እርዳታ ለማቋረጥና ጣልያኖቹን አስገድዶ እንዲ
ዋጉ ለማድረግ ታስቦ በቅድሚያ እነሊቀ መኳስ አባተ ወደ መረብ
ቦታውን ለማጥናት ተላኩ ፤ እነርሱ ደግሞ ፣ “የመረብ ወሃ ስለ ደረቀ
እንኳን ለጃንሆይና ለሠራዊቱ ለእኛም እዚህ ላለነው አልበቃንምና
ጃንሆይ እዚያው ቢቆዩ ይሻላል” የሚል መልእክት አስተላለፉ ።
የነርሱንም ሐሳብ በኋላ እነራስ መንገሻ ዮሐንስ አጽድቀውታል ።



ስለዚህ አልፎ የመሔዱ ጉዳይ በወሃ እጦት የተነሣ ሳይሳካ ቀረ ።
አሁን በፊታቸው ያለው ወይ ከምሽጉ ድረስ ሔደው የኢጣልያን
ጦር መውጋት ወይም በልዩ ልዩ ዘዴና ወታደራዊ ንቅናቄ (ማኑቨር)
የጠላት ጦር ከምሽጉ እንዲወጣ ማስገደድ ነው ። ወደ ምሽጉ
ሔዶ መዋጋት ሕዝብ ማስጨረስ መሆኑን ከመቀሌውም ጦርነት
ተምረውታል ። አሁንም በቅርብ ያሉት እነራስ መንገሻም ፣ ሌሎቹም
ወደ ምሽግ ተጠግቶ የመዋጋቱ ነገር እንዳይታሰብ በጥብቅ አስጠን
ቅቀዋል ።

ስለዚህ ፣ በኢጣልያኖች በኩልም ፣ “የኢትዮጵያ ጦር ወደ ምሽጉ
መጥቶ ካልወጋን በቀር ሜዳ ላይ ወጥተን አንችለውምና በተቻለ
መጠን ከምሽግ ወጣ እያሉና እየተነኳኰሱ ወደ ምሽግ በመመለስ በን
ዴት ወደ ምሽግ መጥቶ እንዲዋጋ ማድረግ ነው” እያለ ሰጣልያኖቹ
የሚመክረው ብዙ ነው ። በነርሱም በኩል ተመሳሳይ ችግር ስላለባቸው
እንዲያውም ፣ “ከምሽግ ወጥቶ ወደኋላ ወደ አሥመራ መመለስ
ይሻላል ” ብሰው አሳብ የሚያቀርቡም ነበሩ ይባላል ።

ከዚህ ቀደም እንዳመለከትነው ፣ በአርጀንቲና የኢጣልያ ወኪል
ሆኖ የተቀመጠው ኢትዮጵያን ዐውቃለሁ ባዩ አንቶኔሊም ካለበት
ከሩቅ አገር የሚልከው ምክር ይኸንኑ የሚያሳስብ ነው ። የዓድዋ
ጦርነት ሊደረግ ስምንት ቀን ሲቀረው እነራስ ስብሐት የኢጣል
ያን ጐራ ትተው ከመጡ ወዲህ ፣ ይኸው ሰውዬ እ. ኤ. አ.
የካቲት 21 ቀን 1896 ዓ. ም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በላከው ማሳሰቢያ
ውስጥ ፣

> “...ከዚህ በፊት ራስ ስብሐትን መጠርጠር ያስፈልጋል ብዬ
> በቴሌግራም አስተላልፌ የነበረው እነሆ አሁን ከሁለት ወር በኋላ
> መሸፈቱን (ወዳጼ ምኒልክ መዞሩን) ስማሁ... አሁን በደረስንበት
> ሁኔታ በዚህ ዓመት በተቻለ መጠን ዓላማችን መከላከል እንጂ ማጥ
> ቃት የለብንም ። መቶ ሚሊዮን(ሊሬ) እንኳን ቢኖረን በዚህ ዓመት
> የኢትዮጵያን የቁሣር ግዛት ማሳመን አንችልም ። ከሁለት ወር በኋላ
> የዝናሙ ጊዜ ይዠምራል ። ከራት ወር በኋላ ደግሞ በሚያጥለቀልቀው
> ዝናም ወንዞቹ ሁሉ በጐርፍ ይሞሉና መንገድ ሁሉ ይዘጋል ። ከሌላ
> ስሕተት ላይ እንደገና ካልወደቅን በቀር እንደ ምንም እየተከላከሉ
> ቆይቶ ምኒልክን ከነሠራዊቱ ወደ መጣበት ሲመለስ ማየቱ የተሻለ
> ነው ። በክረምቱ ወራት እስከ ጥቅምት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ
> ለሚመጣው ዘመቻ በፕላን መደራጀት ነው ። ባናበዛው ኖሮ ምኒልክ
> እስከዚህ ሊወጋንም ባልፈለገ ነበር ...”[1] የሚል ይገኝበታል ።

1 La Prima Guerra d' Africa, F. Crispi, PP. 295 - 297

ውስጥ ዐወቅ እንደ መሆኑ መጠን የአንቶኔሊ ምክሩ ተቃሎ የሚታይ አይደለም ። በእውነትም የኢጣልያ ጦር ከምሽግ ወጥቶ ባያጠቃ የዐፄ ምኒልክ ጦር ወደ ምሽጉ ሔዶ ማጥቃትም ፣ በትግሬም ያን ሁሉ ጦር ይዘው ለብዙ ጊዜ መቆየትም ስለማይሆንላቸው ነገሩ ግራ አግቢ ነበር ። ለውጊያው ተስፋ ቆርጠው ወደ ሸዋ ቢመለሱም ፣ ባንድ ወገን ከየካቲት ወይም ከመጋቢት እስከ ጥቅምት ባለው ጊዜ ውስጥ አዳዲስ ወታደር እየመለመሉ ከኢጣልያ አገርም ጦር ጨማምሮ ለመደርጀት ያመቸዋል ።

ራሱ ጠቅላይ አዛዡ ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ በበኩሉ ከምሽግ ወጥቶ በሜዳ መዋጋትን ስለፈራ ፣ አበሾቹ እስከ ምሽጉ ድረስ ሔደው ቢወጉት ድልን እንደሚያገኝ ያምን ነበር ። በዚህ ምክንያት ፣ ዐፄ ምኒልክ ካሉበት ከዩሃ የርሱ ጦር ወደ መሸገበት ወደ እንትጮ ጠጋ ብለው በገንደብታ በሰፈሩበት ጊዜ ውጊያና ድል ለናፈቀው አለቃው ለክሪስፒ እ. ኤ. አ. በየካቲት 9 ቀን 1896 ዓ. ም. ባስተላለፈው ቴሌግራም እንደዚህ ብሏል ።

> የኛና የሸዋ ጦር በትንሽ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ሁለቱም ጥሩ ጥሩ ስፍራ ይዘው ፊት ለፊት ሆነው ይጠባበቃሉ ። እምሽጋችን ድረስ መጥተው ላለመዋጋት መቁረጣቸውን ሰላዮቹ ገልጸውልኛል ። በርግጥም ከምሽጋችን መጥተው ቢወጉን ድል ማድረጋችን እርግጥ ነው ። ከኛ የበረከተው ጦርና ደህና ሥፍራ ይዞ የሚጠብቀንን ሔደን ብንወጋው ድሉ አጠራጣሪ ነው ።...ድሉ ቀንቶን ጠላት ቢሸሽም ወጣገባ በሆነ አገር የኛ የነጩ ወታደር እንደ ጥቁሩ ጠላትን እንደልብ ሊያባርር አይችልም ። [1]

በዚህ ጊዜ ፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦር አንዱ ቅኝ አገር ለማግኘት ፣ ሌላው ያገሩን ነጻነት ለመጠበቅ ለጦርነት በተሰለፉበት ሰዓት ሁለቱም ድልን ሲመኙ ፣ ወደዚህ ድል የሚያመራውን ቁርጠኛ ጦርነት ለማድረግ የሁለቱም ፍላጐት ለየብቻ መሆኑ ግልጽ ነው ። ከዚህ በላይ ላለቃው ለክሪስፒ እንዳስተላለፈለት ፣ "ዐፄ ምኒልክ ካሉበት ከገንደብታ እስከ መሸግሁበት እስከ እንትጮ ፣ እስከ ሳውሪያ ድረስ መጥተው ቢወጉኝ ምሽጌን ይዤ በመዋጋት ድልን አገኛለሁ" ብሎ በናፍቆት እንደሚጠባበቅ ሁሉ ዐፄ ምኒልክም ፣ "የተደበቀበትን ምሽግ ለቆ ወደ ውጭ ወደ ሜዳ ወጥቶ ምነው በተዋጋሁና

1 Memoire d' Afrique..,PP. 349-350



በለየልን" በሚል ምኞት ተይዘው ይጠባበቃሉ ። እኚህን "ወደ ምሽጉ ሔደው አይዋጉ ፤ ሠራዊትዎን ያስጨርሳሉ ። ያንንም ከሜዳ ሔደህ አትግጠም ሠራዊትህ ያልቃል" የሚላቸው የየግል መካር በብዛት አሏቸው ማለት ነው ። ቢሆንም ፣ ሁለቱም ከጥንቃቄና ራስን ከመጠበቅ ጋር ወታደራዊና ስልፋዊ ንቅናቄ ማድረጋቸው አልቀረም ። ዐፄ ምኒልክ ከነበሩበት ከዩሃ ተነሥተው ወደ ገንደብታ ፣ ከዚያም ወደ አሳይ መጥተው ሰፈሩ ። ጣልያኖችም ከተኩዝ በስተደቡብ ያለውን ሳውሪያ (ሱዋሪያ) የሚባለውን ይዘው መሸጉ ። ከዚህም ቀጥሎ ባለው ጊዜ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ የኢጣልያ ሹማምንት ፣ ሦስት መቶም አምስት መቶም ወታደር እያስከተሉ አገርና ስፍራ ምርመራ ሲወጡ እነቀኛዝማች ታፈሰ በሩቅ እያዩ ፣ ሲያባርሯቸውና እስከ ምሽጋቸው እያደረሱ በመመለስ ጦርነት ሲያደርጉ ሰንብተዋል ። ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስም ባንድ ወገን የጠላት ወታደር የሚመላለስበትን መንገድ በሚያውቁት አገር በአጋሜና በእንደርታ እየሔዱ ሲያስናክሉና በማይ መሬት እነፊታውራሪ አምባዬ በሞቱበት ቀን ኃይለኛ ጦርነት ማድረጋቸው አልቀረም ።

ብዙ ጊዜ ደግሞ ፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች የደፈጣ ጦርነት እያደረጉ ጣልያኖቹን ያበሳጩአቸው ነበር ። ዝም ብለው መንገድ አሳልፈው በጫካ ተደብቀው ተኳኩሰው ከተነኮሷቸው በኋላ ጣልያኖቹ ውጊያ ሲያምራቸው ይሰወሩባቸዋል ። ስለዚህ አንድ ካርዴላ የሚባል ሻምበል በጻፈው መጽሐፍ ፣ "እነዚህ ጥቁሮች ፈሪዎች ናቸው ። ሲያዩን ይሸሻሉ ፤ ተበታትነን ስንጓዝ ደግሞ ይወጉናል ጭካኔያቸውም ከፍ ያለ ነው [1] ..." ሲል አመልክቷል ። የነርሱ ከምሽግ አለመውጣት በፍርሃት መሆኑን ግን ፣ ይኸው ካርዴላ ሊጠቅሰው ስለአልፈለገ ፣ አድላዊ ጸሐፊ ነው ማለት ይቻላል ። ካርዴላ ፣ "እነዚህ ጥቁሮች ፈሪዎች ወይም የፈሪ ጨካኞች ናቸው" ብሎ የጸፈውን የመቀሌን ጦርነት የተካፈለው ኮሎኔል አሜን—ዶላጂኒ "ባበሾች ላይ ፈሪ የፈሪ ጨካኝ ብለህ የጻፍከው ከውነት የራቀ ነው ፣ በመቀሌ ጦርነት ፊት ለፊት እየተዋጉ በምሽጋችን ፊት የሬሳ ቁልል ትተው የለምን?" በማለት አስተባብሏል ። ወደፊት ይኸው ካርዴላ በዓድዋ ሲዋጋ ስለ ተማረከ ፣ የሐበሾቹን ጀግንነት የራሱን ፈሪነት በልቡ ሳይገነዘበው አይቀርም ።

ይሁን እንጂ ፣ ዋናው የኢጣልያ ጦር በእንትጮና በሳውሪያ መሽጎ ስለ ተቀመጠና ወጥቶ ከመዋጋትም ስለዘገየ ፣ ዐፄ ምኒልክ ከዚህ ቀደም

1 Da Adua al Congo ,E. Cardella, PP. 17-18

እንዳሰቡት ፣ የመሸገውን ጦር እንዳለ ትተው በግራ በኩል ወደ ሐማ
ሴን ለመዝለቅ ያሉበትን ኀንደብታን ለቀው ወደ አሳይ (ያባ—ገሪማ
ጉልት) ከዚያም ወደ ዓድዋ ዘልቀው ሰፈሩ ። በዚያ ሳሉ ምናልባት
ኢጣልያኖች መጥተው በድንገት ውጊያ የገጠሙ እንደሆነ በማለት
ለጥንቃቄ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ራስ ሚካኤል ፣ ራስ ወሌ ፣ ራስ ቢት
ወደድ መንገሻ ፣ ራስ መኰንን ግንባር ቀደም ሆነው በእባ ገሪማ በኩል
ተሰልፈው እንዲጠብቁ ተደረገ ። ዳሩ ግን ፣ ጣልያኖቹ ከሰፈራቸው ሳይ
ነቃነቁ ዐፄ ምኒልክም ከእባ ገሪማ ዓድዋ መጥተው መሣሪያቸውን
እንደያዙ ሁሉም ሲጠባበቁ ዋሉ ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ ከዚህ በፊት ወደ ኤርትራ ለመዝመትና ጣልያኖ
ችን ከጀርባ ለማጥቃት እንዲያጠኑ እነሊቀ መኳስ አባተን ልከው
እንደነበረ አሁን ደግሞ ራስ መንገሻ ዮሐንስን ፣ ራስ መኰንንን ፣ ፊታ
ታውራሪ ገበየሁን ፣ ፊታውራሪ ተክሌንና ሊቀ መኳስ አድነውን "ወደ
ፊት ሔዳችሁ አዲኳላ ሰፍራችሁ ጠብቁኝ ፣ እኔም ከናንተ ቀጥዬ እመ
ጣለሁ" ብለው ልከዋቸው ነበር ። እነሱም ታዘው ከሔዱ በኋላ መረብ
ሲደርሱ የመረብን ወንዝ ደርቆ ስላገኙት ፣ ከዚህ በፊት እነሊቀ መኳስ
አባተ እንዳሉት ፣ "እዚህ የጃንሆይ መምጣት ይቅርና ለኛም እዚህ
ላለነው የመረብ ውሃ ስለደረቀ ፣ ሰውም ከብትም ከትናንት ጀምሮ
ወሃ ለማጠጣት ተቸግረናል" የሚል መልስ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ ።
ስለዚህም ወደ ሐማሴን ዘልቆ ኢጣልያኖቹን በጀርባ የመክበብና ቅኝ
አገር አድርገው የያዙትን ሐማሴንን ፣ እከለ ጉዛይንና ሰናፌን የመው
ረሩ ነገር ቀረ ።

መረብንም ተሻግሮ ለመዝመት የታሰበበት አንደኛው ጉዳይ ፣
"የያዝነው ግዛት የሚወረር ከሆነ ከምሽጉ ወጥቼ ብዋጋ ይሻላል"
ብሎ የጣልያን ጦር ከምሽጉ እንዲወጣና እንዲዋጋ ለማድረግ የታሰበ
ዘዴ ነበር ። የሆነ ሆኖ ፣ በመጨረሻ ለሰውም በተለይ ለከብት
ሣርና ወሃ በማይጠፋበት በዓድዋ መቆየቱ ይሻላል ተብሎ ተመከረና
ዋናው ሰፈር በዓድዋ እንዲሆን ተወሰነ ። ቢሆንም ጣልያኖች ዐፄ
ምኒልክ እስከ ሐማሴን ዘልቀው ከገርባ ለመውጋት ያላቸውን ሐሳብ
ከሰላዮቻቸው በሰሙ ጊዜ በጣም ሠግተው ነበር ። የኢትዮጵያ ጦር ወደ
ሐማሴን ሔዶ በምጽዋ በኩል ከአሥመራና ከአዲኡግሪ ሳውሪያ ላለው
ለዋናው ጦራችን ስንቅም ፣ መሣሪያም የሚያመላልሰው የተቋረጠ እን
ደሆነ ጦሩ ዙሪያውን ተከቦ በመቀሌ እንደ ሆነው ዓይነት ችግር እንዳ
ይፈጠር በመሥጋት የኢጣልያ ጦር አዛዥ አንድ ብልሃት መፍጠር
ስለ አስፈለገው ፣ አበሾቹ ወደ መረብ እንዳይጓዙ ከአዲግራትና ከሳው
ሪያ ምሽግ ሠራዊቱ እሚዋጋ እየመሰለ በመውጣት የንጉሡ ጦር ባለ
በት በኩል በሰልፍ እንዲታይ ገኔራል ባራቲዬሪ አዘዘ ። በዚህ



ምክንያት የካቲት 17 ቀን የታዘዘው ጦር በሰልፍ ለውጊያ እስመስሎ
ወጥቶ ወደፊት ይጓዝ ጀመር ።[1]

የኢትዮጵያ ቃፊር ጠባቂዎች ፣ የኢጣልያኖችን በሰልፍ መምጣት
በሩቅ ሲመለከቱ በፍጥነት ለንጉሠ ነገሥቱ አስታወቁ ። በዚያን ጊዜ
ዐፄ ምኒልክ የኤፍራታውን ገዥ ደጃች ወልዴንና ያክስታቸውን ልጅ
ደጃች በሻህ አቦዬን ፣ "ወደፊት ቀድማችሁ ሌሊቱን ተጠባበቁ ። እኔም
ሊነጋ ሲል ጦሬን አስከትዬ እደርስባችኋለሁ" ብለው እነርሱ ወደፊት
ቀድመው እንዲጠባበቁ አደረጉና እርሳቸው በማግሥቱ ሊነጋ ሲል ጦራ
ቸውን ለውጊያ ግራና ቀኝ አሰልፈው ራሳቸው ከመካከል ሆነው ነጋሪ
ታቸውን እያስጎሸሙ ወደፊት ተጓዙ ። ዳሩ ግን ፣ "የኢጣልያ ጦር
ያፄ ምኒልክን ንቅናቄ ባየ ጊዜ ፣ በሰልፍ እንደወጣ ምንም ሳይታኮስ
ተመልሶ በግሥጋሤ እምሽጉ ገባ" የሚለው ወሬ ላፄ ምኒልክ ስለ
መጣላቸው ፣ እርሳቸውም ሠራዊቱም አዘኑ ። ይኸን ዓይነቱን ወጣ
ገባ የማለት ሰልፍ ኢጣልያኖች ደጋግመው ሠሩበት ። በዚያን ጊዜ
የኢትዮጵያ መኳንንትና ጦር ሠራዊት ፣ "ብቅ ይሉና ስንመጣባቸው
እንደ ኤሊ እድንጋያቸው ውስጥ እየገቡ ይሸሸጋሉ ፤ እልፍ ስንል ደግሞ
ብቅ ይላሉ ምን ይሻላል" እያሉ በብስጭት እጉረመረሙ ። ከዚያ በኋላ
የሚያደርጉት ቢያጡ የጦር አለቆች ተሰብስበው ፣ "እዚሁ እያለንበት
እንደርና ነገ በጧት ሔደን እምሽጋቸው ድረስ እንግጠማቸው" ብለው
ተማከሩ ። የነርሱንም ምክር ንጉሠ ነገሥቱ በእሺታ አጸደቁት ።

በዚህ ምክር ሁሉም ተስማምቶ ከጨረሰ በኋላ ፣ ከዚህ ቀደም እን
ዳመለከትነው ራስ መንገሻ ዮሐንስ ወደፊት ቀድመው በሌላ ክፍል
ይጠባበቁ ስለነበረ ፣ የዚህን የምክር ውሳኔ በሰሙ ጊዜ በጦራቸው ታጅ
በው በፈረስ ሆነው በግሥጋሤ መጥተው ፣ "ጃንሆይ ጉድባ ጎድቦ ምሽግ
መሽጎ በተቀመጠ ጠላት ላይ በኃይል ብንገባ ሠራዊታችንን ከማስጨ
ረስ በቀር ምንም ጥቅም አናገኝም ። ዐፄ ዮሐንስ ያ ሁሉ ጦራቸው
መተማ ሔዶ ያለቀው በዕንጨት እተመሸገው ምሽግ ገብቶ አይደለ
ምን? ስለዚህ ከድንጊያ እተመሸገው ምሽግ ይኸን ሁሉ ጦር ልና
ስጨርስ አይገባምና እኔ በዚህ አልስማማበትም" ብለው ተናገሩ ።
ሁሉም የርሳቸውን ምክር ልብ አድርጎ ተገነዘበው ። ዐፄ ምኒልክም
"እንግዲህ ወዲያ ኢጣልያኖች በሙሉ መጥተው መታኮሳቸውን ሳላይ
ጦሬን ሁለተኛ አሰልፌ አልነሣም" ብለው እየተበሳጩ ወደ ድን
ኳናቸው ተመለሱ ።[2] ሁለቱም ባላጋራዎች በዚህ መካከል የስንቁ

---

1 Memoire d' Afrique . . Chap. XXIX

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ምዕ. 63 Italia ed Etiopia . . Conti - Rossini, PP. 300-315.

ነገር ከሥጋት ላይ ጥሏቸዋል ። በኢጣልያኖች በኩል ለመብል የሚሆን ሥጋም እልቆ የጭነት በቅሎአቸውን እያረዱ የበሉና የሚበላ ዳቦ ለማግኘት ልብሳቸውን ላገር ተወላጅ ወታደር የሸጡ የኢጣልያ ወታደሮች አሉ ።[1]

እቴጌ ጣይቱም ፣ ራሶቹም ፣ ሹማምንቱም ፣ ወታደሩም በዚህ ነገር በጣም እያዘነ ምን ማድረግ እንደሚሻል በሚወያይበት ጊዜ ፣ እቴጌ ጣይቱ ፣ ደጃች በሻህ አቦዬን ጠርተው ፣ "ወንድሜ ሆይ ምን ይመስልሃል ይኸውና ጦራችንን ሁለት ጊዜ እያሰለፍን እየወጣን ሁለት ጊዜም ምንም ሳናደርግ ተመለስን ። ይኸም የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ አዝኛለሁ" ብለው አማከሩዋቸው ። ደጃች በሻህም ፣ "ጦርነት የሚጀመረው ድንገት ሳይታሰብ ነው ። በጦርነት የሚሞቱትም ገና እህል ውሃቸው ባያልቅ ነው ። ይልቅስ ወደፊት ለሚሞቱት ይዘኑ እንጂ በሌላው ነገር አይዘኑ" ብለው መለሱላቸው ። በኋላም የዓድዋ ውጊያ ለት ደጃች በሻህ አቦዬ በጦርነቱ ላይ ስለሞቱ እቴጌ ይኸንኑ ንግግራቸውን አስታውሰው አዘኑላቸው ።[2]

በዚህ በየካቲት ወር ፣ የኢጣልያና የኢትዮጵያ ጦር አለቆች አንድ ዓይነት የስንቅ ችግር በነበረባቸው ጊዜ ሁለቱ ወገኖች አሳባቸው አልፈጸም ቢላቸውም ፣ በብዙ ችግር በብዙ ውይይትና ዘዴ ፈጠራ አንዱ ሌላውን ወደሚያሸንፍበት ምቹ ሥፍራ ስቦ ለመዋጋትና ለማሸነፍ ሲጣጣር ሰነበተ ። በዚሁ መሠረት ባራቲዬሪ ፣ "በየጊዜው ከምሽግ ውስጥ እንደሚዋጋ ጦር ብቅ እያላችሁ ለኢትዮጵያ ጦር በሰልፍ እየታያችሁ ሲመጡባችሁ ደግሞ ወደ ምሽጋችሁ ተመለሱ" ማለቱ ለጦርነት ሲል ፣ ቤት ንብረቱን ለቆ ከወጣ አምስት ወር ያለፈው የኢትዮጵያ ጦር በንዴት የተመለከተውን ጦር ተከታትሎ እስከ ምሽጉ ድረስ ሔዶ ሲዋጋ የመጣውን ጦር ምሽጋችንን ከለላ አድርገን በመድፍና በመትረየስ በጠመንጃም ፈጅተን በቀላሉ ድል እናደርጋለን በማለት ነው ። ነገር ግን ፣ የነርሱን ብልሃት እነራስ መንገሻም ፣ እነራስ ስብሐትም በትክክል ስለሚያውቁት ፣ ወደ ምሽግ ተሔዶ ጦርነቱ እንዳይደረግ በጥብቅ ማሳሰባቸውን ተመልክተናል ። ንጉሠ ነገሥቱም እነራስ መኰንንም ቢሆኑ የምሽግ ጦር አስቸጋሪ መሆኑን እንደማይስቱት የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ፣ ብዙ ቀን በመፋጠጥ ጊዜው ካለፈ በኋላ ፣ ዐፄ ምኒልክና ሹማምንቶቻቸው ደግሞ የኢጣልያ ጦር ልብ አግኝቶ ምሽጉን ለቆ


1 Gli Italiani in Africa Orientale, A. Del Doca, PP. 640-641.

2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 258




ወደ ውጭ እንዲወጣላቸው በበኩላቸው ልዩ ልዩ የመሳቢያና የማታሰያ ወሬ ይፈጥሩ ጀመር ። ከዚሁም አንደኛው የኢጣልያ ጦር የልብ ልብ በቅቶት ወጥቶ እንዲዋጋ ፣ "የኢትዮጵያ ወታደር ስንቅ እልቆበት ለዘረፋ በያገሩ ተበትኗል ። ይበልጡም በያገሩ ተመልሶ ገብቷል ። እነራስ እገሌም ሞተዋል ። ወይም ከድተዋል ። ዐፄ ምኒልክ ታመዋል" እያሉ ዐውቀው ያስወሩ ጀመር ። ባንድ ወገን ደግሞ እነ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ እነራስ መኰንን ፣ እነራስ ሚካኤል ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እየተማከሩ ፣ "ጦርነቱን ብትጀምር ዞረን ወደናንተ እንገባለን" እያሉ ቢቸግራቸው ለጣልያኑ አዛዥ እስከ መጻፍ መድረሳቸውን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴና ነጋድራስ አፈወርቅ ያረጋግጣሉ ።[1]

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . .ገጽ 258 ፣ ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ፣ ገጽ 32-33



ራስ ወሌ ብጡል ከልጃቸው ከደጃዝማች ዓመዴ ጋር
ከካርሎ አናቶሪ መጽሐፍ



ራስ መንገሻ ዮሐንስ በዓድዋ ዘመቻ ጊዜ
ከኤሪትሪያ ኔልፓሳቶ



በጦርነት ሰዓት የኢጣልያኖችን ጐራ በስውር ለቀው ወደወገናቸው ወደ ዓፄ ምኒልክ ጦር መጥተው የተደባለቁት ራስ ስብሐት

# ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

## የኢጣልያኖች ተታይላኒትና የጄኔራል ዳቦርሚዳ ደብዳቤዎች

ከዚህ በፊት እንዳልነው ፣ ፈረንጆች ከቆዳ ቀለማቸው የበለጠ በሥልጣኔያቸው ስለሚመኩ ፣ ባልሠለጠነው በእስያና በደቡብ አሜሪካ ፣ ይልቁንም ከመልኩ መጥቆር ጋር በሥልጣኔ በጣም ወደኋላ ቀር በሆነው በአፍሪካ ላይ ከጥላቻ ጋር የተደባለቀ ንቀት መኖሩ በየጽሑፉ ላይ ይነበባል ። ናቂዎቹ ኢጣልያኖች የኢትዮጵያን ተወላጅም ሁሉ በጠቅላላው አረመኔዎች እያሉ መጥራትን ያዘወትራሉ ።

ወደ ቀይ ባሕር ጠረፍ ኢትዮጵያን ቅኝ አገር ለማድረግ የሚመጡት የኢጣልያ የሲቪልና የጦር ሹማምንት ከንቀት የተነሣ ፣ በቀላሉ ያፄ ምኒልክን ጦር አሸንፈው ለኢጣልያ ቅኝ አገር አውርሰው በመመለስ የሹመት ደረጃና ኒሻን ለመሸለም ዋና ጉጉት አላቸው ። ወዳጄ ምኒልክ ለእርቅ እያስመሰለ ይመላለስ የነበረው ማዦር ቶማሶ ሳልሳ የሚባለው ፣ "ቁጥሩ ትንሽ የሆነው ወታደራችን ብዙውን የጠላትን ኃይል ለማሸነፍ መቻሉ አጠራጣሪ አይደለም . . ." በማለት እርግጠኛ ሆኗል ።[1]

ራሱ ጠቅላይ አዝማቹ ባራቲዬሪ ፣ ቀደም ሲል ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለባሮን ብላን ባስተላለፈው መልእክት ፣ "ጄኔራል ናፒዬሪ ቴዎድሮስን ለማሸነፍ ከፈጀበት የወታደሮች ቁጥርና ጊዜ ባነሰ በምኒልክ ጦር ላይ ድል አድራጊነትን እቀዳጃለሁ" ብሎ ደንፍቶ ነበር ።[2] ከዚህም አያይዞ ከኢትዮጵያ ጦር አንጻር የኢጣልያን ተዋጊ ጦር በፖለቲካ መብሰሉን በወታደራዊ ሥነ ሥርዓት የሠለጠነ መሆኑን በመገምገም ለድል አድራጊነቱ አልተጠራጠረም ።

ሌላው ጄኔራል ማቲዎ አልበርቶኒ የሚባለው ፣ በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ አጠገቡ ያሉት ደጃዝማች ፋንታ የሚባሉት የባንዳ ሹም ፣ በዚህ ጦርነት ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ቢመክሩት ፣ "አበሾች

---

1 Il Generale Tomaso Salsa, E. Canevarie. G. Comisso, PP. 268 -269.

2 Gli Italiani in Africa .. Del Boca, P. 560.

ገና ሲያዩን ነው የሚሸሹት'' ሲል መለሰላቸው ። የርሱም ጓደኛ ጄኔራል አሪሞንዲ ዡሴፔ ጄኔራል ባራቲዬሪ በመጨረሻ በቶሎ ጦርነቱን ላለመጀመር የሚያደርገውን ጥንቃቄ በመንቀፍ ምክንያት እያበዛ ነገ ተነገ ወዲያ እያለ ጊዜ በማራዘሙ እየተበሳጨ ፣ "አሁን ጠላትን ልቡ እስኪጠፋ እያደኑ ማባረር ነው'' ያለውን አንጀሉ ደልቦካ መዝግቦት ይገኛል ።[1]

ከነዚህ የበለጠ ደግሞ ፣ የነዚህ ጄኔራሎች ጓደኛ ጄኔራል ቪቶሪዮ ኢማኑኤል ዳቦርሚዳ ባንድ ወገን ካፄ ምኒልክ ሠፈር በዘዴ አታሎ የኢጣልያን ጦር ከምሽጉ ለማስወጣት የተነዛውን ሐሰተኛ ወሬ በመተማመን ፣ ወዲያውም እንደ ጓደኞቹ ጄኔራሎች የኢትዮጵያን ጦር በመናቅ ፣ የኢትዮጵያን የወታደር ድርጅት በቀላሉ አፈራርሶ የአላጌውንና የመቀሌውን የውርደት ብድር ለመመለስና በክብርና በድል አድራጊነት ወደ አገሩ ለመመለስ እርግጠኛ እንደነበረ ከዓድዋ ጦርነት ከሐያ ቀን በፊት ወደ ኢጣልያ አገር ለባለቤቱ የጻፈው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ደብዳቤ ያስረዳል ።

እንትጮ የካቲት 10 ቀን 1896 (የካቲት 3/1888) የልጆቻችንን ደብዳቤዎች ተቀበልሁ ። ግልጽ በሆነው ፍቅራቸው ልቤ ተነክቷል ። ካንድ ወር በኋላ የምንመለስ(ወዳገራችን) አይመስለኝም ። በአፍሪካ ነገሩ ሁሉ እየተጐተተ መርዘም አለበት ። ጠላት ወደፊት ከገፋ በኋላ ወደኋላ መለስ ብሏል ። * እኛም ከአለንበት ከአዲግራት ወደእንትጮ እልፍ ብለናል ። ከአለንበት ስድስት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ የጠላት ጦር ይታያል ። የቀረው ወደኋላ ያለው በጋራ ተሸፍኗል ። እኔ እንደማስበው በድንገት አደጋ ጥለን ብንወጋው የሚሸሽና በትንሽ ወታደሮች መሥዋዕትነት ከፍ ያለ ፍሬ (የድል) የሚገኝ ይመስለኛል ።

የኛ ወታደሮች ፣ የውጊያ አምሮት እያላቸው እነዚያ (ሐበሾቹ) ግን ፣ ሰላዮቻችን እንደሚሉት ወደቤታቸው መመለስን እንጂ ፣ በጦርነቱ እምነት የላቸውም ። ነገር ግን የዕርቅ ድርድር ተይዟል ። ** እኔ ለዕርቁ ፍሬነት እምነት የለኝም ። ንጉሡ (ምኒልክ) በረዥሙ ጦርነቱን አዘጋጅቶ 80,000 ወታደር ከአሰከተተና የግዛቱን ሀብት ከፈጀ በኋላ ምንም እንኳን ክብሩ የኛ ቢሆን ፣ በአምባ አላጌና በመቀሌ ከቀናው በኋላ እኛ የምናቀርበውን ውል ተቀብሎ ወደቤቱ ለመመለስ ይችል ይሆን ። ኢጣልያስ ብትሆን ከነርሱ የተሻለ በዓለም የማይገኘውን 20,000 የጦር ወታደሮቿን ወደዚህ በመላክ ከፍ ያለ መሥዋዕት ከአደረገች ወዲህ ከአንድ አረመኔ ሕዝብ የሚቀርብላትን የውል አሳብ መቀበል ትዋረዳለችን? የዕርቁ ድርድር ጉዳይ እየተራዘመ ሲሔድ

1 Gli Itallani in Africa . . ,, PP. 640 -642.

* መረብን አልፎ ለመዝመት ታስቦ በወሃ እጦት የቀረውን ለማስታወስ ይመስላል ።

** ማገር ሳልሳ ከነራስ መኰንን ጋር ያደረገውን መጥቀሱ ነው ።



የጠላትን ሁኔታ እያባሰበት ይሔዳል እንጂ ፣ ቢሆንም ለኛ አዋራጅ ዕርቅ ሊደርስብን አይችልም ። እኔ ግን ጠላት ወደኋላ የተመለሰ እንደሆነ ያጋጠመኝን መልካም ዕድል አጣለሁ* ምክንያቱም ወደኋላ ሲያፈገፍግ ኃይላችንን ይዘን እርሱን እየተከታተልን ፈልገን ለመውጋት የስንቁ ነገር (ችግሩ) ይከለክለናል ። 1

ይኸው ለውጊያና ለዝርብዱ በዚህም ለመሾምና ለመሸለም ጉጉት ያደረበት ጄኔራል ፣ ከዚያ ወዲህ የዓድዋ ጦርነት ሲደረግ ስምንት ቀን ሲቀረው በጻፈው ሌላ ደብዳቤ ላይ ፤

የኔ ፊና አትፍሪ ። እዚህ ያለጥንቃቄ የሚሆን ነገር የለም ። ሁለቱም ባላጋራዎች በጣም ጠንቃቃ ሆነዋል ። . . . በግልጽ ሜዳ በገሃድ መዋጋት አይፈልጉም . . . አበሾች መዋጋት ወይም መመለስ እንዳለባቸው በኛ በኩል የታመነ ነው ። ምክንያቱም ጠላት 80,000 ተዋጊ ጦር ሲኖረው ከሴትና ከልጅ ጋር በድምሩ 150,000 ተቀላቢ ስለሆነ እነዚህን ለመቀለብ ያለበት አገር እህሉ ስላለቀ አይችልም ። ከምሽጋችን መጥቶ ለመውጋት አይደፍረንም ። ስለዚህ በመጭው ጊዜ ወደኋላው ይመለሳል ብለን እንጠባበቃለን ። በዚያን ጊዜ በትግሬ የፈቀደንን ለማድረግ እንችላለን ። ተመልሰው ተዘጋጅተው ለመምጣት ብዙ ዓመት ይፈጅባቸዋል ። ዋናው ከሐበሻ አገር ተዋጊ የሆነው የትግሬ ሕዝብ ከኛ ጋር ስለሚሆን ምንም ማድረግ አይችልም ። . . . መቼም ባለፈው ከደረሰው አድራጐት ያላጌና የመቀሌ ውድቀት በኋላ ዕርቅ ማድረጉ ለኛ አዋራጅ ነው ። . . . ከኢጣልያ አገር የጦሩ እርዳታ ከደረሰ በኋላ ባራቲዬሪ ጉልበቱን ተማምኖ ውጊያ የጀመረ እንደሆነ መፍትሔው በመጋቢት ላይ ይለያል ። ** ስለዚህ ወደ ኢጣልያ አገር መመለሳችን በበጋው ነው ማለት ነው . . . ትናንት የሁለት ባታዮ ጦሬን ይዤ ለምርመራ በወጣሁ ጊዜ በወታደሮቻችን ፊት ላይ ይታይ የነበረው ደስታ ይገርምሻል ። ሁሉም ወደፊት ገሥግሠው መታኮስ ይፈልጋሉ ። 2

በነዚህ ሁለት ደብዳቤዎች ፣ ይህ የኢጣልያ ጄኔራል የራሱን ወታደሮች "በዓለም የማይገኙትን'' ሲል ካገሩ ያልወጣ ወይም በንባብ ያልበሰለ ፣ ዓለምን የማያውቅ በዓለም ያሉትን የጀርመንን ፣ የጃፓንን ፣ የቱርክን የሌሎችንም አገሮች ወታደሮች ዝግጁነት የማያውቅ በሞኝነት የራሱን ወገን ብቻ የሚያጋንን የዋህ ጄኔራል መሆኑን ያሳያል ። በዚህም ላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ አረመኔ የሚል ሥያሜ አስታቅፎታል ። አረመኔ በራሱ ግዛት ሳይቆጠብ የሌላውን አገር ካልገዛሁ

* ተዋግቶ ዝግጁነትን አሳይቶ የመሾም ፣ የመሸለም ዕድል ማለት ነው ።

1 Lettere e Diari . . . ,F Lemmi, PP. 82-83.

** እውነትም የዓድዋ ጦርነት የተደረገው እ.ኤ.አ. መጋቢት 1 ቀን ስለሆነ ትንቢቱ ይዞለታል ።

2 Lettere e Diari . . ,,F. Lemmi, PP.83-84

ብሎ የንጹሐኑን ደም የሚያፈስ ነው ወይስ የራሱን ነጻነት የሚከ
ላከል ? በመቀሌ ተከበው በወሃ ጥምና በረኃብ ሊያልቁ የነበሩትን ሸኝ
ስጥቶ በነጻ መልቀቅ የጠላቱን ሬሳ እስነሥቶ በደንበኛ ቦታ ማስቀ
በር ፡ ይኸ ሁሉ ያረመኔ ሥራ አልነበረም ። ዳሩ ግን ፡ ይኸን ሁሉ የጦሩ
አለቆችና የፖለቲካ ባለሥልጣኖቹ ከፍርሃት ቆጥረውታል ።

ዳቦርሚዳ ፡ እሽናፊነቱን መቶ በመቶ በማመን ፡ "ጠላት ወደኋላ
የሸሸ እንደሆነ ለመከታተል ስንቅ ስለሚቸግረን ፡ ያጋጠመኝን ዕድል
እጣለሁ . . .እንደዚሁም ከእገሬ ለውጊያ መጥቼ ጠላት የሸሸ እንደሆነ
እሸንፌ በዚሁ የማገኘው ክብርና ዝና ይቀርብኛል . . . ጠላት ስንቅ
አልቆበት ወደቤቱ (አዲስ አበባ) ሲመለስ ፡ በመላው ትግሬ የፈቀድ
ነውን እናደርጋለን" ሲል ፡ በእርግጥ ኢትዮጵያ በዚህ ጊዜ ያላትን
ድርጅት የማያውቅ ካለፉት ከአላጌና ከመቀሌ የውጊያ ውጤቶች
ለመማር ያልፈለገ በጠቅላላው አመዛዛኝ አእምሮ የሌለው ሞኝነ
ትና ግትርነት ያጠቃው ተራ የጦር አለቃ ነው ማለት ይቻላል ።

በዚህ ላይ ደግሞ ፡ ጦርነቱ ይቅርብን የሚል ሕዝባዊ ድምፅ እንዳ
ይቀሰቀስ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሮማም አሥመራና ምጥዋም ያሉት
የሲቪልና የጦር ሹማምንቶች በኢትዮጵያ ያለውን ደንበኛ የመከላ
ከያ ሁኔታ እየደበቁ በአምባላጌና በመቀሌ የደረሰውንም እያወላገዱ
በከንቱ የኢትዮጵያን የመከላከል ሁኔታ እያራከሱ ፡ የነርሱን ጀብዱ
እያጋነኑ በመጻፍ፡ ሐቀኛውንም ጋዜጣ ጸሐፊ እያባረሩ ፡ ብዙውን
ሁኔታ ከተዋጊው ወታደርና ጄኔራል ለመደበቅ መሞከራቸው
ግልጽ ነው ።

በጠቅላላ ፡ ኢጣልያኖቹን በጄኔራሎቻቸው መልክና ጠባይ ልን
ወስዳቸው እንችልም ። በመካከላቸው በኢጣልያ አገርና በሮማ ታላ
ላቅ አስተዋዮች ፡ ብልሆች ሞራል ያላቸው ደግነትም ርኅራኄም የሞላ
ባቸው ይገኛሉ ። በዚህ ምክንያት ፡ በምክር ቤት ውስጥ ሳይቀር ክሪስ
ፒና ወገኖቹ ኢትዮጵያውያን አረመኔዎች ናቸው ፡ እየገዛን ልናሠለጥ
ናቸው ይገባል እያሉ ሲደነፉ ፡ ሌሎች በተለይ የግራ ክፍሎች
እስከዛሬ በነጻነት የቆየችውን አገር በኃይል ወርሮ በቅኝ እገዛዝ
ልያዝ ማለት ወንጀልም እብደትም ነው እያሉ ሽንጣቸውን ገት
ረው የሚሟገቱ ሞልተዋል ። ከነዚህም ውስጥ ኮስታ እንድሬያ
ይገኛል ። ይኸም አማካሪ በአምባላጌ ለወደቁት የክብር ሰላምታ ይሰጥ
በተባለበት ጊዜ ፡ "በፖለቲካ ብልሹነት ያላግባብ ለወደቁት ኢጣል
ያኖች ክብር ከመስጠቴ ጋር ያገራቸውን ነጻነት ሲከላከሉ ለወደቁት
አበሾችና የሸዋ ተወላጆች የክብር ሰላምታ መስጠት ይገባል" በማለቱ



በምክር ቤቱ እጭር ሁካታ ተፈጥሮ ነበር ። ከርሱም ጋር ይኸን በመ
ሰለው እሳብ የተባበሩትን ኢምብሪያኒ ማቴዎ ፡ ኡሊስ ባርቢዬሪ ፡ ገብ
ርኤል ሮዛ ፡ ናፖሊዎን ኮላጅያኒ የሚባሉትን ስማቸውን መጥቀስ
ተገቢ ይመስለኛል ።[1]

1 Gli Italiani in Africa . . PP. 287 - 289; La Prima Guerra D' Africa, R. Battaglia, PP. 242 - 258.

# ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

## የመጨረሻው የኢጣሊያኖች ተስፋ ልጅ ጉግሣ ዳርጌ

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ የኢትዮጵያን መሳፍንትና መኳንንት ፣ ሹማምንቱንም፣ ባላባቱንም ጠቅላላውን ተዋጊ ጦር በክተት ዐዋጅ ቀስቅሰው ለዚህ ጦርነት ከአዲስ አበባ ከተነሡ ዠምሮ ከአላጌ እስከ መቀሌ ከድል ወደ ድል እየተራመዱ ፣ እንደልቡ ፈንጭቶ እስከ አምባላጌ የደረሰውን የኢጣልያን ጦር እየጠረጉ ወደ ዓድዋ አካባቢ ነድተውታል ። ወደ ኢጣልያኖች በውድም ፣ በግድም ተጠግቶ የወረራ መሣሪያ የሆነውን ኢትዮጵያዊ መልሰው ለእናት አገሩ እንዲሰለፍ ለማድረግ በዓዋጅና በመልክት እየጋበዙ አስገብተውታል ። በሌላውም ረገድ ኢትዮጵያ ካሳለፈችው የጦርነትና የዕልቂት ዘመን ዐርፋ ሰላምና ጸጥታ እንድታገኝ ለጣልያኖቹ ባለሥልጣኖች የሰላም እጃቸውን ከመዘርጋት ሳያቋርጡ ፣ በማናቸውም ረገድ በሚያደርጉት ፖለቲካዊና ወታደራዊ ተግባር እነሱ ቢያምኑም ፣ ቢክዱም የኢጣልያን ጕራ እያዳከሙበት ሔደዋል ። ሰላምን የሚፈልጉት ከኃይል ተጽዕኖ ጋር ጦርነቱንም የሚቀጥሉት የሰላምን መንገድ በመከተል ስለሆነ ፣ ኢጣልያኖቹ ከጥቁር ሕዝብ እንደዚህ ያለ ያልጠበቁት ከፉ ጠመዝማዛ የፖለቲካና የጦርነት መዘዝ ገጥሟቸዋል ። የተማመኑባቸው ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስ ተፈሪ ፣ ኢጣልያንን ከድተው ወዳፄ ምኒልክ መደረብ ፣ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደምናነበው ፣ በአውሳ የመሐመድ አንፋሪ በነአዛዥ ወልደ ጻድቅ ተመትቶ መሸነፍ ፣ የመሳፍንቱ በምኒልክ የሥልጣን ጥላ ሥር ተባብሮ ለጦርነት ባንድ እግር መቆም ፣ ለኢጣልያ የተደጋገመ ታላቅ በትርና የራስ ምታት ሆነባት ።

ነገር ግን ፣ ከመሐመድ አንፋሪ ከዳት በቀር ገንዘቡም ፣ ስጦታውም ተበትኖ ፣ የወዳጅነት ስብከቱና ማስፈራራቱም በየወቅቱ ተፈራርቆ ለከዳት የሚነቃነቅ መስፍን ባገር ውስጥ ስለጠፋ ፣ ለምኒልክ የዙፋን ባላንጣ ሆኖ ራሱ ከድቶ ሌሎቹን የሚያስከዳ ቢቸግራቸው ከውጭ አገር ይፈላለጉ ዠመር ። በዚህ ምክንያት ፣ ቀደም አድርገው ዐፄ ምኒልክ አገልጋያቸው በነበረው በስዊሱ ተወላጅ በእንጂነር አልፍሬድ ኢልግ አማካይነት የራስ ዳርጌን ልጅ ጉግሣን ከከተማና ከአፈ ወርቅ (በኋላ ነጋድራስ አፈወርቅ) ጋር ለትምህርት ወደ ስዊስ አገር ልከዋቸው ፣ ሦስቱም ወጣቶች በስዊስ አገር በኔሻተል ኮሌጅ ይማሩ ነበር ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላን ካርሎ አልቤርቶ የሚያደርጉት ቢያጡ ፥ "ጉግሣ የራስ ዳርጌ ልጅ ስለሆነ ዳርጌም የሣህለ ሥላሴ ልጅ በመሆናቸው ፥ እንደ ምኒልክ ለዙፋኑ ቀራቢ ስለሆኑ ጉግሣን በማባበልም ፥ በማስገደድም ከኔቸተል ኮሌጅ እናጥለን ወደ ዠኔራል ባራቲዬሪ ብንልከው ፥ ዤኔራሉ ይኸን ይዞ ከምኒልክ ብዙ ሰው ለማስከዳት ይችላል" የሚል የሚያሳፍርና ወራዳ የሆነ ከንቱ ተስፋ አደረባቸው ።

ስለዚህ ፥ ጉግሣን ከጓደኞቹ ከከተማና ከአፈወርቅ ጋር (ምናልባት ኢጣልያንኛ በሚያውቀው በአፈወርቅ በኩል) አባብለው ወደ ኢጣልያ ጠረፍ ጠጋ ሲል እ. ኤ. አ. በታኅሣሥ ወር በ1895 ዓ.ም. በግዴታ ይዘው ወደ ሮማ ለማምጣት እንደ ወሰኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላን ለዤኔራል ባራቲዬሪ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቴሌግራም አስተላለፉለት ።

የሐበሻው መስፍን ጉግሣ በታኅሣሥ ወር በመጀመሪያዎቹ ቀናት ሮማ ይገባል ። ክቡርነትዎ መስፍኑን በምኒልክ ላይ መሣሪያ አድርጎ ለመጠቀም ይመኙ እንደሆነ አባብለን (እግባብተን) ወደ ምጥዋ ልከን በሥልጣንዎ ሥር እንዲሆን እናደርጋለን ።

ዤኔራሉ አሳቡን ከተቀበለው በኋላ ፥ ጉግሣንና ጓደኞቹን ከስዊስ ነጥቀው ወደ ሮማ አስመጧቸው ። ንጥቂያው ማባበልና ማጭበርበር አለበት ። ከዚህ በኋላ ሮማ ምንም ያህል ውለው ሳያድሩ ፥ በመርከብ ወደ ምጥዋ ተልከው እንደ ደረሱ ፥ ከዚያ በእንክብካቤ ዤኔራሉ ወዳለበት ወደ እዳጋ ሐሙስ አደረሱት ። ዤኔራሉም ከአንገት በላይ የሆነ አክብሮት እያሳየ ጉግሣን አነጋገረው ። ሌሎቹም ሹማምንቶች አክብሮት እንዲያሳዩት አደረገ ።

በዚህ ጊዜ ፥ ይኸን የመንግሥ አምሮት የሌለውን ወጣትና ዐይን አፋር ተማሪ ፥ ከስዊስ አገር አታለውና አስገድደው ወደ ሮማ ፥ ከሮማ ወደ እዳጋ ሐሙስ መላካቸውን የሰማና ፥ "ከምኒልክ ብዙ መሳፍንት ያስከዳልናል" በሚሉ ምኞት ልባዊ ያልሆነ የማታለል አክብሮት ማድረጋቸውን የተመለከተ ሁሉ ሣቀባቸው ። መስፍኑ ጉግሣም ካፄ ምኒልክ ሠፈር አንድም ሰው ሊያነቃንቅላቸው አልቻለም ። ተስፋ ሲቆርጡ አክባብረው ፥ እንክባክበው የመሣሪያነቱ ጉዳይ ስለሳተ አመናጭቀው ወደ ነበረበት ወደ ስዊስ መለሱት ።

ራሱ ዤኔራል ባራቲዬሪ ፥ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ በግዞት አገሩ ገብቶ በዕረፍቱ ጊዜ በጻፈው መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ ያሠፈረውን ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።



. . . ከሮማ ወደ ሠፈራችን ስለ ተላከው የሸዋ መስፍን ትንሽ እናገራለሁ ። . . .የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ባሮን ብላን ኢትዮጵያዊው መስፍን ጉግሣ ሊጠቅም ይችላልን ብሎ በቴሌግራም ጠየቀኝ ። ይህ መስፍን የራስ ዳርጌ ልጅ ሲሆን ፥ ለንጉሠ ነገሥቱ ለምኒልክ ያጎት ልጅ ነው ። . . . ስለዚህ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለጠየቀኝ አወን ብዬ መለስሁ ። ስለዚህ ጉግሣ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር ምጥዋ ከዚያም አዲግራት ደረሰ ። ለርሱና ለጓደኞቹ ማናቸውም አክብሮትና እስተያየት ተደረገላቸው ። በእዳጋ ሐሙስ ሠፈር ድንኳናቸው በዋናው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ድንኳን አጠገብ ተተከለላቸው ። ነገር ግን ፥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመጠቀም የሠነዘረው ዓላማ ከመጠን ያለፈና የሳተ ነገር መሆኑ እርግጠኛ ነበር ።

መስፍኑ ጉግሣ ፥ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የምኒልክ ያጎት ልጅ በመሆኑ በሸዋ ሠፈር ምንም የመታወቅና የመሰማት ክብር ሊኖረው አልቻለም ። በመከበር ፈንታ እንዲያውም ከሸዋ በመራቁና ያውሮፓን ሥልጣኔና ልማድ በመውሰዱ ምናልባት ሳይናቅ አይቀርም ። እርሱም ትንሽ ወጣት የተዋጊነት መንፈሱ ያነሰ ፥ ግለኛ ፥ ዝምተኛ ፥ ሁኔታውና መንፈሱ የቀዘቀዘ ፥ በጣልያኖቹ ሠፈር በመገኘቱ የደነገጠና የበረገገ ነበር ። የሱ ጸሐፊ በኑሮው አውሮፓዊ የሆነ የጣና ሐይቅ ተወላጅ (አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ) ስለ ራሱም ስለ መስፍኑም ሲናገር ፥ ጣሊያኖችን እንደሚወዱና ለማገልገል ፈቃደኞች መሆናቸውን ደጋግሞ ይናገር ነበር ።* ነገር ግን ፥ በእዳጋ ሐሙስ በጥር ወር መጨረሻ ጉግሣ ሊስባቸው የሚችለው በንጉሠ ነገሥቱ ጦር ሠፈር ያሉት ወዳጆቹ እነማን መሆናቸውን ለማወቅ ተፈልጎ ቢጠየቅ ትንሽ አወላውሎ አንዳንድ ስም ሰጠ ። ላለመጻፍና ራሱን ላለመግለጽ እንደ ሐበሻ ልማድ ምክንያት እየፈጠረ ጊዜ ያራዝም ዠመር ። . . . በማናቸውም ረገድ በጠላታችን ሠፈር መካከል ሆኖ ጠብና ልዩነት ለመፍጠር ከዐይን አፋሩ ከጉግሣ ሌላ ማናቸውም ዓይነት ሹም . . . ሊጠቅመን በቻለ ነበር ። . . .ጉግሣም ምንም እንኳን ለሐበሻ መስፍንነቱ የሚገባውን ክብር ብናደርግለት ፥ እርሱ ግን ሐበሾቹን በማየት እዳጋ እንዳይደርስበት ማናቸውንም ምክንያት እየፈጠረ ከእዳጋ ሐሙስ ወደ አዲግራት ከዚያም ወደ ምጥዋ ተመለሰ ። 1

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከባራቲዬሪ ጋር ውስጡን ተመሣጥረው ጉግሣን ከስዊስ ወደ ሮማ ከዚያም ወደ ምጥዋ ለመላክ በሚዘጋጁበት ሰዓት የኢትዮጵያን መሳፍንት ለመከፋፈል የተመደቡት ፥ በኢትዮጵያ የነበሩትና በኋላ በጦርነቱ ዋዜማ ካገር እንዲወጡ የተደረጉት ፥ እነቺዛሬ ኔራሲኒ ምንም ካገር ቢወጡ

---

* በዚህ የባራቲዬሪ ማስታወሻ ላይ አፈወርቅ ገብረየሱስ ከሰባት ዓመታት በፊት የውጫሌን ፥ ውል ኪጋዜጣ ላይ አንብቤ አደገኛ መሆኑን ለደጃች መኰንን ገለጽሁላቸው ሲሉ አሁን በዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ምን ለወጣቸው ገንዘብ ወይስ ኃይል! አይታወቅም።

1 Memoire d' Afrique, Gen. Baratieri, PP. 354 - 355. I Russi In Etiopia, 2vol. Carlo Zaghi, P. 245

በጐን ወደ የመሳፍንቱ እየተላላኩ ለማሸፈት ያላቸውን ምኞት በፍጹም ተስፋ ቆርጠው አልተውቱም ።

ከዚህ በፊት ፣ በሐረርና በአካባቢው ራስ መኰንንን እንግሥ ከምኒልክ ለመለየት ፈትኖ ያልተሳካለት ሐኪሙ ቼዛሬ ኔራሲኒ የኢጣልያ መንግሥት በምኒልክ ፈንታ ጉግሣን ደጋግፎ ለማንገሥ ያለውን ዓላማ አባትየው ራስ ዳርጌ ዐውቀው ተደስተው በጉዳዩ እንዲተባበሩ ደብዳቤ ልኮላቸው ኖሯል ። ደብዳቤውን የላከው ከኤደን መሆን አለበት ። የርሱ ደብዳቤ ከሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት ተፈልጎ ሊገኝ አልቻልም ። የራስ ዳርጌ መልስ ግን ፣ ቃሉ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

> የተላከ ከራስ ዳርጌ ይድረስ ከሐኪም ኔራዚኒ እንዴት አለህ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። ወረቀትህም ደረሰልኝ ። እኔ ከዚህ ቀደም አላውቅህም ነበር ። አሁን በወረቀትህ ነው ማወቄ ። ከዚህ ቀደም ይህን ያህል ቀን ሳላውቅህ መቅረቴ ምንኛ ተጐድቻለሁ ። አሁንም የልጄን የልጅ ጉግሣን ነገር ወደ ኢጣልያኖች መግባቱን የሳከህብኝን ሰማሁ ። ይኸማ ከሆነ መልካም ነው እንጂ ምንነገር አለ ። ያጤ ምኒልክን አልጋ መቀበል ነው እንጂ ። እኔም አባቱ አዲስ አበባን አልጋውን ይዤ ተቀምጫለሁ ። ምን የሚቸግር ነገር አለ ። ዳሩ ግን ፣ ያንተ ደብዳቤ ብቻ ነው እንጂ የመጣው የሌላ ደብዳቤ አልመጣም ። ይህ ነገር እሰት ውሸት የሆነ እንደሆነ አንተንም ኔራዚኒ የተባልከውን ናዚራ እባብ ባለ መርዝ ያስመስልሃል ። ኢጣልያኖችንም ጉልበት ቢያንሳቸው የሐበሻን ጉልበት የፈሩ ያስመስላቸዋል ። ያንተንም ሐኪምነት የመልካም ፣ የደግ የነበርከውን የውሸትና የቅጥፈት ሐኪም ያስመስልህ ይመስላል ። ዳሩ ግን ፣ ሐሰቱንም እውነቱንም የሚያውቅ መለኮት (አምላክ) ይመልከት ። በጥር በ1 ቀን ተጻፈ ባዲስ አበባ ከተማ በ1ወ88ወ8 1888 ዓመተ ምሕረት (ዝ ማኅተም ዘእራስ ዳርጌ ርእሰ መኳንንት)

ራስ ዳርጌ ፣ ያፄ ምኒልክ አጐት ብቻ ሳይሆኑ ሁለቱ ከልብ እንደ አባትና እንደ ልጅ የሚተማመኑ ናቸው ። ኔራሲኒ ጉግሣን ለማስከዳትና በርሱና ብርሳቸው ለመጠቀም ያቀደው አሳብ በጣም ገርሟቸው በስጡት መልስ ፣ “ ናዚራ እባብ ባለመርዝ ፣ ውሸታምና ቀጣፊ ሐኪም ” እያሉ በመሳደብና በማፌዝ ቀልደውበታል ።

የምኒልክና የጣይቱ ጠንካራና የደረጀ መንግሥት ፣ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም የሆነ የተሻለ አስተዳደር በማሳየት ፣ ሁሉን እንደ ልማዱ በመያዝ በትዕግሥት ፣ በሰላም ፣ በቸርነትና በመልካም ሁኔታ ላይ ስለ ተመሠረተ ፣ በዚህም በሌላውም ጊዜ ቢሆን እንኳን ሕዝብ የማያውቀው ተማሪው ጉግሣ ቀርቶ ራሳቸው ትልቁና የተከበሩት አባቱ ራስ ዳርጌ ቢከዱና ወደ ኢጣልያ ቢዞሩ ፣ የምኒልክን መንግሥት የጠነከረ አቅዋምና የጦርነቱን ጐራ እምብዛም ሊያናጉት የሚችሉ አይመስልም ።



# ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

## የአውሳ ጦርነትና—የመሐመድ አንፋሪ መሸነፍ

የኢጣልያ ሰላዮች ፣ በኢትዮጵያ በየአውራጃው ተሠራጭተው የየአካባቢው መሳፍንትና ባላባት ከንጉሠ ነገሥቱ ከዐፄ ምኒልክ እየሸፈቱ እንዲለዩ በስጦታም ፣ በማባበልም የሚያደርጉትን ጥረት በመቀጠል ወደ አውሳው ባላባት ወደ መሐመድ አንፋሪ ለስብከትና ካፄ ምኒልክ ለመለየት የተላከው ካፒቴን ሳልቫቶሬ ፔርሲኮ መሆኑን እመልከተናል ።

የአውሳ ባላባቶች ምንም እንኳን አካባቢያቸው ለተወሰነ ጊዜ የቱርኮችና የግብጾች ተጽዕኖ ቢደረግበትም ፣ ቱርኮችና ግብጾች ከተባረሩ ወዲህ እንደገና ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴና ከሌሎች የሸዋ መሳፍንት ጋር ግንኙነታቸውን አጽንተው ይኖሩ ነበር ። በዚሁ መሠረት የአውሳው ባላባት መሐመድ አንፋሪ ለንጉሥ ምኒልክ ታዛዥም ፣ ወዳጅም ሆኖ ከአውሮፓ ፣ ከፈረንሳይም ከኢጣልያኖችም ፣ በአሰብ በኩል ለንጉሥ ምኒልክ የሚመጣውን የጦር መሣሪያና ዕቃ እየተቀበለ ወይም ለሚያደርሱት ሸኚ እየሰጠ ፣ ወደ አንኮበር ለአዛዥ ወልደ ጻድቅ በመላክ መልካም ግንኙነቱን ጠብቆ ይኖር ነበር ። ሙንሲንጀር ባሻ የሚባለው በአውሳ በኩል ባፄ ዮሐንስ ላይ የጦር ግንባር ለመክፈት እንደ እ.ኤ.አ. 1875 ዓ.ም. ሲተላለፍ ፣ የአንፋሪ ሰዎች በገደሉት ጊዜ ያስገፈፈውን አንዳንድ የጦር መሣሪያና ዕቃ ወደ ንጉሥ ምኒልክ በመላክ በማናቸውም ረገድ ታማኝነቱን እስከዚህ ድረስ አላጐደለም ነበር ።[1]

ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ ወዲህ ፣ በመጀመሪያው ጊዜ ይኸው መልካም ግንኙነት አላቋረጠም ነበር ። ነገር ግን ፣ ባለፈው እንዳነበብነው በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ የተነሣ በንጉሠ ነገሥቱና በኢጣልያ መንግሥት መካከል ያለው ጠብ እየተባባሰ ሲሔድ እነኮንት እንቶኔሊ በአውሳ በኩል በሚተላለፉበት ጊዜ ከመሐመድ አንፋሪና ከእማቹም ከአብዱራህማን ጋር መሣሪያና ሌሎች ስጦታዎችም በማድረግ ተወዳጁ ። እደያር ሁለቱንም ከንጉሠ ነገሥቱ ሊለዩዋቸው ቻሉ ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 232

በመጨረሻ መሐመድ አንፉሪና አማቹ አብዱራህማን ፣ የኢጣልያን ወዳጅነትና የበላይ ጠባቂነት ሁለቱም እንዲቀበሉ በመገፋፋት ያገሩንና የሕዝቡን ሁኔታ በቅርብ ሆኖ እንዲያጠናና ወታደርም እየመለመለ እንዲያዘጋጅ ከዚህ በፊት በአላጌው ጦርነት ሰዓት ስሙን የጠቀስነው ይኸው ካፒታኖ ሳልቫቶሬ ፔርሲኮ በ1886 ዓ. ም. ወደ አውሳ መሐመድ አንፉሪ ዘንድ በነዋሪ ተቀማጭነት ተላከ ። ይኸው የኢጣልያ መኰንን የዐረብኛ ቋንቋና የእስልምንና ባህል ዐውቃለሁ ባይ ስለሆነ ፣ ለማለያየቱ ተግባር ምርጫው እርሱ ላይ ወደቀ ።

ገኔራል ባራቲዬሪ ፣ ይኸንኑ መኰንን በ1886 ዓ.ም. ወደ አውሳ ሲልከው በጽሑፍ ያሳሰበው ዋና ዋናው ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

የምሰጥህ ዝርዝር ትእዛዝ የለኝም ። እንዲያውም የሥራህን ነጻነት እንዳላጠብ ትእዛዝ ከመስጠት መራቅን እመርጣለሁ ። ነገር ግን የመልእክትህ ዋና ፍሬ ነገር የኢጣልያንን የበላይ ጠባቂነት የኤርትራን ቅኝ አገር ታላቅነት እየገለጽህ መሐመድ አንፈሪንና አውሳን ወደኛ ለመሳብና ለመያዝ ነው ። ይኸንንም ከዚህ ቀደም በጽሕፈትም ፣ በቃልም አደራዬን እንደ ገለጽሁልህ በጥበብና በትዕግሥት የነሱን አሳብና ልማድ በመፈጸምና ከነርሱ ጋር በማናቸውም እየተመሳሰልህ ነው. . . ስለ ምኒልክ ሲነሣ ይህ ንጉሥ በኢጣልያ የበላይ ጠባቂነት ውስጥ መኖሩንና መልካም ግንኙነት ያለን መሆናችንን እንደሚረዳ ግለጽለት ።

መሐመድ አንፈሪ ፣ እሺ የሚል እንደሆነ የባንዳ ወታደር ለመመልመል አስብበት . . . በሐረር በኩል ሳያልፍ ያበሻ መንግሥት መገናኛውን በኛ በኩል እንዲያደርግ የአሰብ መንገድ በግድ የኛ መሆን አለበት . . . ከአዋሽ በላይ ያሉ የጋላ አገሮች ከወሎ ጋር የሚገናኙበትንና ለጦርነት የሚመቸውን ፍሬያማና ጠንካራ ቦታ መርምረህ እጥና ። ትራቬርሲ ዘወትር መልካም ነው እያለ ስለሚመካበት ስለ አዳሌ ጉቦ ስለ ጋምቦ ትንሽ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ ። እንደዚሁም ፈረንሳዮች የሚያደርጉትን ለማወቅ ተጣጣር ።. . . ለዚህም ሁሉ ሥራህ አብዱራህማን ይረዳሃል ። እርሱም ብልህ ነው ማናቸውንም ተስፋ የሚያደርገው ከኛ ነው ። ብዙ ነገር መጠየቅና ብዙ ነገር ያስፈልገኛል ማለት ይወዳል ። አንተም ይኸን ሲልህ ፣ መልእክቱ ሁሉ በመልካም ሲፈጸም ሁሉንም ታገኛለህ እያልህ የተለመደውን የብልህት መልስ ስጠው ።

የሚወድህ ኦ. ባራቲዬሪ

ከረን 4/1894

እንደዚሁም ከካፒቴን ፔርሲኮ ጋር ቴኔንቴ ካርሎ ጂያኒኒ የሚባል ተላከና ሁለቱም አሰብ ከሚገኙ የኢጣልያ ኮሚሳሮች ከነፒስታሎዛ



እየተመካከሩ መሐመድ አንፉሪንና ልጆቹን እነመሐመድ አይደስን ፣ እነአንፈሪን ፣ መሣሪያም ፣ ልዩ ልዩ ስጦታም እየሰጡ በልዩ ልዩ መንገድ የኢጣልያን ታላቅነት ፣ የኢትዮጵያን መንግሥት ታናሽነት ፡ ኢትዮጵያ በኢጣልያ ጥገኝነት ውስጥ መገኘቷን እያስረዱ ሁለቱን ዓመት ቆዩ ። በኋላም ካፒቴን ፔርሲኮ አምባላጌ መጥቶ ከሞተ ወዲህ አውሳ ያሉት ኢጣልያኖች የአምባ አላጌ ጦርነት የሆነ ጊዜ የተገላቢጦሽ ፣ "የምኒልክን ጦር የኢጣልያ ጦር አሸነፈው " ብለው አወሩ ። በአምባ አላጌ የኢጣልያኖችን ድል መሆንና የመቀሌን መከበብ ሁሉ እርግጠኛውን ነገር መሐመድ አንፉሪ እንዳያውቅ ፣ ከዐፄ ምኒልክ መልክተኛም ጋር እንዳይገናኝ ኢጣልያኖቹ አጥብቀው ሲጥሩ ቆዩ ። የዚህም ምክንያት እስካሁን ለመሐመድ አንፉሪና ለሌሎችም ሲሰብኩ የቆዩት የኢጣልያንን ኃያልነት ስለሆነ ፣ አሁን "የኃይለኛው የኢጣልያ ጦር በኢትዮጵያ ጦር ተሸነፈ " ማለት የተሰማ እንደሆነ የመሐመድ አንፉሪ አሳብ እንዳይለወጥና ከምኒልክ ጋር እንዳይደረብ ነው ።

መሐመድ አንፉሪ ፣ ዋናው ጦርነት እስኪዠመር ድረስ ከማዕከላዊው መንግሥት ከድቶ ጨርሶ ወደነርሱ መሆኑን ሳያረጋግጥ በጣም አወላውሎ ለሁለቱም ወገኖች ለየብቻ ታማኝነቱን ይገልጽ ነበር ። በመጨረሻ ግን ፣ ከኢጣልያኖች ወገን ተጽዕኖው ስለ በረከተበት ወደ ኢጣልያኖቹ ተደረበ ። አዛዥ ወልደ ጻድቅም የተለመደውን ያመቱን ግብር ቢጠይቁ ሳይልክ ቀረ ። ከአምባ አላጌ ጦርነት በኋላ ከዓድዋ ጦርነት በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ኢጣልያኖቹና ሽማግሌው መሐመድ አንፉሪ ፣ ልጆቹና ሹሞቹ በተቀመጡበት ስብሰባ እየተደረገ ሲመከር ሲዘከር ሰነበተ ። በስብሰባውም ላይ አብዛኛውን ጊዜ ኢጣልያኖቹ ለመሐመድ አንፉሪ የሚወተውቱት ፣ "እኛ በሰሜን በኩል የምኒልክን ኃይል ጨርሶ ለማጥፋት የበቃ ኃይል አለን ። ነገር ግን ፣ እናንተም የኛ የቃል ኪዳን ጓደኛ እንደ መሆናችሁ መጠን ከድሉም በኋላ በግንባራችሁ ያለውን ለምለሙን አውራጃ ለመካፈል እንዲመቻችሁ አሁን በቶሎ ወደ አንኮበርና ወደ ሐረር የአውሳ ጦር ይላክና ከሸዋ ጦር ጋር ይዋጋ ። በሸዋ ጦር ላይ የአውሳ ጦር የሚፈጽመውን አደጋ ሁሉ የኢጣልያ መንግሥት ከፍ አድርጎ እየገመተ ልዩ ልዩ ድጋፍና ገንዘብም መሣሪያም ለመስጠት ተዘጋጅቷል " እያሉ ነው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፣ ከዐፄ ምኒልክ ወገን ከግብር ማስገበርና የሩቅ ግንኙነት ከማድረግ በቀር ኢጣልያኖች የሚያወሩትን እያስተባበለ ፣ በአምባ አላጌም በመቀሌም እየተሸነፉ መመለሳቸውን በተጨባጭ

የሚያስገነዝብ አልነበረም ። የሆነ ሆኖ ፡ አንፋሪ ግብር በመከልከሉ ዐፄ ምኒልክን መክዳቱ ታወቀ ። ኢጣልያኖችም ፣ "እርሱን መሣሪያ አድርገው በእንኮበርና በሐረር ግንባር ጦር ሊልኩ ነው" የሚባል ወሬ ተሰምቶ ነበርና ዳግማዊ ምኒልክ ከአዲስ አበባ ተጉዘው ውጫሌ (ወሎ) በደረሱ ጊዜ ከዳቱን ስላረጋገጡ ፣ የሸፈተውን መሐመድ አንፋሪን እንዲወጉ ሦስት ታላላቅ መኳንንት ላኩ ። እነዚህም ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ፣ ደጃች ተሰማ ናደው ፣ የአንኮበሩ አዛዥ ወልደ ጻድቅ ሲሆኑ የበላይ መሪውም አዛዥ ወልደ ጻድቅ ናቸው ። ምክንያቱም ከሁለቱ መኳንንት በሥልጣን እንኳን ባይሆን በዕድሜ ስለሚሸመግሉ ነው ። እንዲሁም ጦርነቱ የሚደረግበት የእንኮበርና የአውሳ አውራጃ የርሳቸው ክፍል በመሆኑ ጭምር ነው ። ሁለቱ ታላላቅ መኳንንት ራስ ወልደ ጊዮርጊስና ደጃች ተሰማ በሥልጣን እንዳይቀናኑና ተባብረው እንዲሠሩ ለማድረግ ከሁለት ላንዳቸው በመስጠት ፋንታ የጦር አበጋዝነቱን ለአንኮበሩ አስተዳዳሪ ለአዛዥ ወልደ ጻድቅ የሰጧቸውም ይመስላል ። የሆነ ሆኖ ፣ እነዚህ ሦስቱም መኳንንት የየራሳቸውን ጦር ይዘው በአዛዥ ወልደ ጻድቅ መሪነት በታኅሣሥ ወር በእርሳ ፣ በሁለዳዊ ፣ በሁምራ በኩል ሲያልፉ በጥር 17 ቀን ብዙ ጊዜ በማመንታት የቆየው መሐመድ አንፋሪ ጦሩን ይዞ መጥቶ ጦርነት ገጠማቸው ።

ስለ ጦርነቱ ግራዝማች ዮሴፍ ከተዉት ማስታወሻ በተጨማሪ በሌላ ጽሑፍ ሙሉው ባይገኝም ፣ እነዚሁ እነራስ ወልደ ጊዮርጊስ ወደ አውሳ ሲዘምቱ የዋሉበትንና ያደሩበትን መንገድ በዘረፋ ምክንያት ከዳዊ አገር ባላገር ጋር ወታደር መታኮሱን ፣ በዚህም አዛዥ ወልደ ጻድቅ ፣ "ጠላታችን ገና ወደፊት እያለ በግና ፍየል ጥይቱን ከፈጀው እኔስ ለምን እሔዳለሁ ። ጠላታችንንስ በምን እንወጋዋለን"* ብለው ራስ ወልደ ጊዮርጊስንና ደጃች ተሰማን ተቆጡአቸው ።

ሁለቱም መኳንንት ወረራ የሔደውን ሰው ሁሉ ገርፈው ያመጣውንም በግና ፍየል ደጃን ለዋለው ሰው እንደ ሰጡበት ይኸው ጽሑፍ ይገልጻል ። ከዚህ አያይዞ ኢቂ መስጊድ በሰፈሩበት ጊዜ ፣ "እናንተ የመጣችሁት እኔን ለመውጋት አይደለም ፤ የምትሹት አብዱራህማንን ስለሆነ እሱ የሚገኘው ቲሮ ነውና ሚሌን ይዛችሁ ወደ ቲሮ ሒዱ ። ደግሞ አሽከሮቻችሁ አሽከሮቼን ገድለው ጦር ፣ ጋሻ ፣ ጩቤ ወስደዋልና መልሱ ። ከዚህም ስፍራ የዋላችሁና ያደራችሁ እንደሆነ አዳል

* ትርጕሙ ወታደራችሁ በግና ፍየል እየቀማ ከባላገር በመታኮስ እዚሁ ጥይቱን ከጨረሰ በኋላ ከመሐመድ አንፋሪ ጋር በምን እንዋጋለን ማለት ነው ።



መጀኑ ይፈጃችኋል ፤ ሚሊን ተሻግራችሁ እደሩ" የሚል የመሐመድ ሐንፈሊ (አንፋሪ) መልስ መጣ ። ከዚያ ከደባል ተነሥተው በጥር 17 ቀን ስርዶ ሰፍረው ሳለ ፣ ከከተማው ጦሩን አስከትቶ የሁለት ቀን መንገድ ተጉዞ መጥቶ ጦርነት እንደ ገጠማቸውና ድል እንደሆነ ፣ የመሐመድ ሐንፈሉም አሊ የሚባል የሚወደው ልጅ ፣ የወንድሙ ልጆች ፣ ሦስት ያጐቱ ልጆች እንደሞቱ ይነበባል ። እነአዛዥ ወልደ ጻድቅም ከዚህ ድል በኋላ ወደፊት አልፈው ከከተማው አድሌ ገብ (ሐደሊ ገብ) በሰፈሩ ጊዜ ፣ ኢጣልያኖቹ የሰጡት ወጨፎ ወተርሴ እንደ ተገኘ ፣ ከዚያ በኋላ ባገሩ ጠባቂ አድርገው እንደ ተመለሱ በማረጋገጥ የአውሳውን ታሪክ ይፈጽማል ።[1]

ሦስቱ ታላላቅ መኳንንት ፣ ኢጣልያኖች በጣም ተስፋ ያደረጉበትን ፣ መሐመድ አንፋሪን በጥር 17 ቀን ሲያሸንፉ ፣ ላገራቸውና ለንጉሣቸው ከፍ ያለ ሙያ ሠርተዋል ። በዓድዋ በኩል የተሰለፈው ዋናው ንጉሡ ያሉበት ጦር መኳንንቱም ፣ ወታደሩም ሞራሉ ከፍ እንዲልና ዋናውን ጦርነት በልበ ሙሉነት እንዲቀጥል አድርገውታል ። የአውሳውን ድል ለመንገር ከነአዛዥ ወልደ ጻድቅ የተላኩት ሰዎች ዐፄ ምኒልክ ዘንድ የደረሱት በየካቲት 22 ቀን እንደሆነ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ገልጸውታል ።[2] በጥር 17 ቀን ድሉን ካገኙ ወዲህ ፣ መልክተኞቹ ወደ ዐፄ ምኒልክ ለመድረስ ከአንድ ወር በላይ ጊዜ ፈጅተዋል ማለት ነው ። የዚህ ወሬ በትክክል በተሰማ በማግሥቱ የካቲት 23 ቀን የዓድዋው ጦርነት ተደረገ ማለት ነው ።


የእንኮበሩ ሊቅ አለቃ ዘወልዴ አዛዥ ወልደ ጻድቅ እዚህ (አውሳ) ድል አድራጊነት በቅድሚያ እንደቀናው አንተም ምኒልክ በዚያ (በዓድዋ) ደግመህ አሸንፍ ለማለት ቀጥሎ ያለውን ቅኔ ተቀኙ ።

ምኒልክ ድግም ድምፀ የብቦ
እስመ ወልደ ጻድቅ ቀደመ ድምፀ ይባቤ በገቦ
ዓልቦ ዘነግሠ ቅድመ ዚአከ
ወድኅረ ዚአከ ዘይነግሥ ዓልቦ

1 ከፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከእጅ ጽሑፍ ክፍል የተገኘ ።
2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ምዕ.63



አዛዥ ወልደ ጻድቅ
ከደ ካስትሮ ኔላ ቴራ ዴል ንጉሥ




ራስ ወልደጊዮርጊስ አቦዬ

ኢንአቢሲኒያ ከሚባለው ከአናራቶሪ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት

## በኢጣሊያኖች ዘንድ የጦርነት ምክር — በሰላይ ተታለው ከምሽግ ወጥተው ለመዋጋት እንደቆረጡ

ባፄ ምኒልክ ዘንድ ባለፈው እንደ ተመለከትነው ፣ ጣልያኖች ከምሽግ ወጥተው አለመዋጋታቸው ፣ መረብን ተሻግሮ የመውረሩ ነገር በአንድ ወገን በወሃ እጦት የተነሣ መቅረቱ ፣ ወደሰሜን አቅጣጫ ጦር ሠራዊቱን አነቃንቆ ጣልያኖችን ከምሽግ የማስወጣቱ አሳብ መሳቱ ፣ ስንቅ አልቆ ወታደር አንዳንድ ጊዜ እስከ ሺሬ ድረስ እየዘለቀ በዘረፋ ከባላገር ጋር መጣላቱ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮ ነበር ። ይህ የተደራረበው ችግር ሁሉ አንድ መፍትሔ ለመፈለግ አስገድዷል ። ለዚህ ሁሉ የተገኘው መፍትሔ ፣ እንደ ምንም በሰላዮች አማካይነት አታሎ ከምሽግ ጣልያኖቹን እንዲወጡና እንዲዋጉ ማድረግ ስለሆነ ይህንኑ ለመፈጸም በየካቲት 23 ቀን በተደረገው የጦርነት ዋዜማ ንጉሠ ነገሥቱና ራሶቻቸውም ትኩረት ሰጥተዋል ። በዚህም ተግባር የእንትጮው ተወላጅ ባሻ አውአሎም ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል ።

በዐፄ ምኒልክ በኩል ፣ ይኸን የመሰለ ችግር ሲኖር በጄኔራል ባራቲዬሪ በኩል ያለው ችግር ይነስ ይብዛ ተመሳሳይ ነው ። በሁለቱ ጦር መሪዎች መካከል ልዩነት ቢኖር ፣ እርሱ የበላይ አዛዦች ሲኖሩት ዐፄ ምኒልክ የበላይ የለባቸውም ። እርሱ ወደ ምሽጉ ለመሳብ ፣ እርሳቸው ወደ ሜዳ እንዲወጣ ለማድረግ በመሞከር በዓላማ ይለያያሉ ። በሁለቱም የጦር ሠፈር የሁለቱም ወገን ሰላይ ተሠማርቶ ወሬውን ለየክፍሉ ያቀብላል ። በቃፊርነት የሚያገለግሉትም እየተቀያየሩ ሥራቸውን በየበኩላቸው በትጋት ይሠራሉ ።

ጄኔራል ባራቲዬሪ ወጥቶ ለመዋጋት አዳጋች መሆኑንና ፣ በምሽግ መቆየቱም የስንቅ ማለቅ ችግር እንደሚያስከትል ተረድቶታል። በቅርብ ከድተው ወደ ወገናቸው የሔዱት እነራስ ሰብሐት የአጋሜንና የእንደርታን ሕዝብ ከማሳደም ጋር ከጀርባው መንገድ እያፈረሱና የስልክ ሽቦ እየቆራረጡ ፣ በማይ መሬት እንደሆነው ፣ አንድ አንድ ጊዜም ይዋጉታል ። ይኸ ሁሉ ተደራርቦ ሥጋትና አሳብ በራሱ ኃላፊነት ላይ ተንጠልጥሎ እንቅልፍ ነሥቶታል ።

ከሁሉ የበለጠ የሚያናድደው ከሮማ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚያስተላልፍለት ምጸትና ወቀሳ አዘል ቴሌግራም ነው ። ባንድ ወገን ፣ “ በአንድ ውጊያና ድል የአምባላጌንና የመቀሌን ውርደት ሊመልስ አልቻለም ” ብለው በሮማ በርሱ እግር ፣ “ከርሱ በብዙ ረገድ የተሻለ ነው” ብለው የሚያምኑበትን ጄኔራል ባልዲሠራን እ.ኤ.አ. በየካቲት 22 ቀን ሾመውታል ።

በተወሳሰበ አሳብ ላይ የሚገኘው ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ “አበሾች እመሸግሁበት መጥተው ይወጉኝና አሸንፋቸዋለሁ” ብሎ ጠብቆ ሞኝ ባላጋራ በማጣት ሳይሆንለት ከቀረ ወዲህ ፣ “ ከአለንበት ከአዲግራት ወደኋላ ወደአዲ ኡግሪና ወደ ሰናፌ ተመልሰን ለስንቅ ማግኛው ለአሥመራና ለምጥዋ ቀረብ ባለው ሥፍራ ሆነን እንከላከል” አለ ። የበታች የጦር አለቆቹ ፣ “በእምባ አላጌና በመቀሌ ድል እየሆንን የሰቀቅነው አገር አንሶ ፣ አሁን ደግሞ ከአዲግራትና ከሳውሪያ ወደኋላ ከተመለስን ጩርሶ የመሸነፍ ያህል ነው” ብለው ተከራከሩት ። በመጨረሻ የመሣሪያና የስንቁ ኃላፊ ሌተና ኮሎኔል ራፓሞንቲ እ.ኤ.አ. ከመጋቢት 4 ቀን በኋላ ፣ በከብትና በስንቅ ማለቅ የተነሣ አዲግራትና ሳውሪያ ላለው ጦር ስንቅ ለማቀበል አለመቻሉን ለጄኔራል ባራቲዬሪ በቴሌግራም አስተላልፎለታል ። ስለዚህ የዚህ ሁሉ የችግር ሐተታ የተጫነው ይኸው ጠቅላይ አዛዥ አንድ ውሳኔ በቶሎ ለመወሰን በግድ አስፈላጊነቱ ተሰማው ።

በዚህ ምክንያት ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ ወደኋላ ማፈግፈግ ወይም ወደፊት ገፍቶ መዋጋት የሚገባ መሆኑን ከበታች ጄኔራሎች ጋር ለመመካከር የካቲት 20 ቀን በድንኳኑ ውስጥ ሰበሰባቸው ።
የተሰበሰቡትም ፣

| | |
|---|---|
| ጄኔራል ጆሴፔ አሪሞንዲ | የብርጌድ አዛዥ |
| ” አማኑኤል ዳቦርሚዳ | ” ” |
| ” ማቴዎ አልቤርቶኒ | ” ” |
| ” ጆሴፔ ኤሌና | ” ” |
| ኮሎኔል ቫሌንዛኖ | ሼፍዲታ ማጆር |

ናቸው ። እነዚህም በተሰበሰቡ ጊዜ ዋናው አዛዥ ሌተና ጄኔራል ባራቲዬሪ ከስንቁ ኃላፊ ከሌተና ኮሎኔል ራፓሞንቲ ፣ አሥመራ ከሚቀመጠው ከምክትሉ አገረ ገዥ ከጄኔራል ላምቤርቲ የተላኩትን ቴሌግራሞች ኮሎኔል ቫሌንዛኖን እንዲያነብ አዘዘው ። ከተነበበና አንዳንድ ንግግር ከተደረገ በኋላ ጄኔራል ባራቲዬሪ እንደዚህ አላቸው ። “የመ



ጨረሻው ውሳኔ የሚሰጠው ከኔ በመሆኑ ፣ አሁን የጠራኋችሁ ለጦርነት ምክር አይደለም ። ነገር ግን እንደ ዘወትሩ ቅን ልባችሁን ገልጣችሁ አሳባችሁንና የጦር ሠራዊቱን ሁኔታ እንድትገልጹልኝ ነው ።”

ከዚህ በኋላ በመጀመሪያ ጄኔራል ዳቦርሚዳ እንደዚህ ሲል ተናገረ ።

> በአሁኑ ጊዜ አንድም ወታደር ከጠላት ጋር ከተሰለፍን ከሦስት ወር በኋላ ወደኋላ እንመለስ የሚል አይገኝም ፤ ኢጣልያም ወደኋላ ከመመለስ ሁለት ወይም ሦስት ሺህ ሰው በጦርነት መሠዋትን ትመርጣለች ። እንዲያውም ስንቅ ከማለቁ የተነሣ ፣ ሌሎች አመርከብ ላይ ያሉት ወታደሮች ሳይደርሱ እኛው በቶሎ እንዋጋ . . . የወታደሩም ከፍ ያለው ሞራሉ (መንፈሱ) ወደኋላ እንመለስ ያልነው እንደሆነ ዝቅ ብሎ ይዋረዳል ። ሹማምንቱም ሁሉ አሳባቸው ከዚህ ያልወጣ መሆኑን በዋስትናዬ አረጋግጣለሁ ። ወደኋላ እንመለስ ያልን እንደሆነ ግን ፣ በቁጥር የሚበልጠን በጉዞና በመንገድ ከኛ የሚፈጥነው መንገዱን ሁሉ የሚያውቀው ጠላታችን ከሸፈቱብን ሰዎች ጋር ተስማምቶ በሰላዮቹ እየተመራ ተከታትሎ እየወጋ አደጋ ሊያደርግብን ይችላል ።[1]

ከጄኔራል ዳቦርሚዳ ቀጥሎ የተናገረው ጄኔራል አልቤርቶኒ ነው ። እርሱም ያገር ተወላጅ ጦር አዛዥ በመሆኑ ፣ ወዲያውም ያገር ውስጥና የኢትዮጵያንም ጦር ሁኔታ በስለላ የሚያስመረምር ነበርና በተራው እንደዚህ ብሎ ተናገረ ።

> የጠላት ጦር እየጐዳ ሔዷል ። ግማሹ ወደ ሽሬ ለዘረፋ ተበትኗል ። ግማሹ ወደ ሸዋ መመለስ ጀምሯል ። ዓድዋ በቀረውም ጦር ላይ በሽታ ገብቶበታል ። . . . ጐበዙ ኰሎኔል ስቴባኒ የሁለት ባታዮ . . . ካፒቴን አደኔ የሁለት ክፍል (ኮምፖኘ) ጦር ይዘው ደርሰዋል ። ማጆር ባሌ ኃይለኛውን የ7ኛውን ቦታዮ ጦር ይዞ ነገ ጧት ይደርሳል ። መድፎቻችን በደህና ሥፍራ ተጠምደዋል ። ወደ ዓድዋ የሚወስዱ መንገዶች ሰለአሉ በነዚያ አልፈን ይኸን የሰነፈውን የጠላት ጦር አደጋ እንጣልበት ። እስካሁን ድረስ ባለው ጊዜ ስምምነት በመካከላችን ሳይኖር እዚህ ደርሰናል ። አሁን ግን ፣ ወደፊት አልፎ ለመዋጋት የሁላችን ፈቃድ ነው . . . ወደኋላ ያፈገፈግን እንደሆነ ግን ፣ እስካሁን ደክመን ያቆምነውን የጠላት ጦር ለቀን ቅኝ አገራችንን ሰወረራ አሳልፈን መስጠታችን ነው ። ከዚህም በቀር ወደኋላ መመለስ የኛን ጦር መንፈስ ሃምሳ በመቶ ያቀዘቅዘዋል ።

ጄኔራል አልቤርቶኒ ፣ በስብሰባው ይኸን ቃል መናገሩን ጄኔራል ባራቲዬሪና ሌሎች ጸሐፊዎች ሁሉ በጻፉት ይገኛል ። ነገር ግን ፣ እርሱ ራሱ በኋለኛው ዘመን በጻፈው ማስታወሻ የቀረውን ሁሉ መናገሩን ሲያ

1 Adua, E. Bellavita, PP, 318 - 319. La Prima Guerra d' Africa, R, Battaglia, PP, 733-786

ምን ፣ "ያበሾቹን መታመም ወይም ወደ ሸዋ መመለስ አልተናገርኩም" ሲል ከዷል ። ይኸውም የጦርነቱ የአጀማመሩ ምክንያት የስለላው ሥራ ስለነበረ ፣ አልቤርቶኒ ብዙ ጊዜ በምርኮ አዲስ አበባ ሰንብቶ ወደ አገሩ ሲመለስ የጦርነቱን ኃላፊነት ከራሱ ላይ ለማስወገድ "አላልሁም" ያለ ይመስላል እንጂ ፣ ከዓድዋ በፊት ባለው ጊዜ ሳይናገር አልቀረም ።

ከርሱ ቀጥሎ የተናገረው ጀኔራል አሪሞንዲ በፋንታው እንደዚህ አለ ።

> ያማሮቹን ቁጥር ሰላዮቹ የሚያመጡልን ከመጠን እያበዙ ነው ። ጠላት በመካከሉ ስምምነት ስለሌለው እኛን ለመውጋት ያመነታል። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ ወደፊት ቀድሞ መውጋት እንጂ ፣ እዚህ ውጊያ መጠበቅ ከንቱ ነው ። እንደዚህ ከተሰበሰብን በአንድነት ወደፊት አልፈን መዋጋት ይሻላል ። ከውጊያም ይበልጥ በሽታ ሊጨርሰን ይችላል ። ወደኋላ መመለስ ወታደሮቻችንን እስንፍ አልሆነ ሥፍራ ላይ ወደ መከላከል ያደርሰዋል ። ወደ ፈረሰው አገር ስንመለስ አገሬው ስለሚነሣብን ለጠላትም ይመቸዋል ። ከጠላት ጋር እንደዚህ ቅርብ ለቅርብ ተሰልፈን ብዙ ሳምንቶች ወጥተን ሳንዋጋ ማሳለፍም ስንፍና ነው ።

ከርሱ ቀጥሎ በመጨረሻ የተናገረው ፣ ባለፈው ጥር ወር ከኢጣልያ አገር የመጣው ጀኔራል ዥሴፔ ኤሌና ነው ። ከሁሉ መጨረሻ የተናገረው በሽምግልናው መሆኑን ራሱ ከውጊያው በኋላ ጀኔራል ባራቲዬሪ በተከሰሰበት የወታደር ፍርድ ቤት ጉባዔ በሰጠው ምስክርነት ሲገልጽ ፣ ራሱ የተናገረው ቀጥሎ ያለው መሆኑን ጨምሮ ያስረዳል ።

> አራተኛው ተናጋሪ እኔ ስለሆንኩ ፣ ሽምግልናዬ በመጨረሻ የመናገርን መብት እንደሰጠኝ ገለጽሁ ። በተረፈ እጦሩ ግንባር (እምሽጉ) ከደረስሁ 12 ቀኔ ብቻ ስለሆነ በጠላት ላይ በቁጥሩም በመንገዱም በውጊያውም ስፍራ አመራረጥ በሁኔታው ሁሉ የግል አስተያየት ስለሌለኝ የምሰጠው ቃል መሠረቱ የጓደኞቼ አሳብ ብቻ ነው ። ስለዚህ የነርሱን አሳብ በመከተል ወደፊት ሔደን እንዋጋ የሚሰውን ቃል ደግፌ የግል አሳቤን እንደዚህ በሚል ቃል ወሰንሁ ። "ወታደራችንን አጠቃለን እንሰብስብና ጠላታችንን አለበት ድረስ ሔደን እንፈልገው ።"

ከመጨረሻው ተናጋሪ ከጀኔራል ኤሌና ቀጥሎ የተናገረውና ጉባዔውን የዘጋው ዋናው አዝማች ጀኔራል ባራቲዬሪ ነው ። በእውነቱ የርሱ አነጋገር አስተያየቱም ከነርሱ የተለየ ነው ። በሹመትም ከፍ ያለ በእእምሮም የበሰለ ስለሆነ ፣ እንደ ሌሎቹ የራሱን ጦር አጋኖ የኢትዮጵያን ጦር ሳያኮስስ በአጭሩ እንደዚህ አለ ። " ምክሩ የድፍረት ነው ። ጠላታችን ጉበዝና ሞትን የሚንቅ ነው ። ለመሆኑ የወታደሮቻችን ሞራል (መንፈስ) እንደ ምንድነው ?" ብሎ ጠየቀ ። ሁሉም ጀኔራሎች በተጠንቀቅ ቆመው " በጣም ጥሩ ነው " ብለው መለሱለት ። ከዚያ በኋላ ፣ " እጠላት ሰፈር ያሉት ሰላዮቻችን የሚያመጡልኝን እጠብቃለሁ ፤ እነርሱ ወዲያው እንደ ደረሱ አንድ ውሳኔ እቆርጣለሁ ።" ብሎ ጀኔራሎቹን አሰናበተ ። ዋነኞቹ የብሪጌድ ጦር አዛዦች ይኸን በሚመካከሩበት ጊዜ ፣ የቀሩት የጦር አለቆች ከድንኳኑ ውጭ ሆነው ውሳኔውን ይጠባበቁ ነበር ።[1]

በጀኔራል ባራቲዬሪ ንግግር በመጨረሻው ፣ " ከጠላት ሰፈር ያሉት ሰላዮቻችን የሚያመጡልኝን ከሰማሁ በኋላ አንድ ውሳኔ እቆርጣለሁ " ያለው የእንትጮው ተወላጅ ባሻ አውአሎምን ነበር ። እርሳቸውም በስለላ እንደምን አገራቸውን እንዳገለገሉ ያገራችን ሽማግሌዎች ፣ ከሚያውቁት ጋር ካርሎ አናራቶሬ የሚባለው ኢጣልያዊ እንደዚህ ሲል ጽፏል ።

> ባሻ አውአሎም የሚባለው ከሰላዮቻችን አንዱ ነበረ ። እርሱም ለጠላታችንም ሰላይ ነው ። ከዓድዋ ጦርነት ከብዙ ቀን በፊት በራስ መንገሻ አቅራቢነት ከዐፄ ምኒልክ በተገናኘ ጊዜ ሃምሳ ብር ጉርሻ ተቀብሎ ራስ መንገሻ ሊያውቅ የሚፈልገውን እየመረመረ በመግለጽና እንደዚሁም ራስ መንገሻ የሚለውን ለባራቲዬሪ በመንገር ጠንክሮ እንዲሠራ ከምኒልክ አደራ ተቀብሎ ተሰናበተ ። ከዚህም ቀን በቀር ከንጉሡ ጋር ሁለተኛ አልተገናኘም ። ራስ መንገሻ እንደነገረው አውአሎም ወደ ጀኔራል ባራቲዬሪ መጥቶ ፣ "የኢትዮጵያ ጦር ስንቅ አልቀበታል ። ብዙም ወታደሮች ሞተዋል ፤ የቀሩትም ታመዋል ። ስለዚህ በዓድዋም ከመቀመጥ ወደኋላም ከመመለስ ፣ ወደፊት ወደ ቅኝው አገር መረብን ተሻግረው አልፈው ስንቅ ሊፈልጉ ነው ።" አለ ። ዚያም ደግሞ በመጋቢት 1 ቀን 'የካቲት 23 ቀን' ንጉሡ እንደ ፊተኛው አሳቡ ወደኋላ ለመመለስ ነው ብሎ ተናገረ ። ከዚህም ወሬ የስንቁ ማለቅ የበሽታው መግባትና ወደኋላ ለመመለስ መታሰቡ እውነት ነው ። ወደፊት ወደ ኤርትራ ሊገቡ አስበዋል ያለው ግን እበቱ ነው ። ባራቲዬሪ ለመዋጋት የቆረጠው በተለይ በነዚህ ወሬዎች ተመሥርቶ ይመስላል ።
>
> ባሻ አውአሎም ፣ በ22 ሰዓት (ከሌሊቱ በ4 ሰዓት) የተደረገውን የኛን ስልፍ በተመለከተ ጊዜ የኢጣልያኖች ጦር መጣ ብሎ እንዲነግር አንድ ወጣት ላከ ። ምኒልክ ግን ፣ ሌሊት አገር ለመፈተሽ የወጡ ወታደሮች ይሆናሉ እንጂ ጣልያኖች ውጊያ ቆርጠው የሚወጡ አይመስሉኝም ሲሉ መጠርጠራቸውን ገልጸው ፣ ቢሆንም በጥንቃቄ መጠባበቅ ነው የሚል ትእዛዝ ለራስ መንገሻ ላኩባቸው ። ይኸም ሰላይ ከጀኔራል ባራቲዬሪ ጋር ሆኖ ወደፊት ተጉዞ እኩለ ሌሊትም ራዓዮ ተራራ ሲደርስ ከኛ ጦር ውስጥ አምልጦ የቱሪቶ ባታዮ ከመ

1 Memoire d' Afrique . . (Chap.) XXX; Italia ed Etiopia, PP. 316 - 321

ድረሱ በፊት ወደ ራስ መንገሻ ሰፈር ደረሱና በጊዜው ለራስ አሉላ ለራስ መንገሻ ለዋግሹም ጓንጉል ነገረ ። ለነዚህም ራሶች ራስ ወሌና ራስ መኩንን ደረሱላቸውና ሁሉም በአንድነት ግንባር ተደመና የኢጣልያ ጦር መታኮስ ሲጀምር ለመዋጋት ተዘጋጁ . . .[1]

ሌላ ደግሞ ፣ ግዕዝኛ ጽሑፍ ለስለላ ከባራቲዬሪ የተላከው ባላምባራስ ገብረ እግዚእ የሚባል መሆኑን ይጠቅሳል ። ገብረ እግዚእ ከባሻ አውአሎም ጋር ተነጋግሮ ሁለቱም ወደ ዐፄ ምኒልክ ገብተው "ጣልያንን ከምሽጉ ብናወጣልዎ ምን ይሰጡናል" ብለው እንደ ጠየቁዋቸው ፣ ንጉሡም ብዙ ብር ለመስጠት በመሐላ ቃል እንደ ገቡላቸው ይገልጻል ። ከዚህ በኋላ ባላምባራስ ገብረ እግዚእ ወደ ባራቲዬሪ ሔዶ የሠራዊቱን ስንቅ ፍለጋ መበተን ፣ ምኒልክ ለመሸሽ ማሰባቸውን ነገር እንዲወጣ ማድረጉን[2] ያረጋግጣል ። እንደዚሁም ግግሹ ሰላይ ፣ "ዐፄ ምኒልክ ታመዋል ፣ ራስ ወሌ ሞተዋል" እያለ በማውራት የኢጣልያ ጦር ከምሽግ እንዲወጣ ገፋፍቷል ማለት ነው ።

ስለዚህ የስለላ ጉዳይ ግዕዝኛው ሰነድ እንደዚህ ይላል ።

"ወእምዝ ፈነዎ ዠኔራል ባራቲዬሪ ለባላምባራስ ገብረ እግዚእ ወልደ አብ ከይሲ ከመ ይኩን ኀበ ባሻ አውአሎም እንተ ሰብአ ዓይን ዝውእቱ ለላይ ዘኢጣልያን ዘይነብር በጥቃ ዓድዋ ወተማከሩ እሉ ደቂቀ እባ ከይሲ ወቦኡ ኀበ ምኒልክ ወይቤልዎ ምንተ ትሁበነ ከመ ናውጽእ ለከ ሠራዊተ ጣልያን እምነ እርድ ። ምኒልክኒ ንጉሥ አሠፈዎሙ ለእለ ባሻ እውአሎም ከመ ይሁቦሙ ብዙኀ ብሩረ ወመሐለ ሎሙ ወእምዝ ሆረ ባሻ (ባላምባራስ) ገብረ እግዚእ እኀወ እውአሎም በጽሐ እንኪዉ ወዜነዎሙ ለዠኔራል ባራቲዬሪ ወአሪሞንዲ ከመ ተዘርወ ሠራዊተ ንጉሥ ለሐሚሠ እክል እስመ ጸንአ ቦሙ ረኃብ ወተርፈ ምኒልክ ለባሕቲቱ ወይፈቅድ ይጕየይ ከመ ያድኅን ርእሶ ወሰበ ሰምኡ ዘንተ እሉ ዠኔራል ተፈሥሑ ዓቢየ ፍሥሐ ወተንፍሑ ቀርነ ።"

ባለፈውም እንደ ተመለከትነው ፣ ከዚህ በላይም አናራቶሬ እንደ ጻፈው ፣ ዐፄ ምኒልክ ኢጣልያኖቹ እስከ መሸጉበት እስከ ሳውሪያ ሔደው እንዳይዋጉ ሠራዊታቸውን ማስጨረስ ስለሆነ ፣ ዝም ብለው የኢጣልያኖችን ከምሽግ መውጣት ለብዙ ጊዜ እንዳይጠብቁ በሰፈር በሽታ ገብቶ ከዚህም የባሰ ወታደሩ ስንቅ አልቆበት የሚራብ ፣ በዚህም የተነሣ በዘረፋ ከባላገሩ ጋር የሚጣላ በመሆኑ ከፍ ያለ ችግር እንዳይፈጠር ብዙ አስበውበታል ። አንወጣም ብለው ያስቸገሩትን ኢጣልያኖች ከምሽግ አውጥቶ ለመዋጋት ይኸን የመሰለ በተንኮል

1 In Abissinia, Carlo Annaratore, P. 343

2 የኢትዮጵያ ጥናት (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ቁ. 681 ፣ ገጽ 128—129



የማስወጣት ዘዴ መፍጠር አስፈለጋቸው ። ይህን ዘዴ ባለፈው ከአናራቶሬ ወይም ከግዕዝኛው ጽሑፍ እንደ ተገነዘብነው ፣ "የሐበሾች ጦር ስንቅ አልቆበት ተርቧል ። ግግሹም ታሟል ። ብዙም ሞቷልና አሁንም በድንገት ደርሰህ ብትወጋው ታሸንፈዋለህ" እያለ ለኢጣልያኖች ታማኝ መስሎ ተናግሮ የሚያሳምን ሰው ሲፈለግ ፣ የዚህ ተግባር በራስ መንገሻ ዮሐንስ አማካይነት በባሻ አውአሎም ላይ ወድቋል ። እርሳቸውም ወገኖቻቸውን በደንብ ለማገልገል ቢሉ አስመስለው በቀጥታ ወይም በነርሱ ታማኝ በነበሩት ዘባላምባራስ ገብረ እግዚእ አማካይነት ለባራቲዬሪ ነግረዋል ። በመጨረሻም የኢጣልያ ጦር አዛዥ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አንድ ጊዜ ፣ "ወደ ኋላዬ ልመለስ" ሌላ ጊዜ ፣ "በምሽጌ ተቀምጬ ሐበሾቹ እርስ በርሳቸው ተጣልተው ወይም ስንቅ አልቆባቸው ሲበተኑ እዋጋለሁ" እያለ ብዙ ጊዜ የቆየውን አሁን ባሻ አውአሎምና ጓደኞቻቸው በነገሩት ወሬ ተመርኩዞ በየካቲት 22 ቀን ማታ ከምሽጉ ወጥቶ ለመዋጋት እንዲቆርጥ አደረጉት ።

ጄኔራሎቹን ሰብስቦ አሳባቸውን ከሰማ በኋላ ፣ "እጠላት ሰፈር ያሉት ሰላዮቼ ከተመለሱ በኋላ አንድ ውሳኔ እሰጣለሁ" ብሎ በነበረው መሠረት የነዚህን የሰላዮች ወሬ ከሰማ በኋላ ፣ የመጨረሻውን የኢጣልያና የኢትዮጵያ ዕድል የሚወሰንበትን ትልቁን የዓድዋ ጦርነት ለማድረግ ጄኔራል ባራቲዬሪ እ. ኤ. አ. የካቲት 29 ቀን(የካቲት 22 ቀን) ማታ ጦሩን ከዚህ እንደሚከተለው አሰልፎ ለመውጣት ተዘጋጀ ።

፩ኛ. ጄኔራል ዳቦርሚዳ 3800 ወታደር 18 መድፍ ይዞ በቀኝ በኩል
፪ኛ. " አሪሞንዲ 2493 ወታደር 12 መድፍ ይዞ በመካከል
፫ኛ. " አልቤርቶኒ 4076 ወታደር 14 " " በግራ በኩል
፬ኛ. " ኤሌና 4150 ወታደር 12 መድፍ ይዞ ከኋላ ተጠባባቂ ሆኖ እንዲዘምቱ ተደረገ ።

የነዚህ ድምር 14,579 ወታደር 56 መድፍ ነው ። ሌሎች 5000 ግድምም ከሚሆኑት ውስጥ ግማሾቹ ከዋናው ጠቅላይ አዛዥ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ጋር ሆነው ፣ የቀሩት ደግሞ በልዩ ልዩ አገልግሎት ተከፋፍለዋል ። ከነዚህ ውስጥ 6790 የሚሆኑት በተጽዕኖዋቸው ሥር ካደረጉት ከልልና ከሱዳን ከሌላም ኢጣልያኖች ከያዙት አገር የተሰበሰቡ ያገር ተወላጅ ወታደሮች አሉበት ። በተረፈ ከማገርር አሜሊዮ 1300 ጦር በሰሜን በኩል በዩሃ አራተኛ የጦር ግንባር ከፋች ሆኖ እንዲዘምት ተደርጓል ።[1]

1 Memoire d' Afrique . . .Chap. XXXII; Italia ed Etiopia, P. ; 330in Abyssinia C. Annaratore . . PP. 345 - 350; The campaign of Adwa . . PP. 261 - 271,

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ በዚህ ዓይነት ጦሩን ከፋፍሎ ከደለደለ በኋላ ፣ እ.ኤ.አ. የካቲት 29 ቀን (የካቲት 22 ቀን) ያወጣው ትእዛዝ የዳቦርሚዳ ፣ የአሪሞንዲና የአልቤርቶኒ ጦር እያንዳንዱ ከማታው በሦስት ሰዓት የሳውሪያን ምሽግ እየለቀቀ በዓድዋ አቅጣጫ ጉዞውን እንዲጀምርና እነርሱም ጉዞ ከጀመሩ አንድ ሰዓት ቆይቶ ተጠባባቂው የኤሌና ጦር ተከትሎ እንዲጓዝ ነው ። አስቀድሞ እንማገርር ሳልሳ ያዘጋጁት ያገር ፣ የስፍራ ፣ የወንዛ ወንዝና ፣ የተራራዎች ምልክት ያለበት የጦር ፕላን ተሠርቶ ስለነበረ ፣ የዚሁ ፕላን እንዳንድ ግልባጭ ለአዝማቾች ተሰጥቶአቸዋል ። ሊዋጉ ያሰቡት በደንበኛ ፕላን ስለሆነ ፣በዚህ በፕላኑና በምክርም በተወሰነው መሠረት የቀኙ አዝማች የዛህላን በር የረቢ አሪዮኒን መንገድ ይዞ እንዲጓዝ ፣ የመካከለኛው አዝማችና ተጠባባቂው ጦር የእንዳ ገብጣን አቅጣጫ ይዞ እንዲጓዝና የግራው አዝማች በኪዳነ ምሕረት በር በኩል እንዲሔድ ተወስኗል ።

እንደ ወጣው ትእዛዝ ፣ እያንዳንዱ ወታደር 112 ጥይት ፣ የሁለት ቀን ስንቅ ፣ ከላይ የሚደርበውን ካፓ (መንጠልያ) ፣ የውሃ ኮዳና የዳቦ መያዣውን እንዲይዝ ፤ የእርድ ከብት ከነመሣሪያው በሠራዊቱ ኋላ እንዲጓዝ ፤ የዝኒ ክፍሎች (ምሽግና የጦር ስፍራ የሚያከናውኑት ) ስልከኞችና ቴሌግራም አስተላላፊዎች መሣሪያዎቻቸውን ይዘው በየክፍላቸው ሆነው ከየክፍሉ የጦር አለቆች የሚሰጣቸውን ቃል ለጠቅላዩ ሹም በፍጥነት እንዲያስተላልፉ ትእዛዝ በዝርዝር ተሰጥቷል ። ምንም እንኳን ጦሩ በቀኝ ፣ በግራ ፣ በመካከልና በኋላ አራት ላይ ቢከፈል ፣ ከዋናው ሰፈር ለጦርነት ጉዞ የሚጀመርበት ሰዓት ቢለያይ ፣ አንዱ ሠራዊት ሌላውን ርቆት እንዳይሔድና ተነጥሎ በመገሥገሥ ከጠላት ጦር ጋር ብቻውን ገጥሞ አደጋ እንዳይደርስበት ከበላዩ አዛዥ ለየጄኔራሎቹ ጥብቅ ትእዛዝ ተሰጥቷል ። የመንገድ መሳሳትም እንዳይኖር ተጠንቶ የተዘጋጀው የካርታ ፕላን ለየአለቆቹ ከመታደሉ በቀር ፣ በነርሱ ውስጥ ሆነው የሚያገለግሉት ያገር ተወላጆችና ባላገሮች መንገድ እንዲመሩ እየተከፋፈሉ ለየክፍሉ ጦር ተሰጥተው ነበር ።

ከነዚህም ጋር የዓድዋን አካባቢ የሚያውቅ እንደሚረዳው ፣ ሜዳ ቢኖርም በሜዳው ላይ ተበታትነው የሚታዩ ብዙ ጉብታዎች ስላሉ ፣ በነዚህ ጉብታዎች ሆነው “ቴሌግራፍ አፕቲክ” በሚባል መሣሪያ እየተመለከቱ ፣ “ለገሌ ረዳት ጦር ይጨመርለት ፤ እገሌ ወደፊት ይግፋ ወይም ወደኋላ አፈግፍጎ ለእገሌ ይደረብና ይኸን ስፍራ ይያዝ”የሚል ትእዛዝ የሚሰጡ የፕላንና የሎጂስቲክ ሹማምንት ተመድበዋል ። የነርሱን ትእዛዝ ደግሞ እያፋጠኑ ለየክፍሉ የጦር አለቃ የሚያደርሱ የፈረሰኛ ጓዶች አሉ ። ተዋጊ የጦር አባል ሞቶ ወይም ቆስሎ በወደቀ



ጊዜ በቶሎ አንሥተው የሕክምና እርዳታ የሚያደርጉት ሁሉ በየክፍላቸው በደንብ ተደልድለው ተሰልፈው ነበር ።

እንደዚሁም ፣ ወሬው ለኢትዮጵያ ጦር ደርሶ ተጠንቅቀው እንዳይጠብቁ በማለት ከሰፈር የመነሻው ጊዜና ሰዓት ለማንም እንዳይነገር በጥብቅ ታዞ ነበር ። ነገር ግን ይኸ ሁሉ ከኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ዠሮ ያመለጠ አልነበረም ። ጦርነቱ ካለቀ በኋላ ግራዝማች ዮሴፍ ተማርኮ በኢትዮጵያውያን እጅ ከገባው ከጄኔራል አልቤርቶኒ ጋር ጭውውት ሲያደርጉ ፣ ስለ ስለላ ጉዳይ አንሥተው በተነጋገሩበት ጊዜ ፣ “እናንተ ሰላዮቻችን የምትሏቸው ምኒልክ የላኩላችሁን ነው ። የናንተ ሰላዮች ይነስ ይብዛ በሙሉ ለንጉሡ የሚታዘዙ ናቸው ። እርግጠኛውን በናንተ በኩል የተደረገውን በትክክል ይነግሩን ነበር ” ብለው እንዳጫወቱትና የተማረኩትም የኢጣልያ ሹማምንቶች ከባታዮ ወታደሮቻቸው ውስጥ ሰላዮች የነበሩትን እንደ ተመለከቷቸው ፣አልቤርቶኒ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ያወጣው ማስታወሻ በኮንቴ ሮሲኒ ታሪካዊ መጽሐፍ ላይ ተብራርቶ ተገልጿል ።[1]

እዚህ ላይ እንባቢ ሊገነዘበው የሚገባው ፣ በዚህ ጊዜ በኢትዮጵያ በኩል የነበረውን የተሳካ የጦር ድርጅት ብቻ ሳይሆን ለድል ዋና መድን የሆነውን የስለላ ሥራ ነው ። የጦርነቱንም ድል ያስገኘው ምንም እንኳን የሠራዊቱ ዠግንነት ፣ የነገበየሁ ፣ የነታፈሰና የነበሻህ አቦዬ የጋለ አርበኝነት ቢሆንም ፣ ለመዋጋት ዕድል የተገኘው ከምሽግ አልወጣም ብሎ ያስቸገረው የኢጣልያ ጦር በነዚህ ሰላዮች ተታሎ በመውጣቱ ነው ። የኢጣልያን ጦር ያወጣሙን ሁኔታ ፣ የጉዞውን ፣ የጦርነቱን አጀማመርና ፍጻሜ በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንመልከት ።

---

1 Italia ed Etiopia.. PP. 325 - 326.

# ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

## የዋናው ጦርነት አጀማመርና ፍጻሜ በጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ

የኢጣልያ ጦር ፣ በ1887 ዓ.ም. በኮአቲትና በሰንዓፌ ራስ መንገሻን፣ ደብረ ኃይላ ላይ እነቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን በጦርነት ያሸነፈ ጊዜ "ከዚህ በኋላ የኢጣልያንን ጦር ማንም ሊመልሰው አይችልም ፤ የሚዋጋንም ቢኖር ፣ ሁልጊዜ አሸናፊዎቹ እኛ ነን" የሚል ጽኑ የየዋህነት እምነት ሮማም ለቅኝ ግዛት በመጡትም ኢጣልያኖች ዘንድ አደረ ።

በዚህ ምክንያት ፣ ከደብረ ኃይላ ጦርነት ወዲህ ልጓሙ እንደ ወለቀለት ፈረስ ከደብረ ኃይላ እየፎለሉ ረዣዥሙን የአጋሜን ፣ የእንደርታን ፣ የእንዳ መሆኔን ወረዳዎች አልፈው ዋጀራት ፣ አሸንጌ ሐይቅ አጠገብ ደረሱ ። በንጉሠ ነገሥቱ ከኋላ የተደገፈው ግንባር ቀደሙ የነራስ መኰንን ጦር መጠጋቱን ሲሰሙ ፣ ከአሸንጌ ሐይቅ ወደኋላ መለስ ብለው አላጌ ላይ መሸጉ ። የአላጌው ጦር ሲፈርስ እንደ ታላቅ ውርደት ቆጠሩት ። በቁጭት " የአላጌውን መሸነፍ እንመልሳለን" ሲሉ የመቀሌው ተደገመ ። "ሁለቱንም ውርደቶች በእጥፍ እንደማያዳግም አድርገን እንመልሳለን" ሲሉ የዓድዋው ተሠለሰ ። ጣልያኖቹም ወደፊት እንደምናነበው ፣ "በዓድዋ ድል ሳናደርግ መታረቁ የኢጣልያን ክብር ይነካል "ብለው በሮማ ዋና ምክር ቤት ተከራክረዋል ። ሦስተኛውም ውጤቱ የመሸነፍ በትርና ውርደት ማግኘት ሆነ ። ከዚህ ሁሉ ሽንፈት በኋላ ፣ በየጊዜው ተለምነው የገፈተሩትን ዕርቅ ሁሉ በመጨረሻ በግዴታ ሊቀበሉ ተገደዋል ።

በዚሀ ዘመን ፣ በኢትዮጵያ በኩል የታየው የጦር አመራርና የፖለቲካው አረማመድ ዘዴ አስደናቂ ነው ። ደንበኛ የጦርና የፖለቲካ ትምህርት ያልተማረው ወገን ፣ ተማርኩና ሠለጠንኩ የሚለውን ወገን በሁለቱም ግንባር አሸንፎታል ። ኢትዮጵያውያኑ በዝግታ ፣ በትዕግሥት ዕለት በዕለት የጦር ኃይላቸውን እያጠናከሩ ሲሔዱ ባገኙትም ድል ኩራትና ትምክህት አሸንፏቸው ሳይገነፍሉ ፣ በየድሉ ማግሥት የሰላም እጃቸውን ለኢጣልያ ሲዘረጉ ቆይተዋል ። የሁለቱን ጦር ሠራዊት ዕድል የወሰነው የዓድዋው ጦርነት ተጀምሮ ሳለ ፣ ጣሊያኖች የተማመኑበት ግንባር

ቀደሙ ጦር ፈራርሶ ከሚደነፉት ጄኔራሎች አንዱ ተማረከባቸው ፤ ሁለቱ ሞቱ ፤ አራተኛው ከዋናው አዝማች ጋር ወደ አሥመራ ለመሸሽ ተገደደ ።

ቀጥሎም ፤ የኢትዮጵያ ተዋጊዎች ዓድዋ ላይ ሠፍረው ሳለ ፤ ግንባር ቀደሙና ቃፊር ጠባቂው የጠላት ጦር እስከ ገንደብታ ዘልቆና የኢጣልያ ጦር ከምሽግ ወጥቶ መዋጋቱን ሲጠባበቁ ፤ እነሆ በመጨረሻ እንደ ተመኙት ፤ የኢጣልያ ጦር ደርሶ ባለፈው ምዕራፍ እንደ ተገነዘብነው ፤ ግንባር ቀደሙ ጦር ሊፈታ ቻለ ። ያወጣጡንና ያጀማመሩን ሁኔታ በኢጣልያኖች በኩል ያለውን ባለፈው በዝርዝር ተመልክተነዋል ። ከጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ መጽሐፍ ላይ የሚገኘው ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

> ...ከኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ውስጥ የተከዜን ወንዝ ተሻግር እስከ ጸለምት ግማሹ ወደ ሽሬ የቀረውም ወደ ተምቤን ሰንቅ ፍለጋ ሔዶ ስለነበረ ፤ ቅዳሜ ማታ(የካቲት 22 ቀን) ዐፄ ምኒልክ ቀኛዝማች ታፈሰን አስጠርተው እንደዚህ አሉት ። “ሰንቅ ፍለጋ የሔዱት... ተመልሰው የገቡ እንደሆነ ሰኞ እንሔዳለን (ወደ ሐማሴን) ። ስለዚህ አንተ በሌሊት ተነሥተህ ከግምጃ ቤት ጓዝ ወስደህ መተላለፊያችንን እንዳያውኩ በየሠፈሩ የሞቱትን የበቅሎና የፈረስ ሬሣ እያቃጠልህ አጥፋ ።” ቀኛዝማች ታፈሰንም ማዘዛቸው ለጦርነትም ለሌላውም ጉዳይ ሁሉ ታፈሰ ሥራውን ሁሉ የማከናወን ስጦታ እንዳለው በማወቃቸው ነው ። ቀኛዝማች ታፈሰም እሺ ብሎ እንደ ታዘዘው ሔደ ። የዚህም ቀን ቃፊር ሆኖ የማስጠበቁ ተራ የራስ መንገሻ ዮሐንስ ነበር ። ቀኑም (ሲነጋ) የካቲት 23 ቀን የጊዮርጊስ በዓል ነበር ።
>
> ከሌሊቱ 11 ሰዓት ግድም የኢጣልያ ጦር በድንገት ደረሰ ። 500 ከሚሆኑት በር ከሚጠብቁት ከራስ መንገሻ (ዮሐንስ) ወታደሮች ጋር ገጠመ ። እነዚህም መልሰው ሲዋጉ ሁለት ባሻ ቡዙቅ ማረኩና ቢጠይቋቸው ፤ “ግማሹ ያፄ ምኒልክ ጦር ሰንቅ ፍለጋ መሔዱን ስለሰሙ ኢጣልያኖቹ በድንገት አደጋ ጥለው ለመዋጋት አራት ጄኔራሎች በአባ ገሪማ በኩል ፤ አንደኛው ጄኔራል በማርያም ሸዊቶ በኩል ተሰልፈው ይጓዛሉ” ብለው ተናገሩ ። ይኸን ሲሰሙ ከቃፊር ጠባቂዎቹ አንዱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር እየሮጠ ሲሔድ በመንገድ ቀኛዝማች ታፈሰን አገኘና የያዘውን ወሬ ነገረው ። በዚያን ጊዜ ቀኛዝማች ታፈሰ ከበቅሎ ወርዶ እፈረሱ ላይ ተጋባና በግልቢያ ወደ ንጉሡ ድንኳን ደረሰና ለእልፍኝ ዘበኞቹ ንገሩልኝ አለ ... ዐፄ ምኒልክም ከድንኳኑ ወጣ ብለው ምነው ብለው ቢጠይቁት ኢጣልያኖች አደጋ ለመጣል መምጣታቸውን ተናገረ ። ዐፄ ምኒልክ ኢጣልያኖች ተሰልፈው በጣም ተጠግተው ጦርነቱን ካልዠመሩ በቀር ጦሬን አስልፌ ሁለተኛ አልወጣም ብለው ስለነበረ “በከንቱ አስልፎ ሊያሶጣኝ ሳይሆን ሊዋጋ የመጣ መሆኑን ታምናለህን ?” ብለው ታፈሰን ቢጠይቁት “ዛሬስ እርግጥ ነው” ብሎ መለሰ ። በዚያን ጊዜ ዐፄ ምኒልክ



“ሒዳችሁ ይኸን ወሬ አረጋግጡ” ብለው በጅሮንድ ከተማንና* የፈረስ ዘበኞችን አዘዙ ። ከዚያ ወታደሩን ሁሉ መማሪያውን ይዞ እንዲነግ ካዘዙ በኋላ ራሳቸውም የጦርነት ልብሳቸውን ለበሱና ወደ እዳራሹ ድንኳን ሔደው ተቀመጡ ። በዚህን ጊዜ ፀሐይ ወጣች ፤ የትግሬ ጦርም ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምሮ ሳያቋርጥ ይታኮስ ነበርና ሲነጋ በሩቅ የጠበንጃው ጢስ ይታይ ነበር ። የራስ ሚካኤልም ሰዎች ወዲያው ሔደው ወደ ጦርነቱ ተጨመሩ ።

ከጦሩ ሁለት ሲሶ ግማሹ ሰንቅ ፍለጋ የቀረውም አክሱም ጽዮንን ለመሳለም ሔዶ ያለው አንድ ሲሶ ብቻ ነበር ። በሰፈር የነበረው የተኩሱን ብዛት በሰማ ጊዜ ሁሉም መማሪያውን እየያዘ ወደ ጦርነት ሲጓዝ ዐፄ ምኒልክም በበቅሎ ሆነው ተከተሉት ። በዚህም ቀን አገልጋይ ከጌታው ፤ ወታደር ካለቃው ተለያዩና ሁሉም ነዶ እንዳየ ዝንጀር ወደፊቱ ጦርነትና መድፍ ወዳለበት ሳገሩና ለንጉሡ ለመሞት ገሠገሠ ። ማንም ሰው “መድፍ ይመታኛል ፤ የጠበንጃውም ጥይት ይመታኛል” ብሎ በልቡ ፍርሐት ያደረበት የለም . . . አለቃው ሲወድቅ ወታደር ፤ ወንድሙ ሲወድቅም ወንድሙ አያነሣውም ። ቁስለኞቹ ራሳቸው “አልጋው ይርጋ እንጂ እኔን ስትመለስ ታነሣኛለህ ። ስለዚህ እንዳታነሣኝ በመሃይምን እንደበቴ ገዝቼሃለሁ” ይሉ ነበር ። ጥይቱ ያሰቀበት ወታደር ከቆሰለው ወገብ ላይ ወስዶ ተኩሱን ይቀጥላል ። አንዳንዱም በሩቁ ሰፍራ እየሮጠ ተዋግቶ ድካም ሲሰማው ዐረፍ ማለት ይጀምርና ወዲያው ተነሥቶ “ሙማ ሳበላኝ ጠጅ ሳጠጣኝ ጌታዬ ለምኒልክ ብድሩን እንዴት ነው የምመልሰው ”ይል ይደነፋና ጦርነቱን እንደገና ይጀምራል ።

ንጉሡ ወደ ጦርነቱ ቦታ ሲደርሱ ፤ አቡነ ማቴዎስና የማርያምን ታቦት የያዙት ካህናት በኋላቸው ነበሩ ። እቴጌ ጣይቱም ከዘበኞቻቸውና ከደጋፊዎቻቸው ጋር ሆነው በአቡነ ማቴዎስና በታቦቷ ጐን ነበሩ ። የአክሱም ካህናት ቅዳሜ ማታ እንደ ጥንቱ ያስተዳድሩን ብለው ለንጉሡ ለማመልከት መጥተው አድረው የነበሩት በዚህን ጊዜ የእመቤታችንን ሥዕልና ሰንደቅ ዓላማ ይዘው በእቴጌ ጣይቱ ግንባር ተሰልፈው ነበር ። የጽዮን እምቢልተኞችም በእቴጌይቱ ፊት ይጫወቱ ነበር ። . . . ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምሮ እስከ 4 ሰዓት ድረስ ተኩሱ ሳያቋርጥ ከሁለቱም ወገን ሲተኮስ ድምፁ እንደ ሐምሌ ጉርፍ ከመድፉ ተኩስ የሚወጣውም ጢስ የተቃጠለ ቤት ይመስል ነበር ። . . . . በዚህ ቀን ፤ በዓድዋ በዐይናችን ያየነውንና በጆሮአችን የሰማነውን ለመጻፍ ችግር ነው ። በዚህ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ በማጀራታቸው ድንጋይ ተሸክመው በጉልበታቸው ተንበርክከው በጋለ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ነበር ። በወታደር በታጠሩት ንጉሠ ነገሥት ላይ የመድፍና የጠበንጃ ጥይት እንደ ዝናም ይወርድ ነበር ።

እቴጌ ጣይቱ ጥቁር ጥላ አስይዘው ፤ ዐይነ ርግባቸውን ገልጠው በእግር እየተራመዱ በንጉሠ ነገሥቱ ልጅ በወይዘሮ ዘውዲቱና በደንገጡሮች ታጅበው ወደፊት ጉዟቸውን ቀጠሉ ። ወዲያውም

---

*በጅሮንድ ከተማ ማለት ከዓድዋ ድል ወዲህ አንድ ጊዜ አፈ ንጉሥ ተጥሎ ደጃዝማች ተብለው ያገር ግዛት ሚኒስትር የነበሩት ናቸው ።

የኋላው ወታደር ሲያመነታ አይተው ፣ "በርታ ምን ሆነሀል ድሉ የኛ ነውና በለው" ብለው በተናገሩ ጊዜ ወንድ ሴት ሲያበረታው መሸሽ አይሆንለትምና ሁሉም ወደፊት ገፉ ። እቴጌይቱ በዚህ ቀን የሴትነት ባሕሪያቸውን ትተው እንደ ወንድ ወታደሮቻቸውን በቀኝና በግራ አሰልፈው ወደ ጦርነቱ ገቡ ። መድፈኞቻቸውም በቀኛቸው በኩል ጠምደው እየተኮሱ በመካከል የሚዋጋውን የጠላት ጦር ይመቱ ጀመር ። ...አቡነ ማቴዎስ ፣ የማርያምን ታቦት አስይዘው ከቀሳውስትና ከመነኮሳት ጋር ሆነው የጊዮርጊስን ሰብሐተ ፍቁርን እያዜሙ ሲከተሉ ዜማው ሳያልቅ ድሉ ተፈጸመ ። ንጉሡ ግን ፣ የሚሸሹትን ኢጣልያኖች እየተከተሉ የሚወጉትን ወታደሮቻቸውን እየመሩ ሲሔዱ ከቀድሞዎቹ እንደላር ቅጠል በጣም የሚበረከቱ ኢጣልያኖችን አግኝተው ሲዋጉ የተዘረሱም መጠን ከፊተኛው የበለጠ ሆነ ። በዚያም ላይ የኢጣልያ ብዙ ጀግኖች ወደቁ ። የቀሩትም ሸሹ ። ...

በዚህን ቀን ፣ ብዙ መነኮሳት የስሌን ቆባቸውን እንደደፉ ብጫ ካባቸውን እንደደረቡ የቆዳ ቀሚስ ለብሰው ፣ ግማሹ ከንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ ግማሹ ከቴጌይቱ ዘንድ የቀሩትም በተዋጊው መኳንንትና ወታደር ዘንድ ሆነው ወዲያና ወዲህ እየተላለፉ ሲዋጋ ወደ ጦርነቱ የሚገባውን እያናዘዙ ፣ ከጦርነቱ ሲሸሽ ያሰበ ሲያገኙ እየገዘቱ ሲያበረቱና ሲያዋጉ ዋሉ ። የኢትዮጵያም ጦር ከጦርነቱ የሸሸውን የኢጣልያን ጦር የራቀውን በጥይት የቀረበውን በጦርና በጎራዴ እየመታ ፈጀው ። ...የመጀመሪያው ጦር በተሸነፈ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ወደፊት እየገፉ ጦር ያነሰበትን ግንባር እየመረመሩ በፍጥነት ጦር እየላኩ ሲያዋጉ ጊዜው 5 ሰዓት ሆነ ። እንደዚህም እያደረጉ ተራራውን ካለፉ በኋላ 2,000 የሚሆኑ ኢጣልያኖችና ባሻ ብዙቆች ባንድ ዋሻ ውስጥ አበጅተው የሚዋጉትን አገኙ ። በዚያን ጊዜ ከበቅሏቸው ወርደው በዋሻውና በምሽጉ ላይ እንዲተኩሱ መድፈኞቻቸውን አዘዙ ። በዚያን ጊዜ በዋሻው ውስጥ ጣልያኖችና ባሻ ብዙቆች እግዚኦ እያሉ ጮሁ ...

የንጉሡ እሽከር ሊቀ መኳስ አባ ተምሳስ ዣንጥላውን እንዳስያዘ* "ውጋ በርታ" የሚለውን ነጋሪቱን ያለማቋረጥ እያስጎሸመ ሲያዋጋ ዋለ ። ይኸንንም ሁሉ ሲያደርግ የምኒልክ ውቃቢ ስለ ጠበቀው እርሱንም የተቀመጠበትንም በቅሎ የመድፍና የጠበንጃ ጥይት አልነካውም ። የመጀመሪያው ድል ወደ ተፈጸመበት ስፍራ እቴጌዪቱ መጥተው ቆመው በእርኮትና በገምቦ ያለውን ወሀና መጠጥ በገረዶች እያስቀዱ ቁስለኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢጣልያኖችም ሳይቀሩ እንዲጠጡና እንዲረኩ አደረጉ ።

9 ሰዓት ግድም ሲሆን ፣ ያፄ ምኒልክ ጦር ቁስለኛና ምርኮ እየያዘ ከጦርነቱ ቦታ መመለስ መጀመሩን ባዩ ጊዜ እቴጌይቱ ፣ "ንጉሡ

*ለዳንቡ በጦርነት ጊዜ ንጉሡ የሚለብሱትን ለብሶ የሚያዋጋና ንጉሡን ከመመታት የሚያድን ሊቀ መኳሱ ነበር ። አሁን ግን ፣ አዛዥ አባ ተምሳስ ይኸን ሥፍራ መያዛቸው ምናልባት ሊቀ መኳስ አባተ ራሴ እዋጋለሁ እንጂ ይኸን ሥፍራ አልይዝም ብለው ይሆናል ።



ሳይመለሱ ወዴት ነው የምትመለሱት? አሁንም ቁስለኞቻችሁንና ምርኮኞቻችሁን ለኔ እየሰጣችሁኝ እናንተ ወደዚያው ተመለሱ" ብለው ጮሁባቸው ። ይኸንንም ትእዛዝ ቢያለበት አስተላለፉ ። ከርሳቸውም ጋር ያሉት እህታቸው ወይዘሮ አዛለች ምርኮ ይዘው የሚመለሰውን ሰው ባየችው ጊዜ ... ፣ "ንጉሥህን ጮማና ጠጅህን ትተህ የምትመለሰው በዓድዋ ቤት አለህን" ... ብላ ለፈፈች ... ። ያፄ ምኒልክ ደግነት ወንዱን ብቻ ሳይሆን ሴቱንም መነኮሳቱንም ሁሉ አጀግነው (ጉበዝ አደረጋቸው) ። በዓድዋ ጦርነት እቴጌ ጣይቱና አብረው የነበሩትን ሴቶች ማድነቅና ማጋነን ይገባናል ። አለሥራቸው ሲሠሩ ውለዋልና ታሪኩን ጽፈን ለመፈጸም አንችልም ።

እቴጌይቱ እንዳዘዙት ፣ ከጦሩ ግንባር የተመለሰው ጦር ምርኮኛውንና ቁስለኛውን እያስረከበ ንጉሡ ወደሚዋጉበት የጦርነት ቦታ ተመልሶ ከተዋጋ በኋላ ፣ "የጠላት ጦር ገና አልተሸነፈምን ምነው ቆዩ ጊዜውስ መጨለሙ አይደለምን" ብለው እንዲመለሱ ሲሉ ፣ አንድ ወታደር እቴጌይቱ ላፄ ምኒልክ ቢልኩ ንጉሡ ፣ "በግራ በኩል ተኩስ እሰማለሁ በዚህ በኩል ግን ሁሉም አልቋል" የሚል ቃል ከመለሱላቸው ወዲህ ወደ ሰፈር መመለስ ጀመሩ ። እቴጌይቱም የንጉሡን መመለስ ሲያዩ ወደ ሰፈር ተመለሱ ። ጊዜው ድንግዝግዝ ያለ ጊዜ ነበር ። እቴጌ ወደ ድንኳኑ በደረሱ ጊዜ እውስጥ ገብተው መከዳ ብቻ ላለበት ዙፋን እጅ ነሥተው ተቀመጡ ...* ዐፄ ምኒልክ ወደ ሰፈር ሲገቡ ግን ጨልሞ ነበር ። ወታደሮቹም ቁስለኛውን በከብት የሞተውን ሬሳ በቃሬዛ አድርገው ወደ ሰፈር መግባት ጀመሩ ። በግራ በኩል ያለው የኢጣልያ ጦር ገና ስላልተሸነፈ ፣ በዚያ በኩል ያሉት ጦረኞች እስከ ሌሊቱ 5 ሰዓት 6 ሰዓት ድረስ ሲገድሉ ፣ ሲማርኩ ቆይተው በኋላ ተመለሱ ። 1

የዚህ የጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ታሪክ ፡ ወታደሩ በእንዴት ያለ ቆራጥነትና ዠግንነት እንደተዋጋ ፣ "ሁሉም ጮማ ሳበላኝ ፣ ጠጅ ሳጠጣኝ ጌታዬ ለምኒልክ እሞታለሁ" እያለ ወደፊት እየገሠገሠ ጠላቱን በመግደል ራሱም ሳገሩ መሠዋቱን ፣ ንጉሠ ነገሥቱም ዋና መሪ ሆነው ጦር ከበዛበት ወደ አነሰበት ወታደር በመቆጣጠር እያደላደሉ ፣ "በዚህ አለፉ ፣ በዚህ በኩል ተዋጉ" እያሉ በጦርነቱ መካከል ተገኝተው ሲያዋጉ መዋላቸውን ፤ በንጉሠ ነገሥቱ ኋላ አቡነ ማቴዎስና ቀሳውስቱ የሚሸሽ ባገኙ ጊዜ ውጊያውን እንዲቀጥል በማዘዝ ሲመልሱት ፣ የቀሩትም መነኮሳት የስሌን ቆብ የደፉ ብጫ ካባ ደርበው ፣ የዳባ ቀሚስ ለብሰው በጦርነቱ መካከል ወዲያና ወዲህ እየተላለፉ የሚሞተውን በማናዘዝ ፣ የሚሸሸውን በመገዘት

*መከዳ ላለበት ዙፋን እቴጌዪቱ እጅ መንሣታቸው ንጉሠ ነገሥቱ ባይቀመጡበትም ዙፋን የተከበረ የሥልጣን ምልክት ነው ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ... ገጽ 261—264 ።

ላገራቸውና ለሃይማኖታቸው ደንባቸው የሚፈቅድላቸውን የአዋጊነትና የመንፈሳዊ አባትነት ሥራቸውን መፈጸማቸውን ያመለክታል ። በጊዜው የነበረው መንግሥትና ሕዝብ ኅብረት አንድ በመሆኑ ፣ በወራሪነት የመጣበትን ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀውን ጠላት ከፉኛ መትቶ አሸነፈው ። ይህም በአፍሪካ አህጉር ከዚህ በፊት ያልተደረገ ድል አድራጊነትን የሚያንጸባርቅ የድል ኮከብ ብርሃኑን በኢትዮጵያ የነጻነት አየር ላይ እንደ ፈነጠቀ ኖረ ።

ከሁሉ በበለጠ ሁኔታ በውጫሌ የውል ክርክር ጊዜ ፣ በፖለቲካው ተግባር ያልተለዩትና በአንቶኔሊና በኢጣልያኖች የወራሪነት ሐሳብ ሲናደዱ ሲቆጩ የቆዩት እቴጌ ጣይቱ ፣ በዚህ በዓድዋ ጦርነት የሠሩትን ሙያ ጽሑፉ አጉልቶ የተናገረውን ተመልክተናል ። ድል ማድረግም ፣ ድል መሆንም የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በመገንዘብ በቅድሚያ ጦርነቱ ሲጀመር ፣ በማኅራታቸው ድንጋይ ተሸክመው ፣ በጉልበታቸው ተንበርክከው እግዚአብሔርን በጸሎት ከለመኑ በኋላ ፣ ቀጥሎ ጦርነቱ ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ ከንጉሠ ነገሥቱ ኋላ ከጳጳሱ ጐን ሆነው ለተጠማ መጠጥና ውሃ እየሰጡ ፣ የቆሰለውን እያሳካሙ ፣ የሚሸሽ ወይም ወደፊት ለመግፋት የሚያወላውል ሲያገኙ ለእቴጌነታቸውና ለቁንጅናቸው መሸፈኛ የሆነውን ዐይነ ርግብ ከፊታቸው ላይ እንሥተው እንደ ወንድ ፣ "ወደፊት ግፋ በለው" እያሉ በጩኸት እየተናገሩ ሲያዋጉ መዋላቸው ፣ ይልቁንም አንዳንድ ወታደር ወይም የጦር አለቃ ተዋግቶ ለጊዜው የማረከውን የጣልያን ወታደር ወደኋላ እርሳቸው ወዳሉበት ይዞ ሲመለስ ፣ "ንጉሡ ሳይመለሱ የት ነው የምትመለሱት ፣ አሁንም ምርኮኞችሁን ለኔ አስረክቡኝና እናንተ ተመልሳችሁ ውጊያውን ቀጥሉ" ያሉት ፣ ለዚህ ጦርነት ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥለው ደንበኛ አሳቢ ትጉኅ መሪና አዋጊ መሆናቸውን እንገነዘባለን ። የጦርነቱ ድል የሚገኘው ጠንክሮ በመዋጋት እንጂ ፣ ጣልያንን ማርኮ በመመለስ አለመሆኑን ተገንዝበው ምርኮኛህን ለኔ ተወው ፣ ጦርነቱን ቀጥል ማለታቸው በአስተዋይነት መምራታቸውን ያስረዳል ። እንደዚህ አድርገው ጠቅላላው ጦር የሚዋጋበትን ሲያስቡ ፣ በተለይ የግላቸው ቁጥሩ ከአምስት እስከ ስድስት ሺ የሚደርሰው ጦራቸው በውስጡ አራት መድፍ ይዞ መዋጋቱም አይዘነጋም ።

በጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጽሑፍ ላይ ፣ "የኋለኛው ሰልፍ እንደ መወዝወዝ (ይኸውም ማለት እንደ ማወላወል) ሲል ባዩት ጊዜ ፣ እቴጌ ቃልዎን አፈፍ አድርገው (ይኸውም ማለት ጮኸው) ተናገሩ ። "እይዞህ አንተ ምን ሆነሃል ድሉ የኛ ነው ብለው አሉት ። ሰዉም የተናገሩትን ቃልና እቴጌን ባየ ጊዜ ሴት ሲያጣና (ሲያበረታ)



ወንድ መሸሽ አይሆንለትምና ጸጥ አለ" ወደፊት በሚነበበው በኢጣልያንኛው ጽሑፍ ላይ ደግሞ ፣ "በዚሁ ጊዜ ተጠባባቂው የ7ኛው ባታዮን ጦር ደርሶ እንድነት ያደረጉት መቋቋም ሐበሾችን ወደኋላ 1000 ሜትር ያህል እንዲያፈገፍጉ አደረጋቸው" የሚለው ተገናዛቢ ነው ። ዐይነ ርግባቸውን ገልጠው ወይዘሮ ዘውዲቱንና ደንገጡሮቻቸውን አስከትለው በኢጣልያኖች መቋቋም የተነሣ የኛን ወታደር ማፈግፈግ ሲያዩ ፣ "ምን ሆንክ አንተ ድሉ የኛ ነው ብለው" ያሉት በዚህ ጊዜ ነው ማለት ነው ። ይህ አንድ መስመር የማይሞላው ኃይለ ቃል እኅታቸው ወይዘሮ አዛለች ወደኋላ በምርኮ ሰበብ ሊመለስ ላሰበው ጦረኛ ወታደር ፣ "ንጉሥህን ትተህ የምትመለሰው ዓድዋ ቤት አለህን" ብለው ከሠነዘሩት ጋር ተባብሮ ታላቅ የድል ፍሬ ካስገኙት ሰበቦች አንዱ ነው ማለት ይቻላል ።

ስለዚህ ፣ በዚህ ጦርነት ከጦር ሠራዊቱ እኩል በየተግባራቸው ተሠማርተው ዘመቻውን የተካፈሉትን የቤተ ክህነት ሰዎች ከአቡነ ማቴዎስ ጋር ፣ ሴቶቹንም ከእቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ጋር በዚያን ጊዜ ባሳዩት መሥዋዕትነት በተገኘው ድል የተጠቀምንና ዛሬ የምንመካ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሁሉ ሳናደንቅና ሳናመሰግን አናልፍም ። እንግዲህ በኛ በኩል የጦርነቱን አዠማመሩን ፣ አካሔዱንና አፈጻጸሙን ከጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ መጽሐፍ ላይ በዚህ ዓይነት ከተገነዘብን በኋላ ፣ በኢጣልያኖቹ በኩል የካቲት 22 ቀን በዋናው ጦርነት ዋዜማ ሲመከርና ሲዘከር ተውሎ ለ23 አጥቢያ ሌሊቱን ተጉዘው ጦርነቱን የዠመሩበትን ሁኔታ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን ።

በዚህ ታላቅ ጦርነት ሽማግሌው ራስ ወልደ ሚካኤል ስሎሞን የነራስ ኃይለ መለኮት አባት ምንም በእድሜ ገፍተው ቢያረጁ የአሽከሮቻቸውን እጅ እንደጨበጡ ይዋጉ ነበር ። እንደርሳቸውም በእድሜ የገፉት በዠግንነት የታወቁት ራስ ደረሶ ምንም እንኳን የጦር አዛዥነቱ ወደ ራስ ወርቄ ቢዛወር ከንጉሥ ተከለ ሃይማኖት አልለይም ብለው መጥተው ጦርነቱን ተካፍለዋል ። ይኸ ሁሉ ያገር አፍቃሪነትንና አንድነትን ያመለክታል ።



ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረሥላሴ
ከሞሪስ ደኮፔ



ከዓፄ ምኒልክና ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በኅብረት የዓድዋን ጦርነት
የተካፈሉት ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ

ከሞሪስ ደኮፔ

# ምዕራፍ ዐርባ

## የኢጣሊያኖች የሌሊት ጉዞ — የግራው አዝማች ጦር መደምሰስ— የአርበኛው ጦር አበጋዝ የፈታውራሪ ገበየሁ አሟሟት — የጄኔራል አልበርቶኒ መማረክ

ማናቸውም ድርጅትና ጥንቃቄ ከተደረገ በኋላ፣ የካቲት 22 ቀን ከማታው በሦስት ሰዓት ከሩብ የጄኔራል አልቤርቶኒ፣ የጄኔራል አሪሞንዲ፣ የጄኔራል ዳቦርሚዳ ጦር ተሰልፎ ከምሽጉ ወጣ። በአራት ሰዓት ተኩል ላይ ተጠባባቂው የጄኔራል ኤሌና ጦር ተከተለ። ዋናው አዝማች ከደጀኑ ጦር ፊት ታጅቦ ይጓዝ ነበር። ከሰፈራቸው ዓድዋ ኢትዮጵያውያን እስካሉበት ድረስ ርዝመቱ 15 ኪሎ ሜትር ስለሆነ፣ ይህ ጉዞ 8 ሰዓት እንደሚፈጅባቸው ገምተው እንደነበረ ባራቲዬሪ ያረጋግጣል። የጦር መኰንኖቹ ጦርነት እያማራቸው አለቅዩው ጄኔራል ባራቲዬሪ በኃላፊነቱ ምክንያት ለጥንቃቄ ሲል የጦርነቱ ጊዜ ወደ ኋላ በመራዘሙ፣ ከማዦር ማልሳ በቀር ጄኔራሎቹም ወታደሮቹም በተለይም በቅርብ ጊዜ ከኢጣልያ አገር የመጡት ሹማምንቶችና ወታደሮች እየተበሳጩ በጄኔራል ባራቲዬሪ ላይ ሲያጉረመርሙበት ነበርና አሁን የናቁትን ጦርነት ለመግጠም ጉዞው በመጀመሩ ሁሉም በልቡ ደስታ እየተሰማው አስቸጋሪውን የሌሊት መንገድ መጓዝ ጀመረ። ምንም መንገዱ ወጣ ገባ፣ በቆዳ ጫማ ለተሸፈነ ለፈረንጅ እግር የማይስማማ ቢሆንም፣ ይህ ሌሊት ሙሉ የጨረቃ ሌሊት ስለነበረ የደስታ መንገዳቸውን ይበልጥ አቃናላቸው።

ከሦስቱ ዋና አዝማቾች አንዱ የግራው አዝማች ጄኔራል አልቤርቶኒ የሦስቱ ጦር ሠራዊት ሳይለያይ እየተጠባበቀ በአቅራቢያ ሆኖ እንዲጓዝ ተብሎ ከበላዩ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ከፕላን ጋር በጽሑፍ የተሰጠውን ትእዛዝ ተላልፎ ወደፊት ገሥግሦ በመጀመሪያ ጦርነት የጀመረ እርሱ ነው። ይኸንን ያደረገበትን ምክንያት፣ ብዙ ጸሐፊዎች በልዩ ልዩ ዓይነት ተርጕመውታል። ግማሾቹ "የአበሾቹን ኃይል በመናቅ ብቻዬን አሸንፋቸዋለሁ ብሎ ነው" ሲሉ፣ ግማሾቹ "በአለቅዩው በባራቲዬሪ ላይ እርሱና አሪሞንዲ ንቀት ስለ ነበራቸው፣ እርሱ ቀደም ብሎ ከአበሾቹ ጋር ተዋግቶ የድል አድራጊነትን ዝና ለግሉ

ለማስቀረት ነው"[1] ብለዋል የቀሩት ደግሞ ፤ "የሥስቱ አዝማቾች አቅጣጫ የጉዞ መሥመር ለየብቻ በመሆኑ ወጣ ገባውን መንገድ በዝር ዝር ባለማወቅና የሌሊት ጉዞ በመሆኑ የጦርነት ጓደኞቹ ወደኋላ መቅ ረታቸውን ሳይገነዘብ ፣ ወደፊት ቀድሞ ጦርነቱን በስሕተት ጀመረ" ይላሉ ። የሆነ ሆኖ በርሱም አሳቦ ፤ "በኢትዮጵያውያኑ ጦር ላይ ድን ገት ደርሼ አደጋ አደርሳለሁ" ሲል ፣ እነርሱ ደግሞ አስቀድመው ወሬ ውን እንደ ሰሙት ተጠባብቀው እንደ ተቀበሉት የታወቀ ነው ።

የርሱን ጉዞና የጦርነቱን አኳኋን የታወቀው ደራሲ ኮንቲ ሮሲኒ ከጻፈው ላይ ዋና ዋናው የሚከተለው ነው ።

የአልበርቶኒ ጦር ከሰፈሩ ደንበኛ ጉዞውን ጀመረ ። ለርሱም መሪ የሚሆኑ ከጠቅላይ አዛዡ የተሰጡት 6 ያገር ተወላጆች ሲኖሩ 7ኛውና 8ኛው ደግሞ የአልቤርቶኒ ልዩ ታማኞች ነበሩ ። ከነርሱም ጋር ስፍ ራዎችንና መንገዶችን ደህና አድርጎ የሚያውቀው ፊታውራሪ አይኩን የሚባለው ባንዳ አብሮት ነበር ።

. . እስከ ገንደብታ ድረስ በቀላሉ ከተጓዘ በኋላ . . በ9 ሰዓት ተኩል ከአሪሞንዲ ጦር ጋር ተገናኘ . .

የአሪሞንዲ የነጭ ወታደር ባስቸጋሪው መንገድ እንደልብ ስላ ልተራመደ ፣ ያገር ተወላጅን ጦር የያዘው አልቤርቶኒ ወደፊት በግሥጋሴ ደርሶ እንዲይዝ በፕላኑ ተወስኖ የነበረውን ስፍራ አሳሳተ ።. . . በፕላኑ ላይ የኤራራ ጉብታ በማለት ፈንታ ኪዳነ ምሕረት ተብሎ ተመ ልክቶበት ስለነበረም ስሕተቱ ተፈጠረ ።. . . ሌሎቹን እንዳይቀድም ክበላይ ትእዛዝ እያለው ከሌሎቹም የጦር ጓደኞቹ ለመገናኘት ፈጣ ኖቹ ያገር ተወላጆች መልከተኞች እያሉት ፣ እንደዚሁም በግራው በኩል በማርያም ሸዊቶ ላይ የጠላት ጦር መኖሩን ሰምቶ ሳለ ፣ ይኸንን ሁሉ እያወቀ ችላ ብሎ ወደፊት የገፋበትን ምክንያት ማወቅ ችግር ነው ። ኤራራ በደረሰ ጊዜ ጠላት በፍጹም በዚህ ስፍራ አልነበረ በትም ። የኤራራን በር አልፎ በምዕራብ በኩል ጦሩ አሽቀለቀለ ። መንገዱ መጥፎ ከመሆኑ የተነሣ ፣ አንዳንድ ጊዜ ተቀጣጥሎ እያንዳ ንዱ ሰው ከመሔድ በቀር ሁለት ሰው ጐን ለጐን ሆኖ ለማለፍ አይ ችልም ነበር ። በዚህም የሌሊት ጉዞና በመጥፎ መንገድ ከገር ተወ ላጅ ወታደር ጋር አብሮ መራመድ ያቃታቸው የነጮች ወታደሮች ነበሩ ። ይሁን እንጂ ፣ እነሱም ችግሩን አልፈው ወደ ተመደበው ስፍራ በደስታ ለመድረስ ቻሉ ።. . . እንደዚህ ሆኖ የጦሩ ጫፍ ከሌሊቱ 5:30 (በዐሥራ አንድ ሰዓት ተኩል) አዲ በቂ በር ላይ ደረሰ ።. . . እዚያም ላይ ሆኖ ጄኔራል ባራቲዬሪ በስሜን ምዕራብ የሚገኘውን ዓድዋን በስሜን ያለውን መነኩሴቶን በደቡብ ያለውን ስንደዶን

1 Ventitre anni di vita Africana, G.Pantano, Chap. VII.



ተመለከተ ። መሪዎቹም በደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኘውን የጐስ ሶን በሰሜን በኩል ያለውን የእንዳ ኪዳነ ምሕረትን ጉብታ አመለ ከቱት ።

በዚህም ሳለ እኋላ የነበረው ጦሩ በሙሉ ከተተ. . . ከዚያ የኪ ዳነ ምሕረት በር አልተያዘም ነበርና በዚህ ምክንያት አልቤርቶኒ ተቆጣ ።. . . ከዚያም ወደ መነኩሴይቶ ጉብታ ላይ ወጥቶ ሐበሾቹ ያሉበትን የሻዊቶን ሰፈር ይቃኝ ጀመር ። . . . ከዚያ መውረድ ሲጀ ምር የተኩስ ድምፅ ስለተሰማ ግንባር ቀደም ሆና የተላከው የማዦር ቱሪቶ ጦር ከጠላት ጋር መታኮስ መጀመሩን ተረዳ ።. . . ከቱሪቶ ጋር የገጠመው የጠላት ጦር ቁጥሩ አምስት ወይም ስድስት ሺ ይሆናል ። ለነዚህም ከሰሜን ወደ ደቡብ እየመጡ ተጨመሩላቸው ። ማዦር ቱሪቶ በዚህ ጊዜ የባታዮውን ጦር በሙሉ አሰልፎ ሲነጋ 6:10 (ዐሥራ ሁለት ሰዓት ከዐሥር ደቂቃ) ላይ ጦርነት ተጀመረ ። ከሐበሾቹ ወገን ተዋጊዎቹ የራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ የዋግሹም ጓንጉል ሰዎች ነበሩ ። ለነርሱም በፍጥነት የሰሜኑ የደጃች ገሠሠና የበጅሮንድ ባልቻ ጦር ደረሰላቸውና ጦርነቱ ከሁለቱም ወገን ተፋፋመ ። ማዦር ቱሪቶም እርዳታ እንዲደርስልኝ ሲል ሌተና ሳርቤሪስን ወደ ጄኔራል አልቤር ቶኒ ላከው ። መልክተኛውም ሲሔድ በመንገድ ወሬ ለመጠየቅ ከአል ቤርቶኒ ከተላከው ከካፒቴን ባሲ ጋር ተገናኘ ። ባሲም ከርሱ ጋር ሆኖ ሁለቱም ወደ ጦርነቱ ተመለሱና እስከ መጨረሻ ተከላከሉ እያሉ ወታደሮቻቸውን ግማሽ ጦር ወደ አባ ገሪማ ፣ ግማሹንም በቀኝና በኋላ ቢታትነው ከቢ እንዳይደረግባቸው አደረጉ ።

ስለዚህ በሐበሾቹ ላይ ድንገት አደጋ ጥለን እናስደነብራለን ተብሎ የነበረው እሳብ ሳተ ። ባራቲዬሪ ለጦርነት መምጣቱ ወሬው በሐበ ሾቹ ዘንድ እንዳይሰማ ምንም ቢጣጣር ፣ በሐበሾቹ ሰፈር የጦርነት ግንጋኔ እንደነበረ ነው ። ይሁን እንጂ በዚህ ቀን የጊዮርጊስ በዓል ስለነበረ ፣ ብዙ ወታደሮች እያስፈቀዱ ገና በዋዜማው ወደ አክሱም ሔደው ያስቀድሱ ነበር ። ነገር ግን በዚሁ ንጉሡ ባሉበት በዓድዋ ሰፈር "በያላችሁበት ተጠንቀቁ" የሚል ለፋፊ በየሰፈሩ ይሰፍ ነበር ። ሌሊቱን በጉዞ ላይ ታማኝ መሪ ሆኖ ከ6 ሰዎች ጋር የተቆጠረው ያገር ተወላጅ ሰውዬ ጠፋ ።* 1 የቦታው ሹም ፊታውራሪውም በዚሁ ሌሊት እንደጠፉ አልቤርቶኒ አረጋግጧል ።. . . ከልዩ ልዩ ምንጭ እንዳ ገኘሁት ከሐበሾቹም ጽሑፍ እንደ ተረዳሁት ጦርነቱ ሲጀመር ዐጼ ምኒልክ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ራስ መኰንን ፣ ራስ መንገሻ አቲከም ራስ (ፊታውራሪ) ገበየሁ ሌሎችም ብዙ አለቆች ከሌሊቱ ከ4 (ከ10 ሰዓት) ጀምረው ዓድዋ በሚገኘው በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ያስቀድሱ ነበር ። ቀዳሹም አቡነ ማቴዎስ ነበሩ ። እርሳቸውም በሚቀድሱበት ጊዜ ክፍት በሆነው በር በኩል የጦርነቱ ተኩስ ወደ

*የመሪዎቹንና የጠፉውን መሪ ስም በዝርዝር አይናገርም ። ነገር ግን መርተው በኋላ የጠፉት ባሻ እውዓሉም መሆናቸው ነው ። በጠፉ ጊዜ የጦሩ መሪ "እውዓሉም እውዓሉም" እያለ ቢጣራ "ዘወዓልከዮ እያውዕለኒ" በዋልክበት እያውለኝ ብለው መለ ሱለት ይባላል ። 1 የእቴጌ ጣይቱ እጭር የሕይወት ታሪክ ፣ ታደሰ ዘወልዱ ፣ ገጽ 25 ።

ውስጥ እየገባ ተሰማ ። ወዲያው ተመልሰው የኢጣልያኖችን መምጣት ተናገሩ ። በዚህም ጊዜ ምኒልክ የድንጋጤም ፣ የመበርገግም መልክ አልታየባቸውም ይባላል ። በጸጥታ ቆመው ጥቂት ደቂቃዎች እንደቆዩ ወደ አቡነ ማቴዎስ ጠጋ ብለው ትንሽ ንግግር ከተለዋወጡ በኋላ ተመልሰው እስፍራቸው ቆሙ ። ከዚህ በኋላ አቡነ ማቴዎስ በቀኝ እጃቸው መስቀላቸውን ከፍ አድርገው ይዘው በዚያ ላሉት ሁሉ እንደዚህ ብለው እስተዛዝነው ለቅሶ ጭምር ተናገሩ ። "ልጆቼ ሆይ ዛሬ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚፈጸምበት ቀን ነው ሒዱ ለሃይማኖታችሁና ለንጉሣችሁ ሙቱ ኃጢአታችሁም ይሰረይላችኋል (እግዚአብሔር ይፍታ)"

አቡኑ ይኸን ተናግረው ሲጨርሱ ፣ መኳንንቱ ሁሉ እየተሽቀዳደሙ የአቡኑን መስቀል ተሳልመው ከወጡ በኋላ ፣ እያንዳንዱ በችኮላ ወደየሰፈሩ ሔዶ በሰፈርም የነበረው የጦርነቱን መጀመር ሰምቶ እመዘጋጀት ላይ ነበር ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ብቻ ቁርባን ለመቀበል ሊቆዩ አሰበው ነበር ። ነገር ግን ፣ ዐፄ ምኒልክ ኃጢአትዎ ወርዷል ፤ ይልቅስ እዚህ መቆየት አደጋ ነው ስለአሏቸው እርሳቸውም ወጥተው ሔዱ ። በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ምኒልክ ብቻ ቆዩ ።

ማዦር ቱሪቶ የያዘው የኪዳነ ምሕረት በር ዓድዋ ለሰፈረው ለዋናው ለሸዋ ጦር ወለል ብሎ ይታየው ነበር ። . . . የኢጣልያን ጦር መምጣቱን ሲያረጋግጡ የንጉሡና የራስ ሚካኤል ጦር ደግሞ ፡ በግራ በኩል ለመክበብ ወደ ኪዳነ ምሕረትና ወደ አባ ገሪማ ጉብታ ተጓዘ ። ደጃች በሻህም ፈረሰኞቻቸውን ይዘው በጐን ጫፍ ቀደሙ ። አጋማሹ የራስ መንገሻ ጦር በቀኝ በኩል ወደ ማይ አጋም ዘልቀው በዠርባ ሊመጡ ነበር ። ነገር ግን ዘባን ቀይህ ሲደርሱ በዘዴ ቀርቶ ወደ ዓድዋ ወደ ማርያም ሸዊቶ የሚያሳልፈውን የረቢ አሪዬኒን መንገድ . . . እንዲይዙ ታዘዙ ። የንጉሡም ጦር ከዓድዋ መጥቶ የዘባን ቀይህን ስፍራ ይዞ ከቆየ በኋላ ፣ ማይ አጋም ወጥቶ ከአልቤርቶኒ ጦር ጋር በማርያም ሸዊቶ ከጄኔራል ዳቦርሚዳ ጦር ጋር ውጊያው ተጀመረ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ጄኔራል አልቤርቶኒ ያለበትን ሁኔታ ለማስታወቅ ለጄኔራል ባራቲዬሪ እንደዚህ ሲል 6፡30 (በ12 ሰዓት ተኩል) ላይ ጻፈ ። "ጠላት ሳያውቅ የኪዳነ ምሕረት በር በ11 ሰዓት ተያዘ ። ጠላት በዓድዋ ዙሪያና በማርያም ሸዊቶ ይገኛል ። የአንደኛው ባታዮ ጦር (ቱሪቶ) ከበሩ አልፎ ወደፊት ዘልቆ የተፋፋመ ጦርነት እማድረግ ላይ ነው ። እርሱንም በመርዳት ባንዶች አብረው ይዋጋሉ ። 6ኛው ባታዮ በቀኝ ያለውን ተራራ ይዟል ። የቀሩት ሁለት የባታዮ ወታደሮች መድፋቸውን እንደያዙ ተሰብስበው ይጠባበቃሉ ። ትልቅ ጦርነት ሊደረግ የቀረበ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ይሰማኛልና የአሪሞንዲ ጦር ተቆጥኖ ይድረስ ። ግማሹንም የጠላት ጦር እንዲይዝልን የዳቦርሚዳ ጦርም ወደፊት ቢገሠግሥ መልካም ነው ። "ጄኔራል አልቤርቶኒ መልክቱ በ7፡30 (በአንድ ሰዓት ተኩል)እንደሚደርስ አስቦ ነበር ። ነገር ግን ለባራቲዬሪ የደረሰው ከ8፡30 (ከሁለት ሰዓት ተኩል) በኋላ ነው ።

ግንባር ቀደም ሆኖ ጦርነቱን የጀመረው የማዦር ቱሪቶ ጦር ፣ በጥይትና በመድፍ አንዳንድ ጊዜ በሳንጃ የጨበጣ ውጊያ አድርጎ



ሐበሾቹ ስለአየሉ ፣ ግማሹ እየሞተ የቀረው ሊማረክ ሲቀበል ፣ ከዚያ የተረፈው በዚሁ በቱሪቶ እየተመራ ወደኋላው ሸሽቶ ወደ ዋናው ወደ አልቤርቶኒ የጦር ሰፈር ደረሰ ። . . . የአበሾቹም ጦር እየተከታተለ ደርሶ ዋናው ጦርነት ስለ ተጀመረ ፣ ጄኔራል አልቤርቶኒ የቀረው በመድፍና በጠበንጃ በሚዋጋበት ጊዜ ሻርፕኔል የሚባለው የሚፈነዳ ቦምብ እንዲተኮስ አዘዘ ። ይኸንንም ማድረጉ ሐበሾቹ በዚህ ተዠስ ድንጋጤ እንዲሸበሩ ነው ። በዚሁ ጊዜ ሐበሾቹ 1500 ሜትር ካሬ የሚሆን ቅርበት ያለውን ስፍራ ይዘው አንድ አንድ ጊዜ 1000ሜትር ተጠግተው ሲዋጉ በዚሁ ቦምብና በመድፍ ብዙ ሰው አለቀባቸው ። ወደኋላም ማፈግፈግ ሲጀምሩ ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ ለአልቤርቶኒ የጻፈው መልስ መጣለት ። ደብዳቤውም የሚገልጸው የአሪሞንዲ ጦር . . . በረቢ አሪዬኒ ተጠባባቂው ጦር በገንደብታ መገኘቱን ነው . . . በዚህ መካከል የአላጌን በር የሰበረው ፊታውራሪ ገበየሁ ጦሩን ይዞ ለወታደሮቹ ምሳሌ በመሆን እፊት ሆኖ እየመራ በግሥጋሤ ወደ ጦርነቱ ገባ ። ከርሱም ጋር ሦስት ወይም አራት ሺ የራስ ሚካኤል ፣ ሦስት ሺ የፊታውራሪ ተክሌ አንድ ሺ አምስት መቶ የፊታውራሪ ተፈሪ ጦር ደረሰ ። ከዚህ በኋላ በሁለቱ መካከል የሚደረገው ጦርነት ከልክ ያለፈ የጋለ ሆነ ። ከሁለቱም ወገን በኋላ የነበሩት እፊት ሆነው ለጀመሩት እየደረሱላቸው የብዛት ውጊያ ሲደረግ የጥይቱ ጩኸት አስደናቂ ነበር ። . . . ከኢጣልያኖቹ ወገን እያንዳንዱ ወታደር 142 ጥይት ብቻ ይዞ ነበርና* ጥይት በማለቁ የመሸነፍ አደጋ እንዳይደርስና ሌላ ጥይትም በቅርቡ ለማግኘት ስለማይቻል ፣ ሹማምንቶቹ ወዲያና ወዲህ እያሉ እየቆጠቡ እንዲተኩሱ ለየወታደሩ ትእዛዝ ይሰጡ ነበር ።

የሐበሾቹ ጦር ከመካከለኛው ፀቀር በግራ በኩልም ስለ ተጫነ ጄኔራል አልቤርቶኒ ተጠባባቂው ባታዮ እንዲመጣ አዘዘ ። በዚሁ ጊዜ የእቴጌ ጣይቱ ጦር ስድስት ሐኪንስ **የሚባሉትን መድፎች ይዘው ከተዋጊው 3,000 ሜትር ርቀው መድፍ እየተኮሱ ምንም እንኳን በጣልያኖቹ ላይ ጉዳት ባያበዙ ተዋጊዎቹን ሐበሾች ስለ ደገፏቸው ወደፊት ሁሉም በኪዳነ ምሕረት በር በላጸት እየገፉ ይዋጉ ጀመር ። በዚሁ ጊዜ ተጠባባቂው የ7ኛው ባታዮ ጦር ደርሶ እንድነት ያደረጉት መቋቋም ሐበሾቹን ወደኋላ 1000 ሜትር ያህል እንዲያፈገፍጉ አደረጋቸው ።

በዚህ ዓይነት ፣ ተዋጊው የጦር ሠራዊት ወደፊት ለመግፋት እንዳመነታ ባየ ጊዜ ፣ ቀይ ልብስ የለበሰው ፊታውራሪ ገበየሁ ወደ ሰዎቹ ፊቱን አዙሮ . . . "የአምባ አላጌው አሸናፊ ፊታውራሪ ገበየሁ በምን አኳኋን እንደሞተ ወደ ሸዋ በሕይወት የሚመለሱት ይናገሩ" ብሎ ተናግሮ ፣ እንደ አንበሳ ተወርውሮ ወደ ኢጣልያኖቹ መስመር ገብቶ ሲዋጋ ፣ በ3 ሰዓት ላይ በመትረየስ ተመትቶ ኪዳነ ምሕረት አበሩ

---

* በፊተኛው ላንድ ወታደር የተሰጠውን 112 ጥይት ብሎ የነበረውን አሁን 142 አድርጎታል ።

** Hotcaiss 6 Benjamin Berkley. የመድፍና መትረየስ ሥራን ያመነጨ ሰው ነው ። በፈረንሳይዮች በኩል ወደ ኢትዮጵያ የመጣው መድፍ በርሱ ስም ይጠራል ።

ላይ ወደቀ ። የርሱም ሞት የርሱን ሰዎች አስደንግጦ ወደኋላ እንዲ
ያፈገፍጉ አደረጋቸው ። ግማሾቹ ግን ፣ ተኩሳቸውን ሲቀጥሉ ሳለ የነ
ርሱ የመድፉም ተኩስ ለጊዜው ዝም አለ ።

አልቤርቶኒ ድሉ እንደ ተቃረበ ተስፋ አደረገ ... ነገር ግን
በዚህ ጊዜ ወደ ጦርነቱ ግንባር የመጡት ዐፄ ምኒልክ ያደፋፈሩአ
ቸው ወታደሮች ወደፊት እየገፉ መጥተው እንደገና ሲጀመር ጦር
ነቱ ከፊተኛው የበለጠ ሆነ ... ይልቁንም በሦስት ሰዓትና በሦስት
ሰዓት ተኩል መካከል አበሾቹ ሁለት ጊዜ እየገፉ የመጡትን የ7ኛው
ባታዮ ጦር እያገደ አቆማቸው ። ቀጥሎም ከ8ኛው ባታዮ ጦር ጋር
ሆነው የጨበጣ ጦርነት ሆኖ ትልቅ እልቂት በተደረገበት ሰዓት ከነ
ጮቹ በቀር ያገር ተወላጅ ባንዳና የሱዳን ተወላጆቹም በጉብዝና
ተዋጉ ። እነርሱንም ካፒቴን ፒያንኪኒ ፡ "ጉበዞች ደህና እንደዚህ
በጸጥታ አነጣጥሩና ተኩሱ ። ያለዚያ ጩኸት ብቻ ይሆናል" እያለ
እያነጣጠሩ በጠላት ላይ ደህና አድርገው እንዲተኩሱ ያሳያቸው
ነበር ። ቢሆንም ከሦስት ሰዓት ተኩል በኋላ ሁኔታው እየከፋ
ሔደ ። ከአባ ገሪማ የወረዱት ወደ ጦርነቱ እየቀረቡ ባደረጉት
ውጊያ ከኢጣልያኖቹ ወገን በቆራጥነት በመድፍም ፣ በጠበንጃም በሳ
ንጃም ቢከላከሉ የሐበሾቹ ጦር እየበዛ ሔደ ። ጄኔራል አልቤርቶኒም
ተጠባባቂ ጦር ለማዘጋጀት ካፒቴን ባሲን ወደየባታዮዎቹ ቢልክ
ሁሉም ተደባልቆ ስለሚዋጋ ለተጠባባቂ የሚሆን ሰው አለመገኘቱን
ነገረው ። ጦርነቱም በዚህ ዓይነት ቢቀጥል ጥይት እንደሚያልቅና
ለረዥም ጊዜ ለመመከት አለመቻሉን ተረዳው ። ካገር ተወላጅ ጦር
ውስጥ ባለበት ግንባር ብዙዎቹ አለቁ ። በነርሱ ይተኩስ የነበረው ጠበ
ንጃና መድፍም ስለተረፈ ፣ በነርሱ ፈንታ ነጮቹ እየተተኩ ተኩሱን
ቀጥለው ነበር ። ዳሩ ግን ሁሉም ከንቱ ሆነ ። ሬሳና ቁስለኛ ማንሣም
ስላልተገኘ ስፍራው በሬሳና በቁስለኛ ተሸፈነ ። የጦር መሣሪያውም
አለቀ ። በዚህ ጊዜ የባታዮው የልፍኝ አስከልካይ ካፒቴን ባሲ ወደ
ጄኔራል አልቤርቶኒ ጠጋ ብሎ ፣ "ጌታዬ ጄኔራል ምን ማድረግ
ይሻላል!" ብሎ ጠየቀው ። ጄኔራሉም "የባታዮዎቹ ጦር አልቋል ከኋላ
የነጭ ወታደር እርዳታ ይደርስልናል ብለን ተስፋ የለንም ። እዚህ ካሉት
ጋር ወደኋላ እንሸሽ ማለትም ከንቱ ነው ። ስለዚህ ሁላችንም እዚሁ
ቀርተን እንሙት" ብሎ መለሰለት ። እንደዚህ ሆኖ የኢጣልያኖች ጦር
ወደመሸነፍ በቀረበበት ጊዜ የሐበሾቹ አለቆች ተጠጉ ። ንጉሡና ቀዩ
ዣንጥላቸው በሩቁ ታየ የሚሉ ወሬ ተወራ ። በዚህ ጊዜ የ7ኛው
ባታዮ ጦር ካገር ተወላጅ ሹማምንት ጋር ሽሽት ጀመረ ። እነ
ርሱንም እየተከተለ ሁሉም ሽሽቱን ያዘ ... ጄኔራል አልቤርቶኒም
በማዦር ጋሜራ ግማሾቹን ባንዶች ይዞ ከርሱ ለየት ብሎ ወደ አን
ዲት ጉብታ ለመውጣት ሲሞክር ፣ አልቤርቶኒ ከጥቂት ባንዶች ጋር
እንዳለ ሐበሾቹ ሊከቡት ሲፈልጉ ከርሱ ጋር የነበሩት ባንዶቹ ከፊቱ
እየተበታተኑ መጥፋት ጀመሩ ። ጄኔራል አልቤርቶኒ ከትናንት ማታ
ጀምሮ አንድ ጊዜም ከፊቱ ካልተለየው ከፊታውራሪ አይኩን ጋር
ብቻውን ቆሞ ነበር ። ፊታውራሪም እንዲሸሽ ጄኔራሉን ቢጐተጉተው
ዝም ብሎ ቆመ ። በዚህ ጊዜ ጋሜራም በሩጫ ሔዶ አሁን ጊዜ እያለው
እንዲያመልጥ ቢጐተጉተው ፣ "አባክህ አንድ የምትገድለኝን ጥይት
እየጠበቅሁ ነበር አልመጣ አለችኝ" ብሎ መለሰለትና ዝም ብሎ



እፈረሱ ላይ ሆኖ ይመለከት ነበር ። በኋላ ግን ፣ ከፈረስ ወደ በቅሎ
ተዛውሮ ማዦር ጋሜራን ለመፈለግ በበቅሎ ሆኖ ወደ ዘቅዛቃ ስፍራ
ሲተላለፍ የተቀመጠበት በቅሎ በጥይት ተመትቶ ወደቀና እርሱም
አብሮ ወድቆ ሲንከባለል ጠላቶቹ ደርሰው ማረኩት ። በዚህም አኳኋን
የድብልቅልቅ ጦርነት ከተደረገ በኋላ በዚሁ ጊዜ ጋሜራንም ይኸን
የመሰለ አደጋ አገኘው ። እስከዚህ ጊዜ ቆይተው የነበሩት የኢጣልያን
ሹማምንቶች በውጊያው ላይ አለቁ ።... ካፒቴን ቢያንኪኒ ሆዱን
ተመትቶ ወደቀ ። ቲኔንቲ ባሬቲ ጕሮ ግንዱን ተመትቶ በወደቀ ጊዜ
ጓደኛውን ኮርዲላን ፡ "በሰማይ ላይ እንገናኝ" ብሎ ተናግሮ ሞተ ።..
ስለዚህ በግራ በኩል የተረፈው የኢጣልያ ጦር በሙሉ ተከበበ ።

የሐበሾቹ መኳንንቶች የጦር ልብሳቸውን ለብሰው ጦርና ጠበንጃ
በያዙ ወታደራቸው ታጅበው ሲመጡ ፣ ሊቀ መኳስ አባ ተምሳስ ነጋሪ
ቱን ውጋ ውጋ እያሰኘ ወደፊት የሚገሠግሡትን ጠላቶቹን ለማገድ
ሲዋጋ ዶ ርዛ "ሒድና ለመከላከል አልቻልሁምና ወደኋላዬ እንድመ
ልስ የእግረኛ ጦር ላክልኝ" ብሎ መልቲዶን ወደ ጄኔራል አልቤርቶኒ
(ያልተማረከ መስሎት) ሲልክ ፣ በዚያው ሰዓት የራስ መንገሻ አቲከም
ወታደሮች በጌታቸው እየተመሩ ሳይታሰብ በጀርባቸው በኩል ጦራ
ቸውን እየሰበቁ ሰይፋቸውን እያወዛወዙ እየተጯጯሁ ደረሱባቸውና
አመትረየስ ተኳሾቹ ላይ ወደቁባቸው ... ካፖራል ሳልቶ የሚባለው
መሐል እራሱ እሁለት ተፈልጦ ወደቀ ፣ ትረፒፒ ክፉኛ ቆስሎ ወደቀ ፣
ሌተና ኮርዲላ በጨበጣ ሲዋጋ ቆስሎ ተማረከ ፣ ካፒቴን ማዘቶ ቀኝ
እጁን ስለቆሰለ ፣ በግራ እጁ በሽጉጥ ተታኩሶ ሞተ ። ሌተና አይኒስ
መትረየሱን እንደ ጨበጠ በሰይፍ በትር ሞተ ። ሌተና ሳያ በሁለት
ጥይት ቅልጥሙን ተመትቶ ሳለ ድጋሚ ጭንቅላቱን ተመታ...
ማዦር ዶርዛ በሚያስደንቅ ጸጥታ እጁን እኪሱ ውስጥ እንዳደረገ
በመትረየስ ሲያዋጋ ቆይቶ ከሟቾቹ ጋር ወደቀ ...ከሐበሾቹ ወገን
የሞቱትም ብዙዎቹ ናቸው ። ደጃች ጫጫ የሚባለው በጣም ጀግና
የሆነው የጕላ* አገረ ገዥ በዚሁ ስፍራ ሞተ ። እርሱም እንደ ብዙዎቹ
ጀግኖች ታዝኖለታል ። ... 1

በጄኔራል አልቤርቶኒ የሚመራው ግንባር ቀደም ጦር ፡ በዚህ ዓይ
ነት ተሸንፎ ማለቁን ኮንቲ ሮሲኒ ፡ ከፖሌራ ፣ ከባራቲዬሪ ፡ ከቤላቪታ ፡
ከጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ መጻሕፍት እየቀሰመ በዝርዝር
የጻፈው በዚህ ዓይነት ይጨርሳል ። ኢጣልያዊ ጸሐፊ እንደመሆኑ ፡
ጦርነቱን ኢጣልያኖቹ በጀግንነት እንደምን እንደመከቱ ፡ እያንዳንዱ
የጦር መኰንን በጀግንነት መሠዋቱን ሲገልጽ ከውስጣቸው እጃቸውን
እየሰጡ የተማረኩትን ግማሹ ጦር ማለቁን እያየ ወደኋላ የሸሹትንም
እዚህ ምዕራፍ እምብዛም ዘርዝሮ አልገለጸውም ። ቢሆንም በመጨ
ረሻው ላይ ግን ፣ የሞቱትንና ከጦርነቱ እየሸሹ ወደ አሥመራ የገቡትን

* ጕላ ፡ በአንኮበርና በአሳግርት መካከል የሚገኝ የሸዋ ወረዳ ነው ።

1 Italia ed Etiopia, Conti Rossini, PP.361-381. The Campaign of Adwa ..., G. Berkeley,Chap. X,PP 272-313. La Prima Guerra d, Africa, R. Battaglia. PP. 733-776.

ከነቁጥራቸው ገልጾታል ። የኢጣልያኖቹን እያጋነነ ከነስማቸው ሲያ
ነሣ ፣ የኢትዮጵያን ወገን ከፊታውራሪ ገበየሁና ከደጃች ጫጫ በቀር
እምብዛም አልዘረዘረም ። የዚህም አንዱ ምክንያት ኢጣልያዊ ጸሐፊ
በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ፣ በሥፍራውና በጊዜው ስለሌለበት ከሐበሾቹ
ውስጥ እነማን በጀግንነት እንደሞቱ ስማቸውን እየጠቀሰ ሊተ
ርክ አይችልም ። የተዋጉት የኢጣልያ ሹማምንቶችም ፣ የጠላቶቻቸውን
የኢትዮጵያውያኑን ስምና ሥራ በዝርዝር ስለማያውቁ ፣ ቢያውቁም በዚ
ያን ዘመን አብዛኛዎቹ ጽፈው ስላላስቀሩት ፣ የኛም ወገኖች ዘርዝር
በያይነቱ የመጻፍ ልምድ ስለሌላቸው ፣ ብዙ አስደናቂ ጀግንነት የሠሩት
ተራ ወታደሮች ፣ የበላይና የበታች አለቆች የብዙዎቹ የጀብዱ ሥራቸ
ውም ስማቸውም እንደ ተቀበረ ቀርቷል ። ቢሆንም የመጀመሪያውን
ግንባር ቀደም ጦር የተዋጉት ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ዋግሹም ጓን
ጉል ፣ ራስ መንገሻ አቲከምና ደጃች ገሠሠ ፣ በጅሮንድ ባልቻና ፊታው
ራሪ ገበየሁ ፣ ደጃች በሻህና ደጃች ጫጫ ፣ አዛዥ አባ ተምሳስ መሆ
ናቸውን ፣ ከነዚህም መካከል በተለይ ሁለቱ ታላላቅ የጦር አለቆች
ፊታውራሪ ገበየሁና ደጃች ጫጫ በዚሁ ጦርነት አስደናቂ የጀብዱ
ሥራ እየሠሩ መሞታቸውን ትውልዱ ኢጣልያዊ የሆነው የኢት
ዮጵያን ታሪክ የሚያውቀው ኮንቲ ሮሲኒ ሳይደብቅ ገልጾታል ።
በአጻጻፉ ከሁለቱም የፊታውራሪ ገበየሁ አባ ጎራን አሟሟት ፣
"ከፊት ያሉት ጭፍሮቹ የማመንታት መልክ ሲታይባቸው ፣ ከኋላ
እንደ አንበሳ ተወርውሮ በጠላቶቹ ሰልፍ ገባ " የሚል ቃል ጨምሮ
አድንቆ ጽፎላቸዋል ። ሌሎቹም የጦርነቱን ማስታወሻ የጻፉ የኢጣልያ
መኰንኖች የጀግናው ሬሳ የማዕረግ ልብሱን እንደ ለበስ ወደኋላ ሲመ
ለስ ፣ በምርኮኝነት ተይዘው የነበሩት የኢጣልያ ሁለት የመቶ አለቆች
ጉልዮልሞ ፒኒና ቱዞ ማየታቸውን ገበየሁም ከንጉሡ የጐበዛዝት የጦር
አለቆች ውስጥ አንዱ መሆኑን በማስታወስ ገልጸዋል ።[1]

በዚህ ጦርነት ፣ የራስ መኰንንን ወሳኝ አወጋግ ኮንቲ ሮሲኒ እምብ
ዛም አላገነነውም ። ነገር ግን ፣ ምንም እንኳን ራስ መኰንን የዘመ
ቱበት አቅጣጫ በመነኩሲቶ ግንባር ቢሆንም ፣ በፊታውራሪ ገበየ
በኩል የኢጣልያ ጦር በጣም መጫኑን በመገንዘብ የማሀሉ የ
ሪሞንዲ ጦር ለአልቤርቶኒ የደረሰ እንደሆነ አደገኛ ሁኔታ
እንዳይፈጠር ሲሉ ካሉበት ሠፈር ወደቀኝ በኪዳን ምሕረ
ጉብታ በኩል ተቀልብሰው ከአልቤርቶኒ ጦር ጋር በስ
በኩል ሲዋጉ ቀኝ እጃቸውን ተመትተው ወደቁ ። ያቆስላቸውን

---

1 Adua,E. Bellavita, P 354. Gli Italiani in Africa. Angelo Del Boca, p
656-692. La Prima Guerra d' Africa R.Bataglia pp. 733-776.



የኢጣልያ መኰንን ልጃቸው ተኛዝማች ይልማ ተኩሰው መግደላ
ቸውን ፣ መኰንንም ከወደቁበት ተነሥተው ቁስላቸውን አስረው
ጦርነቱን መቀጠላቸውን ግራጌታ ኃይለ ጊዮርጊስ በግዕዝኛ ጽሑፍ
ቸው ያመለክታሉ ።[1]

የሆነ ሆኖ ፣ የጦር አበጋዙ የፊታውራሪ ገበየሁ መሞትና የራስ
መኰንን መቁሰል ሲሰማ በንጉሡ ነገሥቱ ዘንድ ጥርጣሬና ሥጋት
አሳድሮ እንደ ነበርና ጦሩ ወደ ኋላው መለስ እንዲል ለማዘዝ አስበው
ነበር ይባላል ። ነገር ግን እቴጌዪቱም እነራስ መንገሻ ፣ እነራስ
ሚካኤል ፣ እነንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በየግንባራቸው ደህና አድርገው
በመመከት አሥጊ የነበረው ሁኔታ ተሻሽሎ በዚህ ፈንታ በመጀመ
ሪያው የጦርነቱ ወቅት አሸናፊነት ያገኘ መስሎት የተደሰተው
ጄኔራል አልቤርቶኒ ራሱ ተሸንፎ ተማረከ ። የርሱም መማረክ
ወገኖቹን ሲያስደነብር በኢትዮጵያውያን በኩል የድል ሙራ የሚፈ
ነጥቅ መሆኑ አይጠረጠርም ።

---

1 ዜናሁ ለልዑል ራስ መኰንን ፣ ገጽ 53 ።



የተማረከው ጄኔራል ማቴዎስ አልቤርቶኒ
ከማዞኮኒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ዐርባ አንድ

## የመጀመሪያው ብሪጌድ ጦር ተዋግቶ ስለ መሸነፉ የጄኔራል አሪሞንዲና የኮሎኔል ጋልያኖ ፍጻሜ

በኢትዮጵያውያን በኩል እንደዚያው እንደ ጣልያኖቹ፤ በግራ በኩል የአልቤርቶኒ ጦር በዘመተበት ግንባር የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት፤ የእቴጌ ፤ የፊታውራሪ ገበየሁና የደጃች ጫጫ ጦር በመጨረሻም የንጉሡ ነገሥቱ ዘበኛ እንደ ዘመተ፤ አሁን በመካከል ዘምቶ ሲዋጋ በምንመለከተው በጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ፊት ለፊት ለውጊያ የተሰለፉት ራስ ሚካኤልና ራስ ወሌ ናቸው። ይኸም ጦር በጠቅላላ የቤጌምድር፤ የየጁ፤ የአማራ ሳይንት፤ የወሎና የአካባቢው መሆኑ ነው።

ነገር ግን፤ በዋዜማው በየካቲት 22 ቀን ማታ ኢጣልያኖቹ ከምሽግ ወጥተው ሌሊቱን ተጉዘው ግራና ቀኝ እየተጠባበቁ በጧት በኢትዮጵያውያን ጦር ላይ አደጋ የመጣሉ ጉዳይ በፕላን ስሕተት ወይም ለየብቻ ድል አድራጊነትን በመመኘት፤ ይልቁንም የኢጣልያኖቹ የሌሊቱ ግሥገሣ በነአውአሎም አማካይነት ባፄ ምኒልክ ዘንድ ከሌሊቱ ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ ስለተሰማ ከሽፎባቸዋል ። በዚሀ ምክንያት ሦስቱም ጄኔራሎች ጦርነት የጀመሩባቸው ሰዓቱም ስፍራውም የተለያየ ስለሆነ፤ የግራውን አዝማች የጄኔራል አልቤርቶኒን ጦር በረፋድ ሰዓት ላይ የደመሰሰው የኢትዮጵያ ጦር ወደ ግራው ተቀልብሶ በመካከል ሆነው ለሚዋጉት ለነራስ ወሌ ጦር ተደራቢ ሆኖ የአሪሞንዲን ጦር ለማጥቃት የተመቸ ሆኗል።

የአሪሞንዲን ጦር ወደ ሰባት ሰዓት ላይ ፈጽሞ የደመሰሰው ጦር በቀኝ በኩል ይዋጋ በነበረው በጄኔራል ዳቦርሚዳ ጦር ላይ ደርሶ እስኪጨልም ድረስ ተዋግቶ መደምሰሱን ወደፊት እንመለከታለን። ደጋግሞም ከጄኔራል ባራቲዬሪ በተሰጠው ፕላን መሠረት አሪሞንዲ ለአልቤርቶኒ ቢደርስለት ዳቦርሚዳና በኋላ ያለው የጄኔራል ኤሌና ተጠባባቂ ጦር ከአልቤርቶኒና ከአሪሞንዲ ጋር ተባብሮ ቢዋጋም፤ በመካከል ለተሰለፉት ለራስ ወሌና ለራስ ሚካኤል በጧት ለተዋጉት ለነፊታውራሪ ገበየሁ ጦርም በሌላው የጦር ግንባር ያለው የበረከተው የኢትዮጵያ ጦር ወደነዚሁ በመሰብሰብ መዋጋቱ ስለማይቀር ፤

እንዲያውም በሦስት በመሥመር የተከፈለውን ጦር ለየብቻ በየተራ በመዋጋትና ጦርነቱ ጧት የጀመረ ላይን እስኪይዝ በመቆየት ፈንታ ድምሩ የኢጣልያ ጦር በድምሩ የኢትዮጵያ ጦር ተሸንፎ ምናልባት ውጊያው ወደ ስድስትና ሰባት ሰዓት ላይ ሳያልቅ አይቀርም ነበር ማለት ይቻላል ። በዝርዝር ተበታትኖ ያዋገፈ ያው ጦር በድምር ተዋግቶ ለማሸነፍ የሚከለክለው ነገር ሊኖር እንደማይችል ይገመታል ።

ሆኖም ግን ፣ ጄኔራል አልቤርቶኒ በኢትዮጵያ ጦር ሰፈር በቀኝ በኩል ከዘመቱት ጓደኞቹ ከአሪሞንዲና ከዳቦርሚዳ ተለይቶ ወደፊት ገሥግሦ ጦርነቱን በመገፍመር ተዋግቶ ተሸነፈ ። ተሸንፎም ሲማረክ ይኸን ሁሉ የደረሰበትን አደጋ ጓደኞቹ ጄኔራሎችና የበላዩ አለቃው ጄኔራል ባራቲዬሪ አያውቁም ነበር ። ለምሳሌ አልቤርቶኒ ጧት በሚዋጋበት ጊዜ ፣ “እርዳታ ይድረስልኝ ” የሚል ደብዳቤ ጽፎ ባንድ ፈጣን ፈረሰኛ እጅ ለጄኔራል ባራቲዬሪ የላከ ጊዜ በርሱ አሳብ ፣ “ ደብዳቤው በቶሎ ደርሶ በጦርነቱ ሰዓት የእርዳታው ጦር ይደርሰኛል ” የሚል ምኞት ነበረው ።

ነገር ግን ፣ አዛዡና ታዛዡ 55 ማይል ተኩል ከመራራቃቸውና ከመንገዱ ወጣ ገባነት የተነሣ ፣ መላክተኛው ደርሶ የእርዳታው ጦር ከመድረሱ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ጦሩ ተሸንፎ አልቤርቶኒም ተማርኮ የሞተው ሞቶ የተረፈው ከጦርነቱ ጉራ ‘እግሬ አውጭኝ’ ብሎ የሚሸሸው የጣልያን ጦር በመንገድ ከእርዳታው ጦር ጋር ተገናኘ ። የሸሹት ፣ ጦርነት ካልቀመሱት ጋር ተገናኝተው በአሪሞንዲና በዶጀኑ መሪ በጄኔራል ኤሌና ውስጥ ሆነው እንደገና ባዲስ ኃይል ለመዋጋት ተዘጋጁ ። የጦርነቱን ዝርዝር ታሪክ ኮንቲ ሮሲኒና ሪዶልፎ ማዘኮኒ ከጻፉት ላይ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል ።

> ... የጄኔራል አልቤርቶኒ ጦር ተሸንፎ የተረፈው የነጭና የጥቁር ወታደር እየሸሸ የሸዋው ጦር እያባረረ ፣ የጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ወደ አለበት ወደ ዝባን ዳዕሮና ወደ ራዓዮ ተራራ ደረሱ ። ...በአሪሞንዲ ውስጥ ለውጊያ የተሰለፉት ከፍተኛ የጦር አለቆች የመቀሌው ጋልያኖ ፣ ቦድዋ ፣ ቪያንቺኒ ፣ ደስቲፋኖ ፣ ኮምፒያኖ ... ይባላሉ ። እነዚህም የየክፍል ጦራቸውን ይዘው ሲጠባበቁ ሐበሾቹ ከኋላ እየተከታተሉ የነጩንና የጥቁሩን የኢጣልያን ጦር እያባረሩ ደረሱ ። በዚህ ጊዜ የመድፈኛው አዛዥ ሎፍሬዶ መድፎቹን አስጠምዶ ሊተኩስ ሲል፣ አባራሪዎቹና ተባራሪዎቹ ቅርብ ለቅርብ ስለሆኑ አንዳንድ ጊዜ ተደባልቀው ስለሚዋጉ ደርቦ እንዳይመታቸው ስለፈራ ተኩሱን ማቆም ግድ ሆነበት ... መልሶ ሲተኩስም ፣ አባራሪዎቹ ተኩሱን ሰምተው ተበታትነው በየጫካው በየሸለቆውና በየቁጥቋጦው ገቡ ። በመድፈኛ ተባራሪዎቹን የባንዳ ወታደሮች ለማቆምና ለማዋጋት ተፈልጎ ነበር ። ግን በፍጹም ሊቆሙና አበሾቹን ሊመከቱ አልቻሉም ። የዚህንም ወሬ



ጄኔራል ባራቲዬሪ በሰማ ጊዜ የሚሸሹት ተሰብስበው በራዓዮ ቁልቁለት ላይ እንዲመክቱ ሲል የጦር ሹማምንት ላከ ።

ከአልቤርቶኒ ጦር የሸሹት የጥቁር ወታደሮች ፣ ለእርዳታ የመጡትን የነጭ ወታደሮች አግኝተው ከተጠራቀሙ በኋላ ፣ ወደፊት የሚገፋትን የኢትዮጵያውያኑን ጦር ለመመከት ተዘጋጁ ። ነገር ግን በዝባን ዳዕሮ በኢራሩ ጠባብ መንገድ በኩምሮ ታህታይ በኩል ያፄ ምኒልክ ጦር እየገፋ ክብ ይሥራ ጀመር ። ከዚያ ወደ መቀራረብ ደረሱና በሁለቱም በኩል ኃይለኛ ጦርነት ተጀመረ ። በየበኩሉ መድፈኛውም በሰባት መቶና በሺ ሜትር ርቀት ሲታኰስ ፣ የቀረውም በየጫካው በየሸለቆው በሩቅም በቅርብም ሆኖ እየተታኰሰ ይዋጋ ጀመር ። ... [illegible] ተደበላልቆ በሳንጃና በጉራዴ በጨበጣ ጦርነት እየተደባደበ መጋደል [illegible]

በዚህ ጊዜ ፣ የሸዋ ጦር እየበረከተ ሔደ ። ዐፄ ምኒልክም በደቡብ በኩል የአልቤርቶኒን ጦር ፈጅተው ከጨረሱ በኋላ ፣ በላጺትና በአባ ገሪማ ተራራ መካከል አልፈው በማይ ቆዳ በኩል ወርደው በአቦ በኩል አሻቅበው ወደ ሰማይታ ወጡ ። ከዚያም ወደ ሰሜን ወደ አዲ በቂ አዘቅዝቀው ማይ አጋም ከሚባለው መንደር ቆመው የማርያም ሸዊቶን ውጊያ በሩቁ ይመለከቱ ጀመር ። በዚያም የንጉሡና የራሶቹ ጦር በሁለት በኩል ተከፍሎ አንደኛው በግንባሩ ያለውን የኢጣልያኖቹን ጦር ሲገጥም ፣ የቀረው እየተሯሯጠ በምዕራብ በኩል በዝባን ዳዕሮ ያለውን ጦር ገጠመ ። የቀረውም ወደ ቤላህ ተራራ ሔዶ የዳቦርሚዳን ጦር በዠርባ በኩል ገጠመው ። የዝባን ዳዕሮን ጉብታ ቀድሞ መያዝ ጠቃሚ መሆኑን ዠኔራል ባራቲዬሪ ተረድቶት ስለነበረ ፣ በቶሎ እንዲይዝ ለኰሎኔል ስቲፋኒ ሁለት ጊዜ ላከበት ። ኰሎኔሉም ይቺን የዝባን ዳዕሮን ተራራ ጫፍ ቀድሞ ለሚይዝ ሽልማት አደርግለታለሁ ብሎ ለጭፍሮቹ ተስፋ ሰጠ ። አንድ ዐርባ የሚሆኑ አነጣጣሪ ወታደሮች(ቤርሳሊዮሪ) በሌተና ኰሎኔል ኮምፒያኖና በካፒቴን ፉብሮኒ ... እየተመሩ ዳገት ቁልቁለቱን በችግር አልፈው ወደጫፍ ተጠጉ ዳሩ ግን ጫፉ በሐበሾቹ ተይዞ ተገኘ ። ቢሆንም ኮምፒያኖ ‘አይዟችሁ ልጆች ዛሬ ማታ ዓድዋ ገብተን ኮክ እንበላለን’ እያለ ወታደሮቹን ያበረታታ ነበር ። የቀረው የሬጂማው አዛዥ አለበት ቦታ ሆኖ ኮምፒያኖ አንዱን ያበሻ ወታደር በሰይፉ መትቶ ቁልቁል ሲወረውረውና ቀጥሎ ብዙ አበሾች እርሱን ከበው ሲገድሉትና ከርሱ ጋር ያሉት ጣልያኖችም በዚያው ቦታ እየተዋጉ ሲያልቁ በሩቁ ይታዩ ነበር ። ስለዚህ በ10:30 (በአራት ሰዓት ተኩል) የተራራው ጫፍ በአበሾቹ እጅ ተረጋግጦ መያዙ ታወቀ ።

የዝባን ዳዕሮ ጫፍ የአሪሞንዲን ጦር በቀኝ በኩል ለመምታት ባንድ ወገንም አልፎ የዳቦርሚዳን ጦር ለመውጋት ምቹ ስፍራ ስለሆነ ፣ የዚህ ጫፍ በአበሾች እጅ መያዝ ለሁለቱም ክፍል የኢጣልያ ጦር ፍጻሜ ምልክት ሆነ ። ስለዚህ እዚሁ ስፍራ ሆነው የኢትዮጵያ ወታደሮች በመጀመሪያው ባታዮ ጦር ላይ እየተኰሱ ሲመቱ እንደዚሁ ከግራና ከቀኝ ከበው እየተታኰሱ ዋናውን የብሪጌድ ጦር ከፋኛ ተያዙት ። የመጀመሪያው ባታዮ ጦርም እየተታኰሰ በዠግንነት ቢጋደልም ፣ አበሾቹ ቁጥቋጦ ፣ ዲብና ቋጥኝ ተገን እየያዙ እየተጠጉ በመታኰስ ብዙ ጉዳት አደረጉ ። ስለዚህ ጣልያኖቹ ባሉበት ቦታ መከላከል ከንቱ መሆኑን ስለ ተመለከተ ፣ ማዦር ደስቲፋኖ ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ

ለቆፍሮቹ ትእዛዝ ሰጠ ። . . . በዚህ ጊዜ ገሚሱ ሲሸሽ የቀረው እንደ ጎርፍ የመጡትን የጠላት ወታደሮች ለማገድ ሲታኮስ የቀረውም የሁለቱ ወገን ጦር ተደባልቆ በጨበጣ ይዋጋ ጀመር ። . . .

በዚህ ትልቅ የድብልቅልቅ ጦርነት ጊዜ ቲኔንቴ ከቫሊኒ ወታደሮቹን እያበረታታ ለማዋጋት 'ኢጣልያ ሕያው ትሁን' ብሎ ቢጮህ ጩኸቱን ከፉ ሳይጨርስ ሙሉ ለሙሉ ደረቱን በጥይት ተመትቶ ወደቀ ። ትንሽ ቆይቶ 3ኛው ክፍል የኮሎኔል ጋሊያኖ ጦር ሌሎችም መጥተው ወደ ጦርነቱ ተቀላቀሉና የራዓዮ ጦርነት ይቀጥል ጀመር ። የአገር ተወላጅ ወታደሮች በጋሊያኖና በሌሎቹ ሹማምንት እየተመሩ አድርገው መከቱ ። . . . ከብዙ ሰዓት ውጊያ በኋላ በግራ [illegible] የኢጣልያ ጦር ደከም መፍረስ ሲጀምር በብዙ ፣ ነገድ (ብሔረሰቦች) የተከፈለው የኢትዮጵያ ጦር በያለበት ከቦ በራዓዮና በግርያም ሸዊቶ ያለውን የኢጣልያን ጦር በርትቶ መውጋቱን ቀጠለበት ።

በኋላም የኢጣልያ ጦር መዳከሙን ሲመለከት ፣ ዋናው አዝማች ጄኔራል ባራቲዬሪ ከተጠባባቂው ጦር ውስጥ ያንድ ሬጂማ ጦር መጥቶ ወደ ጦርነቱ እንዲገባ ጄኔራል ኤሌናን አዘዘው ። ዳሩ ግን ከ24 የክፍል ጦር (ኮምፓኒ) ውስጥ 5 ብቻ ሲጠባበቅ የቀሩት ባንድ ወገን ገና አስቀድመው እጦርነቱ ውስጥ ገብተው ይዋጉ እንደነበረ ዋናው አዝማች አልተረዳውም ነበር ። . . . አበሾች የዝባን ዳዕሮን ጉብታ ሌላውንም ምቹ ሥፍራ ይዘው በኢጣልያኖችና ባገር ተወላጅ ወታደር ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አደረጉበት . . . ግማሾቹም አበሾች በየጫካውና በየቁጥቋጦው ውስጥ ሆነው እንጣጥረው እየተኮሱ የማያዩዋቸውን ኢጣልያኖች ይገድሉ ጀመር ። ኢጣልያኖችም አንዳንድ ጊዜ አበሾቹን ሳያዩ ፣ ከጥይታቸው የሚወጣውን የባሩድ ጢስ ብቻ እያዩ ለመተኮስ ሞክረው ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ምንም የረባ ጉዳት በጠላቶቻቸው ላይ ሊያደርጉ አልቻሉም ። ስለዚህ ግማሹ ሸሽት ሲጀምር የቀረው በእልህ ያለበትን ስፍራ ይዞ እየተዋጋ ሲተላለቅ ያበሾቹን ብዛትና ኃይል ክቢያቸውንና የሚያደርጉትን ጉዳት ሁሉ በተመለከተ ጊዜ ጄኔራል ባራቲዬሪ 11:30 (በአምስት ሰዓት ተኩል) ላይ በጥሩንባ ወደኋላ እንዲሸሹና ከተጠባባቂው ጦር ጋር ሆነው እንዲመክቱ ለኢጣልያኖቹ ትእዛዝ አስተላለፈ ።

በዚህም ጥሩንባውን ከሰማው ውስጥ ግማሹ በሥርዓት ወደኋላ ሲያፈገፍግ ግማሹ በየበኩሉ እግሬ አውጭኝ ብሎ ሸሸ ። የቀረው ደግሞ ጥሩንባና ትእዛዝ ያልሰማው አለቀ ። . . . በዚህ በተዘበራረቀ መልስ ላይ ጄኔራል ባራቲዬሪና ጄኔራል አሪሞንዲ ተገናኝተው ተስፋ በመቁረጥ ተያይዘው እጅ ለእጅ ተጨባበጡ ይባላል ። ከዚያም ሁለቱም ጉራዴያቸውን እንደ ጨበጡ ተዘባርቆ የሚሸሸውን ወታደር ለማቆምና በሥርዓት አድርገው ለማዋጋት ሞክረው ነበር ። ዳሩ ግን በራሪውን ለማቆም በፍጹም የማይቻል ሆነ ። በዚሁ መካከል ትእዛዝ ለመስጠት ወደኋላ ቀረት እንዳለ ጄኔራል አሪሞንዲ ተመትቶ ወደቀ 1 . . . ስለዚህ የመካከለኛው ዘማች ጦር በዚህ

1 Italia ed Etiopia . . . ,pp. 380-400



ዓይነት ሲደመሰስ ዋናው አዝማች አሪሞንዲና እንደ ጋሊያኖ ያሉት የታወቁት የጦር አለቆች በዚሁ ጦርነት ሕይወታቸው አለፈ ።

ስለ ጄኔራል አሪሞንዲ አሟሟት ኮንቲ ሮሲኒ ከዚህ በላይ በተጻፈው ዓይነት ሲተርክልን ፣ ሪዶልፎ ማዙኮኒ የሚባለው ሌላው ጸሐፊ ደግሞ እንደዚ ይላል ።

“ጄኔራል አሪሞንዲ . . . በጦርነቱ በግራ በኩል ሆኖ ጦርነቱን ለመምራት አንድ ከፍ ያለ የድንጋይ ቋጥኝ ላይ ተቀምጦ የጠላትን ጦር ሲመረምር በቀላሉ ቀኝ እጁን ተመታ ። ባገዛ እጁ የተመታውን እጁን በመሐረብ አስሮ መነጽሩን በግራ እጁ ይዞ መመልከቱን ይቀጥል ጀመር ። አጠገቡ የነበረው ያይን ምስክር የሆነው አስተርጓሚው እንደዚህ ሲል ቃሉን ሰጠ ። የእግራ ፈረሰኞች በብዛት ሲመጡ አይቶ መድፈኞች እንዲተኩሱ ትእዛዝ ለመስጠት ቢሔድ ፣ መድፈኞቹ ሞተው ግማሾቹም ቆስለው የጋሊያኖ የባታዮ ጦርም ተበታትኖ አገኘው ። በዚህ ጊዜ ወደኋላ ሽሹ የሚል ትእዛዝ ደርሶት ሹማምንቱን ሲሰበስብ አንድ ጥይት ደረቱን መትቶ ጣለው ። 1

ስለዚሁ ጄኔራል አማሟት ኮንቲ ሮሲኒ በሌላ ሥፍራ ላይ ከቃል የሰማውን የጻፈው እንደዚህ ይላል ።

እግሩን ቆስሎ ምናልባት ባንድ መድፍ ሥር ተቀምጦ ሳለ ወደ ኋላ የሚሸሹት ሹማምንቶቹ አግኝተው እንዲሸሽ ቢለምኑት እምቢ አላቸው . . . ወዲያው በቅሎዩን አምጣልኝ ብሎ አንድ የራሱን ወታደር ቢልክ ፣ በቅሎውን ይዞ ይጠብቅ የነበረው አሽከር (ባንዳ) ተገድሎ በቅሎውም ጠፍቶ አገኘው ። አንድ የጥቁር ወታደር አሪሞንዲ ሌሎች ኢጣልያኖች መድፍ ለመጫንና ለመሸሽ ሲሞክሩ እነርሱን ሲረዳ ተመትቶ ወደቀ ይላል ። የቀሩት ደግሞ ጄኔራል አሪሞንዲ ከሰዓት በላይ ሸሽቶ ወደ ዩሃ ሲሔድ ሰላማውያን መስለው ቆመው የነበሩ ባላገሮች አጠገብ ሲደርስ እነርሱ በጠበንጃ ገደሉት ።

ጄኔራል አሪሞንዲ በጦርነት መሞቱ ሲታወቅ የሞተበት አኳኋን ግን በዚህ ዓይነት ተሰያይቷል ። እላይ እንዳልነው ፣ በዚህ የአምባ ራዓዮ ወይም የዝባን ዳዕሮ ጦርነት የአሪሞንዲ ጦርና ሌሎችም ብዙ የኢጣልያ ወታደሮችና የጦር ሹማምንት አልቀዋል ማለት ነው ። ከነዚህ ውስጥ በመቀሌ ምሽግ መከላከል ስሙ የታወቀው ሌተና ኮሎኔል ጕሴፔ ጋሊያኖ ይገኝበታል ። ጋሊያኖ የዓድዋ ጦርነት በሚደረግበት ጊዜ በተጠባባቂው የደጀን ጦር መሪ በጄኔራል ኤሌና ውስጥ ተመድቦ 3ኛውን የጥቁር ባታዮ ጦር ይዞ ተሰልፎ ነበርና በአምባ ራዓዮ የጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ብዙ ሰዓት ተዋግቶ ወደ መሸነፍ ሲያዘነብል ካለቆቹ ታዞ ለእርዳታ መጥቶ ተዋጋ ። የአሪሞንዲ ጦር ጨርሶ ሲጠፋ እርሱም ያገር ተወላጅ ወታደሩን ይዞ ሲዋጋ ቆይቶ ከርሱ ጋር ከዘመተው አንድ ሺ ሁለት መቶ ጦር ሦስት መቶ ተርፈው

1 La Giornata di Adua, R. Mazzuconi, pp. 275-277

ሲሸሹ የቀሩት አለቁበት ። ከርሱ ጋር ከነበሩትም ዐሥራ ስም ንት ሹማምንት ያመለጠ አንድ ብቻ ነበር ። እርሱም በዚሁ ጦርነት ሞቶ ተገኘ ።[1]

ስለ ሌተና ኮሎኔል ጋልያኖ አሟሟትም ፣ ወሬው በሦስት ዓይ ነት ተተርኮ ይገኛል ።

፩ኛ ግምባሩን ቆስሎ ደሙን እያዝረከረከ ፣ "ጌቶች ሆይ ሰዎቻች ሁን እንደያዛችሁ ፍጻሜያችንን (አሟሟታችንን) እናሳምር " ብሎ አጠገቡ ላሉት ሹማምንትና ባንዶች ተናግሮ ወደኋላው ዘወር እን ዳለ ፣ ከዚያ ወዲያ ወዲያ ወዲያ ግን እንደ እዘገመና ከዚያ ወዲያ አለመታየ ቱን እንደ የጦር ሹም ማውራቱ ተጽፎ ይገኛል ።

፪ኛ. መንጋጋውን በግራ በኩል ተመትቶ ደሙ በጣም ይወርድ ስለነበረ ፣ በቅሎውን ይዘው ወደሚጠብቁት አሽከሮቹ ሒዶ ባንድ ደንጊያ ላይ ተቀምጦ ውሃ አምጡልኝ ብሎ ጨርቁን በወሃ እየነከረ ደሙን ለማቆም ሲሞክር የኢትዮጵያ ወታደሮች በድንገት ደርሰው ማረኩት ። ጋልያኖ መሆኑንም ስላወቁ የደስታ ጥይት ወደ አየር እየ ተኮሱ ጐትተው ወደ ታችኛው ሸለቆ ወሰዱት ። በዚያም ለንጉሣችን እናቀርብሃለን ብለው ሲጐትቱት እርሱም 'የርሱን (የምኒልክን) ፊት አላይም' ብሎ ሲተናነቅ አንዱ በጥይት መትቶ ገደለው ።[2]

፫ኛ. ማገር ባቲስታ አሜሊዮ የሚባለው ለጦር ምክትል ሚኒ ስትሩ በጻፈው ደብዳቤ ላይ ፣ "ካሣ ኀይሉ የሚባለውን አሽከር ( ያገር ተወላጅ ወታደር ) በመጋቢት 10 ቀን የእስረኞቹን ወሬ እንዲያጠያ ይቅ ልኬው ስለነበረ ፣ ጋልያኖ ከተማረከ በኋላ የመቀሌን ምሽግ የለቀቀ ጊዜ ፣ ሁለተኛ አልዋጋም ብሎ የነበረውን መሐላ አፍርሶ ሰዎ ቹን ስለወጋ ጥፋተኛ ነው ብሎ አንድ ሊቀ መኳስ እምኒልክ ላይ ከሶት በጥይት ተደበደበ"[3] ይላል ። አንድ የደራሲው ስም ያልታ ወቀ የግዕዝ ታሪክ ፣ መቀሌ የነበረው ጋልያኖ ሁለተኛ ወደ ንጉሥ መጥቶ እንዳይዋጋ በመሐላ ከሔደ በኋላ ፣ ተመልሶ መጥቶ ሲዋጋ ተማ ረከ ማራኪው ወደ ንጉሡ ልውሰድህ ቢለው እምቢ ስላለው ገደለው " ሲል ባጭሩ ደምድሚልና ይኸኛው ሊታመን ይችላል ።[4]

---

1 Italia ed Etiopia . . . P. 404.

2 La Giornata di Adua, PP.276—277.

3 Lettere e Diari, . . . P.56.

4 ወማገር ጋሊያኒ (ጋሊያኖ) ዘነበረ በመቀሌ ወዘመሐለ ከመ ኢይመጽእ ዳግመ ለባእስ መጽአ ተማኅሪኮ ወሰበ አበየ ይሑር ቅድመ ገጸ ምኒልክ ንጉሥ ቀተሎ እንተ ማኅረኮ ፣ የኢትዮጵያ ጥናት IES, No. 681, P. 129. (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)





በዓድዋ ላይ የሞተው ጄኔራል አሪሞንዲ

ከማዙኮኒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ዐርባ ሁለት

## የቀኝ አዝማቹ የብሪጌድ ጦር ተዋግቶ መሸነፍ — የጄኔራል ጆሴፔ ዳቦርሚዳ አሟሟት

ቀደም ብሎ በተደረገው ጦርነት ድል ለተመታው ጦር፥ ግንባር ቀደም ሆኖ የጥቁሩን ወታደር ይዞ በእምባ ኪዳነ ምሕረት የተዋጋው ጄኔራል አልቤርቶኒ ከተማረከና በመካከል በእምባ ራዓዩ የዘመተው የጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ተሸንፎ ከፈረሰ በኋላ፥ ተጠባባቂ ሆኖ በረቢ አሪዬኒ የነበረው የጄኔራል ኤሌና ወታደሮችና በዋናው አዝማች በጄኔራል ባራቲዬሪ ዙሪያ የነበሩት ከውስጣቸው በከፊል እየተመረጡ ሔደው የተሸናፊዎቹን ዕድል መካፈላቸው ታውቋል። ይኸ ሁሉ ሲሆን፥ በቀኝ በኩል የዘመተው ጄኔራል ዳቦርሚዳ ለብቻው ተለይቶ ወደ ማርያም ሸዊቶ ሔዷል። ጄኔራሉ በሩቅ የጥይት ተኩስ መስማቱ ባይቀርም፥ በጓደኞቹና በቀረው የጦር ሠራዊት ላይ የደረሰውን የመሸነፍ አደጋ በትክክል ያወቀ አይመስልም።

ለብቻው ተነጥሎ ሔዶ ለመዋጋት የፈለገበትን ምክንያት በኋላ የተነሡ ጸሐፊዎች፥ "እንደ አልቤርቶኒ ብቻውን የኢትዮጵያን ጦር ተዋግቶና አሸንፎ የድል አድራጊነትን ክብር ለብቻው ለመውሰድ ተመኝቶ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚሁ አያይዘው፥ "ያለዚያ አልቤርቶኒ ወይም አሪሞንዲ በሚዋጉበት ጊዜ ወደኋላ ወደ እምባ ራዓዩ ወደ ግራው ወደ እምባ ኪዳነ ምሕረት ታጠፍ ብሎ ለእርዳታ ቢደርስ ኖሮ የሐበሻ ጦር ሳይሸነፍ አይቀርም ነበር" ብለው እንደ መሰላቸው አመልክተዋል። የቀሩት ደግሞ፥ "በመለገም ሳይሆን በፕላንና በመንገድ ስሕተት ለብቻው ወደ ማርያም ሸዊቶ ተመርቶ ሔዶ አብረውት የነበሩትም የነጭ ወታደሮች አገርና መንገድ የማያውቁ ከመሆናቸውም በላይ በመንገዱ መጥፎነት ከሜካው ብዛት፥ ከስፍራው ወጣ ገብነት የተነሣ ከመድከም ጋር በሌሊት ጉዞ በስሕተት ወደቀኝ ወደ ማርያም ሸዊቶ ርቆ ሔዶ ለብቻው ተዋግቶ ለብቻው ተሸነፈ" ብለው በታሪክ ፊት የስሕተት እንጂ፥ የመለገም ወይም የራስ መውደድ ኃላፊነት እንዳይወድቅበት ተከላክለውለታል። በተለይ የርሱ የልፍኝ አስከልካይ የነበረው ኮሎኔል ቤላቪታ ስሕተቱን በፕላን አሠራር፥ በትእዛዝ አሰጣጥና ባመራር ረገድ በባራቲዬሪ ላይ አድርጎታል።

የእሪሞንዲና የኤሌና ጦር በሚዋጋበት ጊዜ ፣ አደጋ ላይ መሆኑን ዋናው አዝማች ጄኔራል ባራቲዬሪ ተገንዝቦ የዳቦርሚዳ ጦር መጥቶ እንዲረዳ ለማድረግ እነ ኮሎኔል ባሌንዛኖን ፣ እነማዦር ሳልሳን ዳቦርሚዳን እንዲፈልጉ ልኳቸው ነበር ። ዳሩ ግን ፣ ይህ ጄኔራል ከነጠሩ ርቆ ለብቻው ከመሔዱ የተነሣና ግማሹ ስፍራ በድል አድራጊዎቹ ኢትዮጵያውያን ስለተያዘ ፣ መላከተኞቹ ብዙ ሰዓት ተንከራተውና ባዝነው አጣነው ብለው ተመለሱ ።

በኢጣልያኖቹ ጽሑፍ እንደሚገኘው ፣ ጄኔራል ዳቦርሚዳ በውስጡ ሦስት ሺ ስምንት መቶ ስምንት የጦር ወታደር ፣ ዐሥራ ስምንት መድፍ እንደያዘ ፣ እንደ ጓደኞቹ ሌሊቱን ተጉዞ ሲነጋ ወደ ማርያም ሸዊቶ አቅራቢያ እንደ ደረሰ ፣ በያለበት ጦሩን ከፋፍሎ ያሠማራ ጀመር ። ማጆር ደ ቪቶ የሚባለው የጦር አዛዥ የጥቁር ወታደሮች ጦር ጨምሮ ግንባር ቀደም በማድረግ ወደ ማርያም ሸዊቶ ላከው ። በዚህም ጊዜ በአባ አቤል አጠገብ ቃፊር ሆኖ ይጠባበቅ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር በማይቶጉ ሆኖ ቁልቁል የሚወርዱትን ጣልያኖች ተመለከተና ከዚያ ራስ መንገሻ ወዳሉበት ወደ ጌራ ሔደ ። በዚያው አቅራቢያ በኤረር የሸዋ ጦር ስለነበረ ፣ ግንባር ቀደሙ የማጆር ደ ቪቶ ጦር ወደ አምባ ድሪያም አቀበት ሊወጣ ሲል ተኩስ ተጀመረ ። ወዲያው በፍጥነት ተዠሱ ተጋግሎ ይዋጉ ጀመር ። የቀሩት የጥቁሩም ፣ የነጩም ወታደሮች ባንድነት ሆነው እንደ ጐርፍ የመጡባቸውን የኢትዮጵያውያንን ሠራዊት ገትረው ሲዋጉ ደ ቪቶ ወታደሮቹን ይዞ ሳያስብ ፣ ባዶ መስሎት ድሪያም ጉብታ በተለይ አድግባ ከሚባለው ስፍራ ሲደርስ ራስ መንገሻ (ዮሐንስ) በድንገት ተቀብለው ተዋጉትና ሞተ ። የግንባር ቀደሙ ጦር ቢያልቅም ፣ ዋናው የዳቦርሚዳ ጦር በአራት ሰዓት ተኩል ተኩስ በተጀመረበት ጊዜ ከዚህ እንደሚከተለው ተሰልፎ ነበር ።

በግራ በኩል ፣ 10ኛው ባታዮ በደፎኒስካ አዝማችነት ፣ በቀኝ በኩል በአምባ ድሪያም 6ኛው ባታዮ በፕራቶ አዝማችነት ፣ በታች በኩል 5ኛው ባታዮ በጆርዳኖ መሪነት ፣ 18 መድፎችም በሸለቆ ውስጥ ተጠምደዋል ። በቀኝ በኩል 14ኛው ባታዮ በሶላሮ መሪነት ፣ 2ኛው ባታዮ በኮሎኔል አይራጊ የሚመራው ከኋላ ይጠባበቅ ነበር ። ከነዚህም በቀር አምባ ኤረር ላይ በኢትዮጵያውያኑ ተከበው ሊያልቁ የነበሩትን ጣልያኖች ያዳናቸው ማዦር ደ አሚቺስ በዚሁ ስፍራ ይገኝ ነበር ።

የዚህን ጊዜና ስፍራ ጦርነት ካፒቴን ኪዩሪቺ የተረከው እንደዚህ ይላል ።

ከኤረር ጉብታ መቶ ሜትር የሚያህል ወደታች እንደ ወረድን ተጠባባቂው ጦር በድንገት ወደኋላ ሲያፈገፍግ አየነው ። ደ አሚቺስ



እኛ ወደ ተውነው ጉብታ እንድንመለስ አዘዘ ። በዚሁ መካከል ድንገት ከያለበት ዥሮ የሚያደነቁር የጥይት ጩኸት ተሰማ ። ኢጣልያኖችም በዚሁ ጥይት በትር እየተጨጨሁ ተረባርበው ወደቁ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ጥይቱ ከእኩል ሰዓት በፊት ከለቀቅነው ከቅርብ ስፍራ መምጣቱን ተረዳነው ። ነገር ግን ፣ ክሣሩ እርዝግኔ የተነሣ ተኳሾቹን በፍጹም ማየት የተሣነን ቢሆንም ፣ ተሰልፈን የጥይት ተኩስ በሚሰማበት አቅጣጫ እንተኩስ ጀመር ። ዳሩ ግን ፣ ተኩሳችን ፍሬ የሰጠ አይመስለኝም ። በመጨረሻ አምሳ የሚሆኑ የጠላት ወታደሮች ስላየሁ ፣ በሳንጃ ተዋግተው እንዲያባርሯቸው አዝዤ ቀጥሎ በሩጫ ሔጄ እኛንና ወገኖቻችንን የሚለየውን ስፍራ ያዝሁ ። ከዚያ በሰልፍ ሆነን በቅሎቻችንን ከሚጠብቁት ጋር የሚማቱትን ሐበሾች መውጋት ጀመርን . . . እነዚህ ሐበሾች ሐሞት (ጉብዝና) ያላቸው መሆናቸውን መካድ አይገባም ። የሚተኰሱባቸውን ጥይት ሳይፈሩ ጭንቅላታቸውን አጐንብሰው ሰይፋቸውን እያወዛወዙ በቅሎዎቹ የታሰሩበትን ጠፍር በጥሰው ለመውሰድ እየሮጡ ሲመጡ እኔው ራሴ አይቻቸዋለሁ ። ብዙዎቹንም አጠገባችን ከደረሱ በኋላ በሽጉጥ ልንመታቸውና ልንገድላቸው ችለናል ። በግራ በኩል ተደብቆ የኛን ጦር ያጭድ የነበረውንም የጠላት ጦር ሞኒና የሚባለው ጐበዝ መኰንን ከጭፍሮቹ ጋር ገጥሞ በሳንጃና በጨበጣ ተዋግቶ ካሉበት አስወጥቶ ሲያባርር እርሱ ራሱ ተመትቶ ወደቀ ።

ቢሆንም ባለንበት ስፍራ ለመቆየት ከየአለበት በዙሪያችን በብዛት የሚተኰሰው ጥይት አላስቻለንም ። እኛም በያቅጣጫቸው መልሰን ብንተኩስ አልሆነም ። በዚህ ጊዜ አዝማቹ ማዦር ባለበት በኩል 'እየምሸጋችሁ' የሚል ጩኸት ስለተሰማ ፣ በየቁጥቋጦውና በየቋጥኙ ውስጥ አልፈን አንዲት ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ደረስንና የቤተ ክርስቲያኑን ቅጥር እንደ ምሽግ ተገን ይዘን ተቀመጥን ። ይሁን እንጂ በዐሥር ደቂቃ ውስጥ 150 ወታደሮችና 3 መኰንኖች አለቁብን ። . . .ምሽግ ይዘን ትንሽ እንደ ተነፈስን ጠላት እያደር በብዛት እየተኰሰ እያየነው ይከበን ጀመር ። እነጣጥረን ለመተኮስ የምንችለውም የጥይት ጢስ በሚታይበት በኩል ብቻ ነው ።. . .የትግሬን ጦር የያዙት ራስ መንገሻና ራስ አሉላ በአዲ ፈቂ በራዕድ በረቢ አሪዬኒ ያለው ጦር ለእርዳታ ሳይመጣላቸው ጦርነቱን እንዳይጀምሩ ትእዛዝ ተቀብለው ነበር ። የተጠበቀው የእርዳታ ጦር ከአራት ሰዓት ጀምሮ በብዛት ከመጣላቸውና የኢጣልያ መድፎች መጮህ ከጀመሩ ወዲህ ዋናው የሸዋ ጦር የዳቦርሚዳን ጦር በኃይል ገጠመው ። የመድፉ ድምፅ ከቀሰቀሳቸው ወዲህ በአባ እቤል በግራ በኩል የጠላት ሠራዊት በብዛት ተገኝቶ በብዛት እየተኰሰ የኢጣልያኖችን የእግረኛ ጦር ክፉኛ ፈጀው ። ኢጣልያኖቹ እታች ሆነው ወደላይ ወደ አበሾቹ የተኰሱት ምንም ያህል ጉዳት አላደረገም ። ይልቅስ ዐሥራ ስምንቱ መድፎች የጥይት ነበልባላቸውን እየተፉ ጠላት የያዘውን ስፍራ ማስቸገራቸው ግልጽ ነው ። በዚህ ሰዓት ዋናው የዳቦርሚዳ ጦር በሙሉ ጦርነቱን ጀመረ ። . . .ወታደሮቹም ሹማምንቱም ዋናው አዛዥም ፣ ምንም እንኳን አንድ ታክቲክ (የጦር መላ) ቢጐድል ደንበኛ የጦርነት ሞያቸውን አሳዩ ። በነርሱም ብርታትና ዘዴ ጠላት እየለየ ለመምታት

ሳያበችለው ቀረ ። እንዳለበውም ከቦ ለመፍጀት እንዳይችል ጠንክረው ተከላከሉት ።

ቢሆንም ጊዜው በረዘመ ቁጥር ፣ የጠላት ጦር እየተሟሟ ሔዶ የኢጣልያኖቹንም እርምጃ እግር በእግር ሐበሾቹ ይታወሙ ነበር ። ሐበሾቹ በኃይል ተቀስቅሰው ጣልያኖቹ የያዙትን ስፍራ ለማስለቀቅ ሲሞክሩ በጥይት ኃይልና ብዛት መለሷቸው ። ከተመለሱም በኋላ እንደገና እየተዋጉ የፈለጉትን ስፍራ በመቀማት ብዙ ስፍራዎች እየ ሔዱ እየተመለሱ ካንድ እጅ ወደ ሌላው እጅ ተዘዋውረዋል ።

ስለዚህ ፣ ጣልያኖቹ እስከ 13 ሰዓት ድረስ በዚሁ በአባ አቤል በማኅበረ ጸዳል በአጽገባ . . . ጎትረው አራት ጊዜ የበረከተውን የኢት ዮጵያውያንን ጦር ከመለሱና ስፍራቸውን ከአጠበቁ በኋላ ጀኔራል ዳቦርሚዳ በመልካም ሁኔታ የሚገኝ መሆኑን በዚሁ ጊዜ ለዋናው ጠቅላይ አዛዥ ለጀኔራል ባራቲዬሪ መልክት ልኮ ነበር ። ዳሩ ግን አልደረሰለትም . . . ኢጣልያኖቹ ውጊያውን ቆም አድርገው መድፎቻ ቸውን የተሻለ ስፍራ ፈልገው ከጠመዱ ለየባታዮም መጣሪያ አጓ ልተው ከአከፋፈሉ በኋላ ፣ የቆመው ጦርነት እንደገና ተቀሰቀሰ ። ይሁን እንጂ ፣ ከ13 (7) ሰዓት ቀጥሎ ባለው ጊዜ የኢጣልያኖች ኃይል ወደ መድከም ቀረበ ። በአምባ ራዓዮ ተዋግተው የጀኔራል አሪሞንዲን ጦር የመቱት የዐፄ ምኒልክ ወታደሮች ተገልብጠው ወደዚህ ስለመጡ የዳቦርሚዳ ጦር በወታደር ግድግዳ ከጊዜ ወደጊዜ እየተከበበ ሔደ ። የንጉሡ መድፈኞች በግራ በቀይህ ዘባን በኩል እንደዚሁም በቀኝ በአባ አቤል በኩል ድምፃቸውን እያሰሙ ሲያጠቁ የቀረው የእግረኛ ጦር ከቢውን ብቻ እየሠራ ውጊያውን ስጊዜው አላላ . . . የኢትዮጵያው ያን ጦር በየጫካው ተሰግስጎ ከቦ እየተጠባበቀ ሁለት ሰዓት ያህል ያለውጊያ ሲቆይ . . . የኢጣልያ ጦር ከፉኛ ስለ ተከበበ ፣ በዚሁ ጊዜ አንድ የመውጫ መላ መፍጠርና ባንድ ፊት እየተዋጉ ጥሶ መውጣት ግዴታ ሆነ ። . . . ስለዚህ እስካሁን በብርታት ወታደሮቹን ሲያዋጋ የቆየው ኰሎኔል አይራጊ እፈረሱ ላይ ወጥቶ ሲመራ ተነሣ ። በመታከስ ከንዳቸው የዛለው መላሳቸው በውሀ ጥም የተያዘው ወታደሮችም ሲከተሉት ተነሡ ። ነገር ግን ዐሥር ሜትር ያህል እንደ ተራመዱ ብዙ ዎቹ እየተመቱ ወደቁ ። . . .

አዝማቹ ጀኔራል ዳቦርሚዳ ፣ የመከበቡ ሁኔታ በጣም ስላሠጋው የቀሩትም የብርጌድ ወታደሮች ወሬያቸው ስለ ጠፋበት ፣ ተቸግሮ መላ ከተኛ ለመላክ ቢያስብ በዙሪያው ካሉት የቅርብ አገልጋዮቹ መኰ ንኖች ግማሾቹ ሞተው የቀሩትም ቆስለው ወይም ተበታትነው አገ ኛቸው ። ከዚህ በኋላ ጭንቅላቱን አነቃንቆ እጆቹን ወደኋላ አጣምሮ ይዞ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሰ ከተንጐራደደ በኋላ ፣ ቆም ብሎ ቀና አለና ፈረስ አምጡልኝ አለ ። ከመጣለትም በኋላ አንዳንድ ወጣት ዘሎ እፈረሱ ላይ ወጣና የመጨረሻ የመጣስ ሙከራ ለማድረግ ወደ ውጊያው መስመር ሔደ ። ኰሎኔል አይራጊና ሌሎቹም ሹማምንት ተከተሉት ። በዚያን ጊዜ ጀኔራሉ በሠራዊቱ ፊት ጥሩሩን አውልቆ እየወዛወዘ ‘ሳቮያ ሳቮያ’ ብሎ ደጋግሞ ጮኾ ግልቢያ ሲጀምር ፊታቸው በአቧራና በላብ የተሸፈነው ወታደሮቹ የጀኔራላቸውን ድምፅ ሲሰሙ ያለፈው ድካማቸው ሁሉ ተወገደና ባንጃቸውን እያወዛወዙ



‘ሳቮያ’ እያሉ እነሱም በጩኸት መልስ ሰጥተው እየተሯሯጡ ተከተሉት ። * ዳሩ ግን ፣ በዚሁ ጊዜ ከሐበሾቹ የተተኰሰው ጥይት እየረፈረፈ በየመንገዱ ዘራቸውና ስፍራው በሬሳና በቁስለኛ ተሸፈነ ። መሬቱም የነርሱን ደም ጠጣ ። . . . ዐሥራ ስምንቱ መድፎችም እነሱን ለመጠበቅና ለመደገፍ አልቻሉም ። ለመድፎቹ ጥይት የሚያጐርሱት እየተመቱ ወደቁ ።

ከኢጣልያኖቹ በኩል መከላከል መድከሙን ሲረዱ ሐበሾቹ የያ ዙትን ስፍራ እየለቀቁ ቁልቁል ወደ ጣልያኖቹ ወርደው ይታኰሱ ጀመር ። የተረፉትም ጣልያኖች የሞቱትን ጓደኞቻቸውን ለመበቀል ተሰፋ በቆረጠ ንዴት እየተታኰሱ ብዙ ፈጁ ። ከነርሱ መካከልም አንድ ሲቪር ቦኮኒ የሚባል የሚላኖ ተወላጅ በፈቃደኝነት የብርጌዱን ጦር ከረቢ አሪዮኒ ተከትሎ የመጣ ሲቪል ነበር ። እርሱም አንድ የአሜሪካን ካራቢን ጠበንጃ ይዞ አንዳንድ ጊዜ እየዘፈነ ፣ አንዳንድ ጊዜ እያንጣጠረ ብዙ ጠላት በመግደሉ የጦር መኰንኖቹን ሁሉ አስደንቀ ፣ እንደዚህ አድርጐ እየተዋዛ እየተሳለቀ ሲዋጋ ቆይቶ እርሱም በፋን ታው ተመትቶ ወደቀ ። . . . **

ከዚህ በኋላ ጀኔራል ዳቦርሚዳ ወደኋላ ሽሽት እንዲያደርጉ ለኢጣልያኖቹ ትእዛዝ አሳለፈ ። መተላለፊያውም እሾህ ቋጥኝ የሞላ በት በመሆኑ ወደኋላ ለመሸሽ ሁሉም ተፋፈገ ። ትእዛዝም ለየክፍሉ ለማስተላለፍ መተላለፊያ ቸገረ ። በዚህም ጊዜ ሐበሾቹ ምንም ከነርሱም ወገን እልቂትና ድካም ቢኖር ፣ የሚሸሸውን እየተከተሉ እየተጠጉ ስለሚፈጁ ፣ ጀኔራሉና ሹማምንቱ አንዳንድ ጊዜ ፊታቸውን አዙረው እየተዋጉ አጥቂዎቹ እንዲገቱ በራሪዎቹ ትንሽ የመሸሻ ጊዜ እንዲያ ገኙ አደረጉ ። እየተመለሱ ሹማምንቱ ሐበሾቹን ለማቆም በሚዋጉበት ጊዜ ብዙ የጦር መኰንኖች እየተመቱ ይወድቁ ነበር ። በዚህ መካከል ጀኔራል ዳቦርሚዳ ተመትቶ ወደቀ ። . . 1 .

ከዚህ በላይ የተጻፈው ፣ ሪዶልፎ ማዙኮኒ የሚባለው ከመንግሥቱ የባሕር መዝገብ ቁጥር 29 ላይ ወስዶ ባዘጋጀው መጽሐፍ የሚገኝ ነው ። ሌሎቹም እነፖሎራ ፣ እነኮንቲ ሮሲኒ በጦርነቱ ላይ ከዋሉት ከነቤላቪታና ከሌሎቹም ከቃልም ፣ ከጽሑፍም እየሰበሰቡ የጀኔ ራል ዳቦርሚዳ የጦርነት ታሪክ የተጻፈው በዚሁ ዓይነት ነው ። እንደ ተለመደው ጸሐፊ ሁሉ በመሠረቱ እየተስማማ በዝርዝር ይለያያ ልና ኮንቲ ሮሲኒ የዚህን ቀን ጦርነት ሲተርክ ፣ በማርያም ሸዊቶ

---

* SAVOYA የንጉሡ የኡምቤርቶ የነጋሢነት አስመኪ መደበኛ ሥፍራ ነው ። አሁን ይኸ ሥፍራ በፈረንሳይ ምሥራቅ በኩል ይገኛል ፤ ስሙም በፈረንሳይ አጠራር SAVOIE ይባላል ።

** Luici Bocconi የሚባል በሚላኖ በንግድ ሥራ የሚኖር ነበር ። እርሱም ወታደርነት ሳይኖረው የኢትዮጵያን ጦርነት በመናቅና በማቃለል ወደ ሽርሽር እንደሚመጣ በመቁጠር በፈቃደኝነት የመጣ ነው ።

1 La Giornata di Adua, Ridolfo Mazucconi PP. 281—301 Libro verde, No 29.

የተደረገውን ጦርነት ልክ እንደ ሪዶልፎ ይተርከና አንዳንድ እዚያኛው ላይ የማይገኝ ቃል እርሱ እንደዚህ የሚል ጨምሯል ። "ጄኔራል ዳቦርሚዳ ሽሽቱን ሲይዝ በቀኝ እጁ ጥሩሩን እንቆ ይዞ ያለቅስ ነበር ። ኰሎኔል አይራጊም 'ወደኋላ እንመለስ ፣ ነገር ግን ይህ መመለስ(መሸሽ) በዝግታና በሥርዓት መሆኑን እንዳትዘነጉ' የሚል ቃል በጩኸት ለተረፈው ሠራዊት ተናገረ ።"

በሽሽትም ጊዜ ሐበሾቹ ራቅ ሲሉ በጥይት ፣ አንዳንድ ጊዜም ሮጠው በሚሸሹት ጣልያኖች ላይ እየደረሱ በጎራዴና በሰይፍ ይማታሉ ። አንዳንድ ጊዜ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ወታደሮች እየተናነቁ ሁለቱም ተያይዘው ከቋጥኝ ላይ ቁልቁል ወድቀው ሲንከባለሉ መታየታቸውን እየጨመረ ፣ እያስፋፉ ይጽፋል ። ዋናው አዛዥ ጄኔራል ዳቦርሚዳ ሲሞት በትክክል ያየው ለጊዜው ስለጠፋ ፤ የጄኔራል ዳቦርሚዳ አሟሟት እንደ ሌሎቹ በተለያየ ሁኔታ ተተርኮ ይገኛል ።

፬ኛው. ጄኔራል ዳቦርሚዳ እላይ እንደ ተጻፈው ፣ ከጦር ሹማምንቱ ከኰሎኔል ራፒ ፣ ከማዦር ፕራቶና ከማዦር ዴ ሬኒስካ ጋር ሆኖ እሸሽት ላይ እንዳለ ለተረፈው ጦር የመሸሻ ጊዜ ለማስገኘት ፊቱን እየመለሰ በሚዋጋበት ጊዜ ተመትቶ ወደቀ ። በወደቀ ጊዜም "ኢጣልያ ሕያው ትሁን" ብሎ ጮኾ ሞተ የሚሉ አሉ ።

፭ኛው. በዮሃ ሸለቆ በተለይ አዲ ቂልጠይ ከሚባለው ስፍራ ሲዋጋ መሞቱን አልቤርቶ ፖሌራ ይጽፋል ። ከዚሁ አያይዞ የዓድዋ ጦርነት በተደረገ በሦስተኛው ወር ሬሣ ቀባሪዎች ጣልያኖች በመጡ ጊዜ ፣ "በሱንኮሂና ሲዋጋ ክፉኛ ቆስሎ ሳለ ውሃ እንድሰጠው ለመነኝና ከሰጠሁት በኋላ ፣ ወዲያው ሞተ" ብላ አንዲት ያገር ተወላጅ አሮጊት ሴት እንደ ነገረቻቸው በርሷም አመልካችነት ዐፅሙን ሰብስበው ባንድ በተለየ ስፍራ አከማችተው ድንጋይ ቆልለው ስሙንም እንደ ጻፉበት ይኸው ጸሐፊ ያመለክታል ።[1]

፮ኛው. በኮንቲ ሮሲኒ መጽሐፍ ውስጥ ከዊልድና ከካፒ ቶላ መጻሕፍት የተገኘ ተብሎ እንደሚቀጥለው ተጽፏል ።

ጄኔራል ዳቦርሚዳን የገደለው ባሻ ገብሬ ይባላል ። ባሻ ገብሬ ራሱ እንደ ተረከው ፣ ከዓድዋ ሁለት ሰዓት ያህል ሔዶ ብዙ ውሃ በሚፈስበት አጠገብ ቁጥራቸው ትንሽ የሆነ ኢጣልያኖች ሲዋጉ አገኘ ።

I La Battaglia d' Adua Scritta . . . ,A. Pollera,



ከነርሱ መካከል አንድ ሽምግል ያለ የወርቅ መነጽር ያደረገ በቀኝ እጁ ሽጉጥ ይዞ ነጭ ሻምላውን በወገቡ አንዳንጠለጠለ ይታይ ነበር ። በርሱ አጠገብ መድፍ ከተሜኑ ከሦስት በቅሎዎች በቀር ሌላ የጭነት ከብት አልነበረም ። ይኸም ሽማግሌ ወደርሱ የሚቀርበውን እየተኰሰ በመጨረሻ ሦስት የባሻውን ጓደኞች ገደለ ። በርሱም (ገብሬ) ላይ በተኰሰበት ጊዜ ተገን ይዞ ዳነና መልሶ ተኩሶ ሽማግሌውን መታው ። የጥይቱ በትርም ከትከሻው በታች አልፎ በግራ ጡቱ ወጥቶ ገደለው ። ባሻ ገብሬ ከዚያ ወደ ሬሣው ሔዶ ከገፈፈው በኋላ የወርቁን መነጽር ለንጉሡ ሰጠና የቀረውን የግሉ ወረቀቶች ያሉበትን የኪስ ቦርሳውን አዲስ አበባ ይዞት መጥቶ ታይቷል ። ይኸንንም ቃል ዊልድና ቶላ የሚባሉት ፈረንጆች የሰሙት በቀጥታ ከገዳዩ ከባሻ ገብሬ አንደበት ነው ። በተለይ ቶላ የኪስ ቦርሳውንም አይቶታል ። 1

ኰሎኔል ኤሚሲዮ ቤላቪታ ለጄኔራል ዳቦርሚዳ የልፍኝ አስከልካይ ነው ። በጦርነቱ ጊዜ አብሮ ዘምቶ ሳለ ፣ የጄኔራል ዳቦርሚዳን ፍጻሜ በምን አኳኋን እንደሞተ አያውቅም ።ከጦርነቱ በኋላ በጻፈው መጽሐፍ ላይ 1

. . . የኛ መድፈኞች ባደረጉት የውጊያ ተግባር የድል ተስፋ አሳድረውብን ነበር ። . . . በ13 ሰዓት (7) ዳቦርሚዳ አያያዛችን መልካም ነው የሚል ወሬ ለባራቲዬሪ እስከ መላክ ደርሶ ነበር ። ዳሩ ግን ፣ በዚህ ጊዜ ባራቲዬሪ ወደኋላው ሸሽቶ ስለነበረ መልእክቱ አልደረሰውም ። ይሁን እንጂ ፣ ወዲያው ውጊያው ተፋፍሞ በኛ ስፈር የሚሞተውና የሚቆስለው እየበረከተ ሔደ ። እስከ 15(9) ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ጠላት ከአለበት ጉብታ ሆኖ ሊመለከተንም ፣ ሊቆጥረንም ስለቻለ በጥሩ ዓይነት እያስተካከለ በሩምታ የሚተኩሰው ጥይት አንድም የተቃና ቁርጠኛ ሥራ ለመሥራት አላስቻለንም ። . . . ሽማግሌው ኰሎኔል አይራጊ ቆስሎ በሚደማው ፈረሱ ላይ ሆኖ በፉከራና በግለት ጭፍሮቹን ለማዋጋት ሦስት ጊዜ እየወጣ እስከ 10 ሜትር ድረስ ወደ ጠላቶቹ እየቀረበ ሲያዋጋ ጠላት እንደልቡ ወታደሩን ያጭደው ጀመር ።

በዚያን ጊዜ ፣ ጄኔራል ዳቦርሚዳ ጭንቅ ገባው ። ወደኔም ፊቱን አዙሮ የሌሎቹን የብርጌድ ጦሮች ወሬ ማጣት እንዴት መጥፎ ነው አለኝ . . . እኔም ወሬ ለመፈለግ ሔድኩ . . . ከዚህ በኋላ ጄኔራል ዳቦርሚዳ አንድ ጊዜ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ራሱ የተረፈውን ጦር እየመራ ወደ ጦርነቱ ተመልሶ ለመግባት ኰሎኔል አይራጊንና ሌሎቹን የጦር መኰንኖች እንዳስከተለ የራስ ቁሩን በእጁ ወደ ሰማይ ዘርግቶ "ሳቮያ" እያለ ደጋግሞ በመጮህ ፈረሱን አስጋልቦ ወደ ጦርነቱ ሲገባ ፤ ሁሉም ተከትሎት ገባ. . . ሁሉም አንድ ባንድ እየተመቱ ቀድሞውኑ በደም እቀላው መሬት ላይ ተረፈረፉ . . . መድፈኞቻችንም ሁልጊዜ እንደ ተምበረከኩ በተቻለ መጠን በመድፍ ተኩሰ አገዙ ።

1 Italia ed Etiopia . . . PP. 445—446. Li Italiani in Africa—a Del Boca—pp. 683—690.

> . . . ነገር ግን ሼዎቹ ከያለበት እየተኾጐደጐዱ ስለ ወረዱና ማጥቃታቸውን ስላጠነከሩ ምንም ማድረግ አልተቻለም ። በዚያን ጊዜ ዳቦርሚዳ ሌላ የምናቀርበው ተጠባባቂ ጦር እንዳለ ጠይቆኝ አለመኖሩን ባስረዳው ወደኋላ መመለስን (ሽሽትን) አዘዘ . . . ጄኔራሉ ፊቱ አዝኗል ፤ መናገርም አልቻለም. . . በሽሽት ጊዜ በመንገድ ሰው ሁሉ ተጨናንቆ አንዳንድ ሬሳና ቁስለኛ እየረገጠ የሚያመልጥ ግማሾቹ ለሁለት ወይም ለሦስት የጋማውን ከብት የተቀመጡ አንዳንዶቹ በራሳቸው መሔድ ያቃታቸው የከብቱንም ጭራ እየጐተቱ የሚራመዱ ነበሩ ። በዚህም ጊዜ ከኋላ እየተተኮሰበት አንዳንዱ ይወድቃል . . . ቀበሌው ሁሉ በጠላት ቁጥጥር ውስጥ ስለሆነ ፥ ሁሉም ራሱን ለማዳን በሚሸሽበት ጊዜ ወደኋላ የነበረው ጄኔራሉ (ዳቦርሚዳ) ጠፉ ።. . . እኔም ወደኋላ ተመልሼ ብፈልገው አጣሁት ። ሼዎቹም ለድሉ እርግጠኛ ስለሆኑ ጥይት ስላለቀባቸው ይሁን ወይም ስለደከማቸው የማሳደዱን ነገር ትተው ሬሣና ቁስለኛ ይገፉፉ ግማሾቹም ምርኮኛ ይሰበስቡ ጀመር ። ጊዜው መሸ ። ከዚያ እንደምንም በየሸለቆው የሞተውን ፥ ከፉኛ የቆሰለውን አልፈን 300 የምንሆነው በመጋቢት 4 ቀን (እ.ኤ.አ.) አዲ ቀይህ ገባን ። [1]

ስለ ጄኔራል ዳቦርሚዳ አሟሟት ከጦርነቱ በኋላ ተማርኮ አዲስ አበባ የነበረው ጄኔራል አልቤርቶኒ ለቤተሰቦቹ በጻፈው ማስታወሻ ላይ ፥ “የጄኔራል ዳቦርሚዳን በጦርነቱ ላይ መሞት የራስ ሚካኤል ሹማምንትና በኋላም ራስ መኰንን ከአድናቆት ጋር እንዳረጋገጡልት ፥ የሰላሙ ውል ከተፈጸመ በኋላ ፡ ምኒልክ ሻምላውንና ያንገት መጠምጠሚያውን ‘ለቤተ ሰቡ ስጥለት’ እንዳሉት ፥ ስለአሟሟቱ ደግሞ ወደማታ መቶ ከሚሆኑ ተራፊ ጣልያኖች ጋር ባንድ ጉብታ ላይ ሆኖ እየተታኮሰ በጠላቶቹ ላይ ጉዳት ሲያደርስ ቱርክ ባሻ (ታምሬ) ከኋላ ካለው ከፍተኛ ቦታ ሆኖ አነጣጥሮ ከመታውና ከጣለው በኋላ ሮጦ ሔዶ እንደ ገፈፈው ፥ ጥሩ አድርጎ ፈረንሣይኛ የሚናገረው ግራዝማች ዮሴፍ አጫወተኝ”[2] ሲል ያረጋግጣል ።

በዚህ ዐይነት ፥ የዳቦርሜዳ ገዳይ በትክክል መጠሪያ ስማቸው ባይጠቀስም ቱርክ ባሻ ታምሬመ ሆናቸው ነው ። ምናልባት በኮንቴ ሮሲኒ ጽሑፍ በስሕተት ባሻ ገብሬ ያለው ቱርክ ባሻ ታምሬ ለማለት ይሆናል።

---

1 Adua, E.Bellavita, PP. 380—390.

2 Lettere e Diari . . . P.80 .





በዓድዋ ጦርነት ላይ የሞተው ጄኔራል ዳቦርሚዳ

ከማዙኮኒ

# ምዕራፍ ዐርባ ሦስት

## የዳግማዊ ምኒልክ ከጦሩ ግንባር ወደ ሠፈር መመለስ

ከዋናው የዓድዋ ጦርነት ወዲህ እስካሁን በዝርዝር የተመለከት ነው ፡በጽሑፍ ማስረጃ እንደልብ የሚገኝበትን የኢጣልያኖችን ወገን ነው ። ምንም እንኳን ሰነድ ያነሰና የተበታተነ ወይም በዘመኑ ተዘርዝሮ በመታተም በደንብ ለጊዜያችን ያልተላለፈ ቢሆንም ፡ በመጠኑ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፡ ግራዝማች ዮሴፍና ነጋድራስ አፈወርቅ በየመልኩ የተዉልን ማስታወሻ መሠረታዊ ሰነድ ነው ። በተለይ የንጉሠ ነገሥቱ አስተርጓሚ የነበሩት ግራዝማች ዮሴፍ በጦርነቱ ቦታ ተገኝተው ለሞንዶን ቪዳዬ በራፖር መልክ ያስተላለፉት ጽሑፍ ከዚያ በፊት ያልታተመ በመሆኑ በመጠኑ ዝርዝር አሳብ ስላለበት በታሪክ ፊት ጠቃሚነቱ ግልጽ ነው ።

በዚህ ሰነድ ውስጥ ግራዝማች ዮሴፍ ፡ በመሠረታዊውና በታሪካዊው ጽሑፍ ውስጥ አገራቸው ትግሬ መሆኑንና የደጃች አርአያ ዘመድ መሆናቸውን ጭምር ጠቅሰው ማዣር ሳልሳን ለእርቅ ከአሥመራ ወደ እንትጮ ሲመጣ ከፊታውራሪ ደሳለኝ ጋር ሔደው መቀበላቸውን ያረጋግጣሉ ። እኝህ ሰው ከቀድሞ ጀምሮ ዐፄ ምኒልክን ባስተርጓሚነት ያገለገሉ ከመሆናቸውም በላይ ፡ ከወንድማቸው ከጊዮርጊስ ንጉሤ ጋር ወደ አሰብና ወደ ኤደን እየተመላለሱ በመሣሪያ መሰብሰቢያው ጊዜ ሲሠሩ ቆይተው እንደዚሁም በውጫሌው ውል በተነሣው ሰፊ ክርክር ሁሉ ከራስ መኰንን ጋር ተካፍለዋል ።

እኝሁ ሰው ራስ መኰንን ፡ የኢጣልያን አገር የጐበኙ ጊዜ ከተከታዮቻቸው ውስጥ ብዙዎቹ በዘመኑ አነጋገር የራስ ሎሌዎች ሲሆኑ ፡ ግራዝማች ዮሴፍ ብቻ በቀጥታ ያፄ ምኒልክ አስተርጓሚና ሎሌ ናቸው ።

አሁንም ግራዝማቹ ፡ በጦርነቱ ሰዓት ከንጉሠ ነገሥቱ ምን ጊዜም ሳይለዩ በዋናው ሥራቸው ባስተርጓሚነቱ ላይ የጦርነቱን ሁኔታ እየጻፉ ፡ አዲስ አበባ ላሉት ለነሞንዶን በማስተላለፍ በነርሱም አማካይነት በፈረንሣይኛ ጋዜጣ እንዲታተም ማድረጋቸውን ከመቀጠል አላረፉም ። ከዚህ በፊት እንደ ጠቀስነው ፡ የርሳቸው ጽሑፍ በኛ ዘንድ ያሰው ጠፍቶ ሊገኝ የቻለውም የጻፉለት ሙሴ ሞንዶን አዲስ አበባ

በነበረበት ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱና ከየመኳንንቱ የተጻጻፏቸውን ደብዳቤዎች በማጠቃለል አጠራቅሞ ከኢትዮጵያ ከወሰዳቸው ከሌሎች መጻሕፍት ጋር ለፓሪስ ቤተ መጻሕፍት የሰጠውና በቁጥር 82 ተመዝግቦ የተቀመጠው ነው ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፥ ካህናትና ሴቶች ሳይቀሩ ባንድነት አስተባብረው ኢትዮጵያውያንን ባንድ እግር አቁመው ፥ በአገር ወራሪ ፊት አሰልፈዋል ። ቀኑን ሙሉ በማዋጋት ይኸን ዓለም የተደነቀበትን ድል ባገኙበት ማታ ወደ ሰፈራቸው ሲመለሱ ፥ አዲ ፈቂ ጉታ ላይ ወጥተው በእንዳ ስንበት ቤተክርስቲያን ገብተው ይኸን ድል ለሰጣቸው እግዚአብሔር ምስጋና አቅርበዋል ። አዲ ፈቂ በእንዳ ኪዳነ ምሕረት በመነኩሲይቶ ተራራ መካከል የሚገኝ ነው ። የአዲ ፈቂም ተራራ ከባሕር ከፍታው 2062 ሜትር[1] ነው ። ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ወደዚህ መሔድን የመረጡት ምናልባት ጦርነቱ የተደረገው የካቲት 23 ቀን እሑድ ስለሆነ ፥ የአዲ ፈቂ ቤተ ክርስቲያን እንዳ ስንበት (የሰንበት ቤተ ክርስቲያን) ስለሆነ ፥ 'ዕለተ ሰንበት የለቱ ስት ቀናኝ' በሚሉ እምነት ይሆናል ።

ከዚያ ወርደው ሠራዊቱ ፥ "እየገደለ ሰጠው ላሞራ! " እያለ በሆታ እያጀባቸው ፥ በደስታና በእልልታ ወደ ሰፈራቸው ደረሱ ። ወደ ድንኳናቸው ገብተው በዙፋናቸው እንደ ተቀመጡ ፥ ጦርነቱን እንደ ወንድ በትጋት የተካፈሉት የሚወድዋቸው ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ በኢትዮጵያ ልማድ ለዝግና ፥ ለገዳይ እንደሚደረገው ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ተቀመጡበት ዙፋን ቀርበው ፥ እጅ ነሥተው የድል አድራጊነት ምልክት የሆነውን የወርቅ ሎቲ በጕሮአቸው አንጠለጠሉላቸው[2] ።

በማግሥቱም ፥ በዓድዋና በአክሱም ዙሪያ ያሉ ካህናት ለድሉ በዓል ተሰብስበው ነበርና ምራቱ በቅድሚያ ለአክሱም ካህናት ስለ ተሰጠ ፥ ካህናቱ ከድጓ ውስጥ "ሞዖ ለሞት በዓሮ ለጣእት ወገብረ ትንሣኤ በሰንበት"[3] የሚለውን ጥቅስ ገሠው አዜሙ ። ምስማክም "አንተ ቀጥቀጥኮ አርእስቲሁ ለከይሲ ወትሁቦሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ" የሚለው ከዳዊት መዝሙር ተዘመረ ።

1 Guida deil' Africa Orientale, P.224.
2 Storia di Etiopia ,Conti Rossini, P.449
3 የድጓው ትርጉም "ሞትን አሸነፈ ጣኦትንም ሻረ ፥ በሰንበትም ትንሣኤ አደረገ" ተብሎ ለጌታችን በጳውሎስ የተነገረውን ለምኒልክ ለማውረስ ነው ። ጢሞቴዎስ ምዕ.1 ቁ. 10 ፥ ዕብ.2 ቁ. 14



በአዲስ አበባ ገና የጦርነቱ ወሬ ሳይሰማ ውጊያውና ድሉ በተፈጸመበት ቀን የጊዮርጊስ ለት የቤተ ክርስቲያኑ አለቃ መምህር ጽጌ የሚባሉት ሊቅ የተቀኙት መወድስ ቅኔ እንደ ትንቢት ሆኖ ተደንቆላቸዋል ። ቅኔው ታሪካዊ ስለሆነ እንደሚከተለው አስፍረነዋል ።


በሕፃነ ምኒልክ ይረፍቅ ሰማዕተ ልዕልና
ወበሕፃነ ሰማዕት ይትሐወስ አሰረ ምኒልክ ላዕክ
እስመ እም ሮምያ ፈተተ አድባረ ድንጋጼ ወሀውክ
ምኒልክ ንጉሠ አድኅና ዘኢየር መልአክ
ወእግረ ምኒልክ ኢይትሐወክ
እስመ በቅድሜሁ የሐውር ጸያሔ ፍኖት ወልደ አምላክ
ቡርክትሂ ገነተ ጽጌ እስመ ውእቱ ቡሩክ
ዓለመ ምኒልክ ቀዳማዊ ዘይመጽእ ምኒልክ
ወሎቱ ሶርያ ትሰግድ ወታስተበርክ
በጽባሀ እስመ ቀርበ ሙስና ሮምያ መሥዋዕተ ሠርክ[1]

በሙሉ ሁሉን መተርጐሙ ምንም ያህል ስለማይጠቅም ፥ ከሙሉው አንዳንዱን ፍሬ ነገር ግዕዝ ለማያውቁ እናብራራለን ። አምስተኛውና ስድስተኛው ሐረግ ፥ "ወእግረ ምኒልክ ኢይትሐወክ ። እስመ በቅድሜሁ የሐውር ጸያሔፍ—ኖት ወልደ አምላክ" "መንገድ ጠራጊው ወልደ አምላክ በፊቱ ስለሚሔድ ፥ የምኒልክ እርምጃ አይደናቀፍም" ማለት ነው ። ወልደ አምላክ የራስ መኰንን የክርስትና ስም ስለሆነ ፥ መኰንን ግንባር ቀደም ጦር አዝማች እየሆኑ በአላጌና በመቀሌ እየተዋጉ ለንጉሠ ነገሥቱ የጦርነት ጉዟቸውን ያቀኑትን ለመጥቀስ ነው ።

ከሁሉ የቅኔ ሐረጐች የመጨረሻው መስመር ፥ "በጽባሀ እስመ ቀርበ ሙስና ሮምያ መሥዋዕተ ሠርክ" "የሮማ ጥፋት እንደ ዕለት መሥዋዕት በጧት ቀርቧል" ያሉት ለባለቅኔው እንደ ደንበኛ ትንቢት ተቆጥሮላቸዋል ። በእርግጥም ግንባር ቀደም ሆኖ በጧት ግሥጋሤ ደርሶ የተማረከው የጄኔራል አልቤርቶኒ ጦር የተመታውና የኢጣልያ ጦር ቅስሙ የተሰበረው ከጧቱ ላይ ስለሆነ ፥ "በጽባሕ እስመ ቀርበ ሙስና ሮምያ . . ." ብለው የጦርነቱ ዕለት የጦርነቱን ወሬ ኀይሰሙ የተቀኙትና በተግባር የተፈጸመው በትክክል ተገናኝቷል ። አዲስ አበባም እንደገቡ ዐፄ ምኒልክ ይኸንኑ ሰምተው ሸልመዋቸዋል ይባላል ።

1 መጽሐፈ ቅኔ ብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ገጽ 255

## የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት የተዋጋበትን የዓድዋንና የአካባቢውን ሠፈር የሚያሳይ ሠሌዳ




ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ — ጳ ፡ ት ፡ ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ ፡ ምዕ ፡ 62—63 ገጽ 242—268
ITALIA ED ETIOPIA CC. ROSSINI. PP. 344—447 GLI ITALIANI IN AFRICA— A. DEL BOCA. PP. 649—691

# ምዕራፍ ዐርባ አራት

## በዓድዋ ጦርነት ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱትና የቆሰሉት

የኢትዮጵያውያንን ዠግንነት ፡ አንዳንዶቹ ጣልያኖች ሲያደንቁ አብዛኞቹ በከንቱ ለማስተባበል ይሞክራሉ ። ሲጽፉም የተገላቢጦሽ የነርሱን የተሸነፉትን አንዳንዱን የጦር መኰንኖቻውን ፡ "በዠግንነት ተዋግቶ ሞተ ፤ አገሬን የመሰለ አርበኛ በሚያስደንቅ አኳኋን እየተዋጋ ወደቀ" ሲሉ ፡ የኢትዮጵያውያንን ዠግንነት ግን ፡ "እንደ አውሬ እየተጯጯሁ መጡብን ፡ ፊት ለፊት ጕራዴ መዘው ከመድፋችን ላይ ሲወድቁ ዐይን የላቸውም" በሚል ማጥላላት ባለበት አነጋገር ሲገልጹ ይፈልጋሉ ። በጥቂቶቹ በኢትዮጵያውያን ዠግንነት ተሸነፍን ማለትን በመሰቀቅ የተሸነፉበትን ሰበብ ወደሌላ አቅጣጫ እየመሩ ፡

፩ኛ. የዠኔራል አልቤርቶኒ ግንባር ቀደም ጦር በፕላን የተመደበለትን ሥፍራ አልፎ ስለዘለቀ ፤

፪ኛ. አልቤርቶኒ በሚዋጋበት ጊዜ ሌሎች ዳቦርሚዳና አሪሞንዲ ለየራሳቸው ድልን በመመኘት ለእርዳታ ሳይደርሱለት ስለቀሩ ፡

፫ኛ. ከአገር ተወላጅ በቁጥር የሚበልጡት የነጭ ወታደሮች በተለይ በቅርብ የመጡት በማያውቁትና ወጣ ገባ በሆነ መንገድ በሌሊት ጉዞ ስውነታቸው ስለደከመ ፡

፬ኛ. በወታደር ቁጥርም ፡ የኢጣልያን የወታደር ቁጥር የኢትዮጵያ አራት ጊዜ ስለሚበልጠው እያሉ ልዩ ልዩ ምክንያት መስጠታቸውን ባለፈው ተመልክተነዋል ።

በጦርነትም ሆነ በስፖርት የውድድር ግዳ የተሸነፈ ወገን ፡ ሁልጊዜም ምክንያት አያጣምና ሊያስደንቅ አይገባም ። ቢያሸንፉ ኖር ይኸ ሁሉ አሁን የተሰጠው ምክንያት ይቀርና ሌላ የዠግንነት ልዩ ቀለም እየተሰጠው ድል የማድረጉ ዝና ከበቂ በላይ በተጋነነ ነበር ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ፡ በቁጥር የኢትዮጵያ ወታደር ቢበልጥም በዝግጅትና በጠቅላላ የጦር ትምህርት ዕውቀት ኢጣልያኖቹ ስለሚበልጡ ፡ በቁጥር ማነሳቸውን ያላቸው ሥልጣኔ ሊክሰው በቻለ ነበር ።

ቢሆንም ብዙ የኢጣልያ የጦር መኰንኖች ከጀኔራሎቻቸው ጋር በጀግንነት እየተዋጉ መሞታቸውን ማንም ሊክድባቸው አይገባም ። በዓድዋና በአካባቢው ፣ በየሜዳውና በየሸለቆው የተረፈረፈው ሬሣ ራሱ ምስክር ነው ። ዠግና ከሁለቱም ጦር ሠራዊት ውስጥ መኖሩን ሳንዘነጋ ፣ ይኸን ስመ ጥር ድል ያወረሱን ያባቶቻችን ዠግንነት ምንጊዜም የሚረሳ አይደለም ። በውጊያው ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተካፋይ ሆኖ የሕይወቱን መሥዋዕትነት በመክፈል አንጸባራቂ ድል አግኝቷል ።

እያንዳንዱ ጀግና ግዳጁን በጥንቃቄ ባያከናውን ኖሮ ይህ አኩሪ ድል ባልተገኘ ነበር ። ከሞቱትና ከቆሰሉትም ውስጥ የማናውቃቸው ስለሚበዙ ፣ ስማቸውንና ዠብዱቸውን ለትውልድ ለማስተላለፍ ብንመኝም አልሆነልንም ። ቀድሞውን በዘመኑ በማስታወሻ ስላልተላለፈና በዚያን ዘመን ጦርነቱን የተካፈሉት በሕይወት ስለሌሉ እንደዚሁ መቅረቱ ያሳዝናል ። በዠግንነት ከሞቱት መካከል ያንዳንዶቹን በተለይ የመኳንንቱን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በተዉልን መጽሐፍ ላይ ስማቸውና አሟሟታቸው ባጭሩ የተጠቀሰው ከዚህ ቀጥለው ያሉት ናቸው ።

ሀ/ ደጃች በሻህ አቦዬ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ደፋር ይባላል ። የዐፄ ምኒልክ አክስት የወይዘሮ አያህሉሽ ልጅ ፣ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ፣ የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስና የደጃች ሰማ አቦዬ ወንድም ናቸው ። ባገልግሎት ከወንድማቸው በኋላ ፣ ንጉሥ ከተባሉት ከራስ ወልደ ጊዮርጊስና ከነራስ መኰንን አያንሱም ። ምናልባት እነዚህ ዝንባሌያቸው ወደ አስተዳደር ጭምር ሲሆን ፣ በሻህ መንፈሳቸው ፍጹም ወታደራዊ ይመስላል ። ታናሽ ወንድማቸው ወልደጊዮርጊስ ራስ ሲባሉ የርሳቸው በደጃዝማችነት መቆየት ሰበቡ ይኸው ይሆናል ።

በ1870 ዓ. ም. ዐፄ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ዐፄ ምኒልክን ለማስገበር የመጡ ጊዜ ካፄ ምኒልክ አሽከሮች ጠና ጠና ያለው ፣ “ዛሬ ዐፄ ዮሐንስን በጦር ትጥቅ እንችልምና አሁን ገብረን እኛም ወደፊት መሣሪያ ሰብስበን በሚመች ጊዜ እምቢ እንላለን” ሲል ፣ እንደ በሻህ አቦዬ ያሉት ጉበዛዝቱ የጦር መኰንኖች “እንበለው!” እያሉ ይፎክሩ ነበር ። በፉከራም ጊዜ ፣ “ካፄ ዮሐንስ ጦር ሃምሳ ባለሰናድር ማርኬ እመጣለሁና ተዋሰኝ” የሚል ኖሯል ። በዚያው ሰሞን የዕርቁን ጉዳይ ለመጨረስ ደጃች ናደው በሚመላለሱበት ጊዜ ደጃች በሻህ አቦዬ ያፄ ዮሐንስ ሠራዊት በሜዳ ላይ ሲጓዝ አይተው እልህ ይዟቸው ፣ “በማን አገር ሜዳ እንዲህ ሆነህ ትጓዛለህ” ብለው በፈረስ ጋልበው ሔደው አንድ ባለ ቀሚስ ገድለው ተመለሱ ። በዚህም ምክንያት ፣ “ለሃምሳ ሰናድር



ዋስ የጠራችሁ ፣ በሻህ አቦዬ ከፈለላችሁ” ተብሎ በሰንጉ ሞት ተገጥሞላቸዋል ።

ከነራስ ጕበና ፣ ከነራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር ዳር አገሩን እያቀኑ በግራኝ ወረራ ምክንያት ተነጣጥለው በየባላባቶቻቸው እየተገዙ ይኖሩ የነበሩትን እውራጃዎች እንደገና ለማዋሐድ ዐፄ ምኒልክ በሚያደርጉት ዘመቻ እርሳቸውም ከመጀመሪያዎቹ ጋር ሆነው የከፋንና የጌራን ሕዝብ በማሳመን ወገን ከወገኑ እንዲደባለቅ አድርገዋል ። በዚሁ ምክንያት ፣ ደጃች (በኋላ ንጉሥ) ወልደ ጊዮርጊስ ሲሙን ፣ ደጃች (ራስ ቢቶደድ) ተሰማ ናደው ኢሉባቦርን ሲያስተዳድሩ ፣ ደጃች በሻህ አቦዬ ጌራና ከፋ ተሰጥቷቸው ነበር ። ስለዚህ የደጃች በሻህ አቦዬ አንዱ ጉብዝናቸውን የሚያመለክተው በዚያን ዘመን ከነበሩት ከደጃች ኃይሌ አንዳርጋቸው ጋር በማመሳሰል ፣ “ከጉበዞቹ የምናውቃቸው በሻህ አቦዬ ፣ ኃይሌ አንዳርጋቸው” ተብሎ የተገጠመላቸው ነው ።

የበሻህን ሞት እቴጌ ጣይቱ ሰምተው በሐዘን እንዳስቀሱላቸው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ጠቅሰው ከዚሁ በማያያዝ ስለደጃች በሻህ አቦዬ አሟሟት ፣ “ታላቅ የመኰንን እርበኛ የንጉሠ ነገሥቱ ያክስትዎ ልጅ ደጃዝማች በሻህ የፈረሱ መሪ አባ ደፋር ተብሎ በውነት ስሙ የተጠራው . . . ካልጋ ወርዶ ከበቅሎ ላይ ፣ ከበቅሎ ወርዶ ከፈረስ ላይ ሆኖ ተቀማጥሎ ያደገው ባለመጣብር ፈረሱን ሐያ ሁለት ቃዳ መሬት የሚራመደውን ለጓሚ* ይዞበት ባንድ ወገን ሔደ ። በእግሩ ሲሮጥ የወታደር ፈረስ ተውሶ ከአባራሪ ላይ ወደቀ” 1 ሲሉ በራሳቸውና በዘመኑ አነጋገር ገልጸውታል ።

ስለዚህ ፣ ጦርነቱ እንደ ተጀመረ ከመድፉና ከጠበንጃው ተኩስ ብዛት የተነሣ ግርግር ሆኖ በግርግሩ ላይ የጭናቸውን በመጣብር ያጌጠውን ፈረሳቸውን የያዘው እሽከር ባንድ ወገን ሔዶ ስለጠፋ ፣ በግራቸው ሲሮጡ አንድ ወታደር ምናልባትም ከጭፍሮቻቸው አንዱ ሊሆን ይችላል ፣ ፈረሱን ሰጥቷቸው በርሱ ላይ ተጋብተው እያባረሩ ጠላትን ሲወጉ ተመትተው ወደቁ ። ተዋግተው የሞቱት ከዠኔራል አልቤርቶኒ ጦር ጋር በእምባ ኪዳነ ምሕረት ላይ በተደረገው ጦርነት ነው ። በርሳቸው ሞት የተናደዱ ጭፍሮቻቸው በቁጭት ብዙ የኢጣልያ ምርኮኛ ገደሉ ይባላል ።

---

* ለጓሚ ማለት በቅሎ ወይም ፈረስ እየሜነ ፣ እያራገፈ ፣ እየቀለበ የሚኖር ተከታይ አሽከር ነው ። ከዛሬው የመኳንንት ሹፌር ጋር ሊመሳሰል ይችላል ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 266

ለ/ ከደጃች በሻህ አቦዬ ጋር በዚሁ ቀንና ስፍራ በጀግንነት ተዋግተው የሞቱ የጉላው ገዥ ደጃዝማች ሜጫ ናቸው ። የርሳቸው የጀግንነት አጓጓት ባጭሩ እንኳ ዝርዝር የለንም ። ሲዘምቱ የጉላን ጦር ይዘው ነው የዘመቱት ፤ በዘመኑ የጉላ ጦር አስፈሪ ነበር ። ሠፈሩ አዲስ አበባ የጉላ ሠፈር የሚባለው ነው ። እርሳቸውም የነደጃች ተሰማ ፣ የነደጃች ብርቄ አባት ናቸው ። በአገልግሎት ዕድገት ያገኙ የመናገሻ አርሞ ናቸው ይባላል ። ጉላ በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ የሚገኝ በዚያን ጊዜ ባለነጋሪት ደጃዝማች የሚሾምበት ታላቅ ወረዳ ነበር ።

ሐ/ ደጃች በሻህና ደጃች ሜጫ በሞቱበት የጦር ግንባር ስመጥሩው የንጉሡ የጦር አበጋዝ ፊታውራሪ ገበየሁ አባ ጐራ ሞተዋል ። እርሳቸውም ዐፄ ምኒልክ ሐረርጌ ከአሚር አብዱላሂ ጋር ከዘጠኝ ዓመት በፊት በ1879 ዓ.ም. የተዋጉ ጊዜ ሻቃ ገበየሁ እየተባሉ ጦርነቱን ተካፍለዋል ።

በ1881 ዓ.ም. ሻቃ ገበየሁ የሰናድር ያዥዎች ሹም እንደ ነበሩና በውስጣቸው የሚያዙት ጦር ቁጥሩ 3000 እንደነበረ በጣልያኖች የባሕር መዝገብ (ሊብሮ ቨርዴ-ቅጠልማ መጽሐፍ) ተጽፎ ይገኛል ።[1] በግዛት አንድ ጊዜ አማግርትን ፣ ሌላ ጊዜ የጉራጌን አውራጃ ተሹመው አስተዳድረዋል ። የትውልድ አገራቸው ተጉለት ነው ይባላል ። መቃብራቸውም እንጉለላ ኪዳነ ምሕረት ነው ።

በዚህ ዓመት አላጌ ላይ በተደረገው ጦርነት ዋናው የድሉ ባለቤት እርሳቸው እንደነበሩ በዚያው ምዕራፍ ላይ አመልክተናል ። የመቀሌውንም ጦርነት በደንብ ተካፍለዋል ። እንዲያውም ራስ መኰንን የዕርቅ ነገር በሚነጋገሩበት ጊዜ ገበየሁ እየተዋጉ ስላስቸገሩ ፣ እንደ አላጌው እንዳይዋጉ ራስ መኰንን አስረዋቸው ሳለ ፣ በኋላ ላይዋጉ አስምለው እንደ አስለቀቋቸው ከኢጣልያኖቹ ወገን የተጻፈው መጽሐፍ ያረጋግጣል ።[2] ከብዙ ጦርነት በኋላ ፣ በስምምነት ጋልያኖ ጦሩን ከምሽግ ይዞ ወጥቶ በራስ መኰንን ሠፈር አጠገብ እርሱና ሹማምንቱ የሰፈሩ ጊዜ ፣ "የአላጌውን የሐበሻ ጀግና የፈረንግይ ጋዜጠኞች በጣም ያወደሱትን ፊታውራሪ ገበየሁን አይተውታል"[3] ሲል ማንቴጋዛ የሚባለው ጸሐፊ ጠቅሶታል ።

ፊታውራሪ ገበየሁ ፣ የዓድዋ ጦርነት ለት በምን አኳኋን እንደሞቱ ኢጣልያዊው ጸሐፊ፣ "በአምባ ኪዳነ ምሕረት ላይ ጧት ከጄኔራል

1 Assedio di Maccalle. V. Mantegazza, P.260
2 Italia ed Etiopia P.P. 242—243
3 Assedio di Maccalle . . . , 413.



አልቤርቶኒ ጦር ጋር በተደረገው ውጊያ የኢጣልያኖቹ መድፍ ክፉኛ ባጠቃበት ሰዓት ወታደሩ ማፈግፈግ ቢጀምር ለወታደሩ "ወደ ሸዋ የሚመለሱ ፣ የአላጌው ጀግና ፊታውራሪ ገበየሁ በምን አኳኋን እንደሞተ ይናገሩ" ብሎ ጮኸ ። "እንደ አንበሳ ተወርውሮ በጦርነቱ ላይ ገባ ። በዚያን ጊዜ በመትረየስ ተመትቶ በ3 ሰዓት ላይ ወደቀ" ያለውን እናስታውሳለን ። ከዚሁ አያይዞ ከመሞቱ በፊት ጥፍሮቹ እንሥተው አንድ ቁጥቋጦ ውስጥ ከበውት እንደ ነበረ የተማረከው ኢጣልያዊ የጦር መኰንን ቲኔንቲ ካሩሶ የሚባለው ባበሾቹ እጅ እንደ ተያዘ ማየቱን አመልክቷል ።[1]

ስለገበየሁ አጓጓት ዦዎቫኒ ቴዶኒ የሚባለው የጦር መኰንን ፣ ተማርኮ እስከ አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ የነበረው በጻፈው ማስታወሻ ላይ በበኩሉ ከላይኛው አባባል በትንሹ ለየት አድርጎ እንደዚህ ይላል ። "... በቢያንኪኒና በማሶቶ *በሚመሩት መድፎች እየተመቱ አበሾቹ ወደኋላ ሲያፈገፍጉ አይቶ ፣ ፈሪ ሁሉ እንዴት ትሸሻላችሁ ፣ እኔ እንዴት እንደምሞት ለንጉሡ ሐዳችሁ ንገሩ ብሎ ፈረሱን ባለንጋ በትር አስነሥቶ በግልቢያ በሚዘንመው የመድፍ ጥይት መካከል ገባ ። እርሱን ሲያይ ሁሉም እየሮጠ ተከትሎት ገብቶ ከመድፈኞቹ ጋር ተጨፋጭፎና ገድሎ መድፎቹን ማረከ ። የገበየሁ ሬሣ ከወደቀበት ቦታ የኛዎቹም የጀግኖች ሬሣ አብሮ በመውደቅ የርሱን ሬሣ አከበረው" በዚያው ሰሞን ምርኮኛ በመሆን በንጉሠ ነገሥቱ ሰፈር ሳለ ባይኑ እንዳየው ፣ ስለገበየሁ ሰው ሁሉ ያለቅስ እንደነበረ ፣ ከዕለታት አንድ ቀን ከሞት የተረፈው በያለቃው ተሰልፎ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሲያልፍ ፣ የፊታውራሪ ገበየሁን የተጫኑ በቅሎ የገዛ ወጣት ልጁ ይዞ (ተቀምጦ) ሲያልፍ ምኒልክ አይተው ማልቀሳቸውን ያረጋግጣል ።[2]

ስለዚህ ፣ የአላጌውን ምሽግ በመስበር በኢጣልያ ላይ የመጀመሪያውን የድል ደወል ያሰሙት ፣ የመቀሌን ጦርነት በመካፈል እጃቸው የቆሰለው ፣ አበጋዙ ፊታውራሪ ገበየሁ አባጐራ የዓድዋ ለት ወደር በሌለው ጀግንነት ላገራቸው ነጻነት ፣ ለሚወዷቸው ንጉሠ ነገሥት ክብርና ፍቅር ሲሉ ሕይወታቸውን ሠውተዋል ። በዚያን ጊዜም ፣ "የዐድዋ ሥላሴን ጠላት አረከሰው ገበየሁ በሞቱ ግባና ቀድሰው" ተብሎ ተገጥሞላቸዋል ።

መ/ ፊታውራሪ ተክሌ የወለጋው ገዥ ያፄ ምኒልክ ልጅ የደጃች

1 Italia ed Etiopia . . . ,PP. 251, 368—369.
* Pianchini & Masotto የሚባሉት ሁለቱ የመቶ አለቆችና የመድፈኛ ክፍል ሹማምንት ናቸው ።
2 Riccordi di un Prigioniero di Menelik, Giovanni Tedone, PP.142—143

አስፋው ወሰን ሞግዚት የነበሩት ናቸው ። እንደነፊታውራሪ ገበ የሁ ዳኄ ምኒልክ የቆዩ የጦር መኰንን ናቸው ። በ1881 ዓ.ም. ሜጫን ይገዙ እንደነበረ በኢጣልያኖች ማስታወሻ ይገኛል[1] ። የወሎጋ ገዥ ሳሉ በዐዋጁ መሠረት ጦራቸውን አስከትተው አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ፣ በራስ መኰንን ጦር ውስጥ ግንባር ቀደም ሆነው የአላጌን ጦር ነት ከነፊታውራሪ ገበየሁ ጋር ተካፍለዋል ። የዓድዋ ጦርነት ዕለትም እንደነፊታውራሪ ገበየሁ ጢት በተደረገው ውጊያ ላይ በዠግንነት ወድቀዋል ።

ሠ/ ቀኛዝማች ታፈሰ ዓባይነህ ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ትንታግ ነው ። በዓድዋ ዘመቻ ዕድሜያቸው 25 ዓመት ነበር ። በዕድሜ ወጣት ቢሆኑም ዠግንነታቸው ከፊታውራሪ ገበየሁ ጋር በመጠኑ ተመሳሳይ ነው ። በግዛታቸው በማረቆ ሲኖሩ በአደን ስመ ጥሩ ስለነበሩ ወደ አዲስ አበባ በመጡ ቁጥር የዝሆን ቀንድ ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀርቡ እንደ ነበር ፣ በውጊያ ጦርጦራ ወታደር ፣ ለሁሉ ሥራ ከተፎ ሥል ጡን ስለነበሩ ላስቸጋሪው ሥራ ሁሉ ዐፄ ምኒልክ "ታፈሰን ጥሩ" ይሉ እንደነበር ፣ ብርታታቸውንና ጠንካራነታቸውን እያዩ "ይሞትብ ኛል" እያሉ ንጉሠ ነገሥቱ እጅግ አጥብቀው ይሳሱላቸው እንደነበረ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በመጽሐፋቸው ጠቅሰዋል ። በአላጌ ጦርነት በከፍተኛ ዠግንነት እንደ ተካፈሉ ተመልክተናል ። በዚሁ ጦርነት ሃምሳ የሚሆኑትን ጣልያኖች ባንድ ጐራዴ እንደ ጨፈጨፉ ፣ አንድ ላይ ቆመው የተኮሱት አየር (ቀለሀ) እንደ አርበጫ (ኩይስ ቁልል) እንደ ተቆለለ ፣ በአሁኑ በዐድዋ ጦርነት ስሞን መነጽር ይዘው ከጭፍሮቻቸው ጋር ወደፊት እየዘለቁ በየተራራው ላይ ሆነው የኢጣ ልያኖችን ከምሽግ መውጣትና አለመውጣት ቃፊር ሆነው በመጠባበቅ አንዳንድ ጊዜም በርከት ብሎ ከወጣ የነጭና የባሻ ብዙቅ ወታደር ጋር ተገናኝተው በመዋጋት ግዳይ ዳኄ ምኒልክ ይጥሉ እንደነበረ ጸሐፊ ትእዛዙ አመልክተዋል ። ከዚሁ አያይዘው የኢጣልያኖቹን ከምሽግ መውጣት በመጀመሪያ ለንጉሠ ነገሥቱ በፈረስ ጋልበው ያስረዱ እርሳቸው እንደነበሩ ከገለጹ በኋላ ፣ የዓድዋ ጦርነት ለት ስለ አሟሟታቸው እንደዚህ ብለዋል ። "አድኅ ያልጨረሰው ቀኛዝማች ታፈሰ እንኳን ሰውና የውድማ ዝሆን ሲፎክር ድምጡን ሲሰማ ይጨ ነቅ የነበረው ተኩሶ ሲጥል በጐራዴ ሲመታ ፣ ከሁለተኛው ሰልፍ ሰማዕታ ከሚባለው አገር ሲደርስ ከንዱን ቆሰለ ። በቆሰለም ጊዜ አሽ ከሮቹ እንግዲህ ከጥላ ሥር እናሳርፍህ አሉት ። እርሱ ግን ለኢጣልያ ወታደር እንዱ እጂ ይበቃል ብሎ ሲያባርር ከዚያ ላይ ወደቀ. . ."

1 Assedio di Maccalle . . . P.260.



በማለት ጽፈውላቸዋል[1] ።

በዚህ ዓይነት ቀኛዝማች ታፈሰ አባይነህ ተዋግተው የሞቱት ፣ በረዓዮ ተራራ በማይ እጋምና በሰማዕታ በኩል ከዘመተው ከዠኔራል አሪሞንዲና ከተጠባባቂው ከዠኔራል ኤሌና ጦር ጋር በተደረገው ውጊያ ላይ ነው ። ተመትተው የወደቁትም ከሰማዕታ ጉብታ አጠገብ መሆኑ ነው ። ቀኛዝማች ታፈሰ ዓባይነህ የልዑል ራስ እምሩ አጐት ያባታቸው የደጃች ኃይለ ሥላሴ ታናሽ ወንድም ናቸው ።

ረ/ ፊታውራሪ ዳምጠው ፣ የፈረስ ስማቸው አባ ሸኘው የራስ ደስታና የማዦር ዤኔራል አበበ ዳምጠው አባት ናቸው ። በ1881 ዓ.ም. እነፊታውራሪ ገበየሁ ሻቃ እየተባሉ ስናድር ያዥን ሲያዙ ፣ እርሳቸው ባላምባራስ ተብለው የፈረሰኛ ዘበኛ አለቃ ነበሩ ። በኋላ የፊታውራሪነት ማዕረግ አግኝተዋል ።

እንደ ጸሐፊ ትእዛዝ አጻጻፍ ፣ ፊታውራሪ ዳምጠው ሲዋጉ የሞቱት በዚሁ ቀኛዝማች ታፈሰ በሞቱበት የጦር ግንባር በሰማዕታ ጉብታ ይመስላል ። ተዋግተው የሞቱትም ከመስኮብ በተመለሱ በዐሥረኛው ወር ምንም የዕረፍት ጊዜ ሳያጣጥሙ በዙረት ላይ እንዳሉ ማለት ነው ።

በተረፈ ከነዚህ በቀር በዓድዋ ጦርነት ሕይወታቸውን የሠዉት ከየመጽሐፉ የተለቀሙት ቀጥለው ያሉት ናቸው ።

፩/ ደጃች ማን እየ የፈረስ ስማቸው አባ ባሕር ፣ ቀድሞ የደጃች አመንሸዋ የጦር አዛዥ ነበሩ ። ደጃች አመንሸዋ ሲሞቱና ጦራቸው ለራስ መኰንን ሲሰጥ ፣ እርሳቸውም ወደ ራስ መኰንን ዞረው ባዬ ምኒልክ ፈቃድ ደጃዝማች ተብለው ጨርጨርን ይገዙ ነበር ።[2]

፪/ ፊታውራሪ ወልደ ሚካኤል የሜታው ባላባት የፊታውራሪ ገረሡ ልጅ ፣

፫/ ቀኛዝማች አባይነህ የቀኛዝማች ታፈሰና የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ አባት ፣

፬/ ቀኛዝማች ተገኘ ወርቅ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የታወቁ ዠግና ፣

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 267 ።
2 ቼ በለው ፣ ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ፣ ገጽ 28 ።

፭/ ፊታውራሪ እምባዬ ከዓድዋ በፊት በማይ መሬት ጦርነት የሞቱ፣
፮/ ቀኛዝማች ተሰማ ወልዴ ፣
፯/ ፊታውራሪ ሸንኩሩ የደጃች በሻህ ጭፍራ ፣
፰/ ባላምባራስ በለው ፣
፱/ ” እደራ ፣
፲/ ” ሰይፉ ፣
፲፩/ አቶ ሙላቱ የፈረስ ዘበኛ ።

የካቲት 23 ቀን ከማለዳ ጀምሮ እስከ እኩለ ሌሊት በቀየው በዚህ ጦርነት የሞቱት ብዙዎች መሆናቸው ግልጽ ነው ። በንጉሠ ተክለ ሃይማኖት ፣ በየራሶቹና በየደጃዝማቾቹ ውስጥ ሆኖ ዘምቶ የሞተውና የቆሰለው ብዙ መሆኑ ሲታወቅ ከሰነድ ጥፋት የተነሣ ፣ ስማቸውን በዚህ የታሪክ መጽሐፍ ላይ ለማንሣት አለመቻሉ ያሳዝናል ።

ከዚህ ጋር ደግሞ ፣ ካፒቴን ክሉሼት የሚባል የፈረንሳይ ተወላጅ በበጅሮንድ ባልቻ ውስጥ ሆኖ በመድፍ ኢጣልያኖችን በመውጋት ኢትዮጵያን የዓድዋለት ማገልገሉን ልናስታውስ ይገባል ። እርሱም በፈረንሣይ ጦር ሠራዊት ውስጥ በመድፈኛ ክፍል ሳለ ፣ ላፄ ምኒልክ ገብቶ በጦር ትምህርትና በሌላውም በብዙ ወታደር ነክ ጉዳይ ሲመክርና ሲያገለግል የቆየ ነው ። በጦርነቱ ዋዜማ ዓመቱን ሁሉ ወታደሩን የጠመንጃና የመድፍ አተኳኮስ ሲያስተምር ነበረ ይባላል ። በኋላም ጦርነቱን ለመካፈል አልጋውን ከሚጠብቁት ከራስ ዳርጌ ተሰናብቶ ከአዲስ አበባ ወደ ጦሩ ግንባር መጥቶ የካቲት 22 ቀን ደረሰ ። በማግሥቱ ሲዋጋ ውሎ ከድሉ በኋላ በተራው እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ መኰንን ባፄ ምኒልክ ፊት ሲፎክር የተማረኩት ኢጣልያኖች አይተውታል ።

ጆቫኒ ቴዶኒ የሚባለው ምርኮኛ የጦር መኰንን በጻፈው ውስጥ ስለ ካፒቴን ክሉሼት እንደዚህ ይላል ። “. . . በ6 ሰዓት በንጉሡ ድንኳን ፊት እኛ እስረኞቹ ስናልፍ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን በራፍ ላይ እግሩን አጣምሮ የተቀመጠ ጠጉሩ ወርቅማ (ብሎንድ) . . . እኛን በንቀት እያየ የሚስቅ ነጭ አየሁ ።. . .[1] ብሏል ።

በተረፈ በዓድዋ የወደቀውና የቆሰለው የኢትዮጵያ ወታደር ከነመኳንንቱ ቁጥሩ በትክክል አይታወቅም ። ግራዝማች ዮሴፍ አዲስ

1. I Riccordi di un Prigioniero, G. Tedone, P. 44; IL Generale Salsa; E. Ganevari P. 97.



አበባ ላሉት ለሙሴ ሞንዶን ሲያስተላልፉ ፣ የሞቱትን ቁጥር 3867 አድርገውታል ። እነኮንቲ ሮሲኒ ከብዙ የኢጣልያ መጽሐፎችና ከቃል ጥያቄ ለቅመው የሞቱትን ቁጥር ከ5 እስከ 7 ሺ ከፍ ሲያደርጉት ፣ ግማሾቹ ከ7 እስከ 10 ሺ አድርሰውታል ። የቁስለኛውንም ልክ ወደ ሟቾቹ ቁጥር የሚያደርሱት አሉ ። ሚስተር በርክሌ የሚባሉት እንግሊዛዊ የሟቾቹን ኢትዮጵያውያን ቁጥር 7ሺ ፣ የቁስለኛውን ቁጥር 10 ሺ አድርሰውታል ።[1]

ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ከመሳፍንቱ ፣ ከመኳንንቱና ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሰፈራቸው ከተመለሱ በኋላ በተገኘው ድል ምንም እንኳን ደስታ ፣ ቢደረግ ስለሞቱትና ስለቆሰሉት በደስታው ጐን ሐዘን ፣ ዋይታና ለቅሶ ፣ እንደ ተደረገ የታወቀ ነው ። በማናቸውም ድል አድራጊ አገር እንደ ሚደርሰው የንጉሠ ነገሥቱም የሁሉም ደስታ በሐዘን የተበረዘ ነው ማለት ይቻላል ። ወደ ሰፈር መልስ ከሆነ በኋላ ፣ ከማግሥቱ ዠምሮ ንጉሠ ነገሥቱ በያለበት የወደቁትን የኢትዮጵያውያኑን ሬሣ እያስለቀሙ ሲያስቀብሩ ፣ ቆስሎ የወደቀውን ወይም በቃሬዛ ከየክፍል ጦሩ የመጣውን ሁሉ በመድኃኒት ሲያሳክሙ ፣ በየመንደሩም እያሳደሩ ሲያስታምሙ ፣ በየጦሩ ጐራ በየአለበት የተበታተነውን የጠላት መድፍና ጠመንጃ ፣ ጥይትና ቀለህ ሲያሰበስቡ ሰነበቱ ። ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌይቱ ዠምሮ ሁሉም በዕብሪተኛው ጠላት ላይ በተገኘው ድል የተደሰተ ቢሆንም ከታወቁት አርበኞች ከነገበዩ ፣ ከነታፈሰ ጋር በጠቅላላው ቁጥራቸው እስከ 7 ሺ የሚደርስ ከመኳንንት ፣ ከሹማምንትና ከተራ ወታደርም ስለሞተው ወገኑ ፣ ሁሉም ማዘኑ የታወቀ ነው ።

ይህን አስመልክተው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፣ “ከስልፍ ላይ ስለቀሩት እጅግ አጥብቆ ሐዘን ሆነ” ካሉ በኋላ ፣ እልፍ ብለው “ንግሥቲቱ እቴጌ ጣይቱ ስለ አሽከሮቻቸው ፣ ስለ ወዳጆቻቸው ፣ ስለ ክርስቲያኑ ማለቅ መራራ ሐዘን አዘኑ ። ብርሃን የመሰለ ፊታቸው እጥላስ (ጥላት) እስኪመስል አለቀሱ . . . ነገር ግን ፣ እንደ ተሆሉ ብዛት ፣ እንደቀኑ ርዝመት ፣ ሰው ሞተ ብሎ ያዘነ የለም ። ባሏም ፣ ልጅዋም ፣ ወንድሟም የሞተው እንኳን አልጋው ቀመልን ነው እንጂ ፣ ባሌ ልጄ ወንድሜ ሞቱብኝ ብሎ ያዘነ የለም”[2] ሲሉ ገልጸውታል ። ያዘነ የለም ማለታቸው ያነጋገር ፈሊጥ ወይም ከሐዘኑ የተገኘው ድል መብለጡን ለማመልከት ነው እንጂ ፣ ሐዘኑማ ሐዘን መሆኑ አይቀርም ። በሐዘኑ ላይ ግን ፣ የድል አድራጊነትና የነጻነት ደስታ ተበርዞ ሐዘኑን አቀዝቅዞታል ማለት ነው ። እነዚህ ሁሉ እልቀው ድሉ ባይገኝ ኖሮ ሐዘኑ ከመራራ ደረጃ ላይ ይደርስ ነበር ።

1 Italia ed Etiopia . . . P. 452, G.F.H. Berkeley PP. 346—347
2 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ—ገ.ሥ. ገጽ 257—268